# አንድ ለአምስት



ከአስፋው ዳምጤ

t.me/OLDBOOKSPDF

# አንድ ለአምስት

ከአስፋው ዳምጤ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፹

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ / TEL. 11 27 19

ፖስታ ሣ.ቁ. / P. O Box 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል — ከሉቃስ አግረ

ንግድ ማተሚያ ቤት

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማውጫ

1. እንደ መግቢያ ........................................ ፫
2. ምዕራፍ አንድ
መነሾዉ ........................................ 1
3. ምዕራፍ ሁለት
በማገሥቱ ........................................ 31
4. ምዕራፍ ሦስት
ወንድይራድ ተፈሬ ........................................ 63
5. ምዕራፍ አራት
'ሐሙስ የቀን ቅዱስ' ........................................ 90
6 ምዕራፍ አምስት
'ብርሊ ከነቃ ....' ........................................ 180
7. ምዕራፍ ስድስት
ልክ በሳምንቱ ........................................ 254
8. ምዕራፍ ሰባት
እሑድ ........................................ 278
9. ምዕራፍ ስምንት
የተረፈዉ ተገኘ ........................................ 300
10. ምዕራፍ ዘጠኝ
የሁለተኛዉ ሣልስት ዕለት ........................................ 307
11. ምዕራፍ ዐሥር
የፍጻሜዉ ዋዜማ ........................................ 342
12. ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
ዝግጅት ........................................ 403
13. ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
ውሳኔ ........................................ 429
14. ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት
ፈረሰ ........................................ 438

@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አንድ

## መ ነ ሸ ዉ

ወሩ ታኅሣሥ ፣ ቀኑ ቅዳሜ ፣ ሰዓቱ ዐሥር ተኩል ግድም ነው። ሥፍራዉ አዲስ አበባ ዳርቻ ፣ ከላምበረት ወዲያ ከትምህርት ቤቱ ወዲህ ፣ ከደሴ መንገድ በስተሰሜን ፣ አዳገቱ ላይ ነው ። ቤቱ ትልቅና ዘመናዊ ፣ ግቢዉ ሰፊና ባላትክልት ፣ አጥሩ የሽፍሻፌ ፣ የግቢዉ በር የብረት ነው ።

አረንጓዴ የብረት በሩን ዘበኛዉ ተሰማ ከፍቶ ፣ አንዲት ጥቁር አውቶሞቢል—ኦፔል ካዴት—የቀኝ ወገን አግጣጫ ማሳያ ምልክቷን ፣ ብልጭ— ድርግም እያደረገች ወደ አውራ ጐዳናዉ አዘቅዝቃ ፈረጠጠች ። ስትደርስ ተንሸጥሺጣ ቆመች ። በውስጧ ያለው የሚነዳት ወጣት ብቻ ነው ።

ወጣቱ በለጠ ፣ ልቡ በጣም መጣደፉና ከግሥጋሤው በመገታቱ መበሳጨቱ በጉልህ የሚነበብባቸው ዐይኖቹን ፣ እፊቱ በግራና በቀኝ መንገዱን እያዘበት እንስሶች ላይ አንከባለላቸው ። ዐይን የሚገድል ቢሆን ኖሮ ፣ በለጠ ጡጫ ጡጫ በሚያህሉ ዐይኖቹ ሁሉንም እያሉበት ፍግም ለማድረግ ባልተመለሰም ነበር ። ዳሩ ግን ....... እንስሶቹ በበኩላቸው ፣ የማንንም መንገድ የያዙ ፣ ወይም ማንንም ከትልቅ ቀጠሮ የሚያስተጓጉሉ ሳይመስላቸው ፣ ያመኪና መንገዱን ወረው ፣ ወደ ከተማዉ ሕይወቱን ይዘውለት ያዘግማሉ ። እንኳን ሰዉ ፣ አጋሰሱ ፣ አህያዉ ፣ በሬዉና በጉ ዐፈርና አቧራዉን ጠልቶ አስፋልቱን መንገድ ወድዷል ። የአስፋልት መንገድ የሚሠራው ለነርሱ ሳይሆን ‘ ለተሽከርካሪ ነው ’ የሚባለውን ፣ ወይ አልሰሙም አለበለዚያም ሰምተው ከጉዳይ አልጣፉትም ። ስለዚህ ፣ ዛሬም



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት ዐይነት ነች ልጅቱ ? " አለ ተስፋዬ ፤ ያሰበውን ነገር ሁሉ አሳጥሮ ።

"እንዴት ፡ 'እንዴት ዐይነት ?' "

"ቆንጆ ነች ? ቀይ ነች ? ጥቁር ነች ? ወጣት ወይስ አሮጊት ?" አለ ተስፋዬ እንደ መበሳጨት ብሎ ።

"ቆንጆ ወጣት ነች ። "

ተስፋዬ ጣዕሙ ያለቀውን መስቲካ ከወንድይራድ ሲጃራ መኩ ስተሪያ ውስጥ ጣለውና ፤ "እንደ በለጠ አነጋገርማ እንደሰዋ ያለ ሴት ' ድሮም አልነበረም ፡ አሁንም የለ ፤ ወደፊትም አይኖርም ' ። ብቻ ፡ የሱን ነገር ታውቃለህ ፡ ሳያት ሁሉ ዘወትር እንደ ደነገጠ ነው ። ስለዚህ ልቡን ስለ ነደፈችው ሴት ትክክለኛ ግምት ይሰጣል ብዬ እሱን መስማት ትቻለሁ" አለ ።

"ለምን ልጁን ለቀቅ አታደርገውም ? ባንተ ፍቅር ነገር አል ገባ ። "

" ምን ላድርግ ፤ ያናድደኛል ! ወንድ ልጅ ለሴት እንደዚህ መሆን የለበትም ። "

"እንዴት ነው መሆን የሌለበት ? "

"ባያት ሴት ሁሉ መነደፍ ። 'የነደፈችውን' ሁሉ ለማግባት መወጠን ። "

"ያያትን ሴት ሁሉ የሚያሳድድ ማን ሆነና ነው ? " አለ አበራ ፤ በምጸት ።

"እኔ ልጁ ታድያ እነድፋለሁ እንጂ አልነደፍ ። እንደሱ ልቤ ንና ገንዘቤን በማይረቡ ሴቶች ላይ አላባክን . . . . . ያኔ የጥብቅና ጽሕፈት ቤት የከፈተ ጊዜ ያከማቸውን ብር ሁሉ የት አደረሰው ? ለሴቶች ስጦታ መግዣ አይደለም ያዋለው ? "



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ያንተ ተጠንቅቆ መንዳት ብቻ እኮ ካደጋ አይሰውርህም ። ስንቱ ነው እቆመበት የሚገጭ ” አለ አበራ ።

“ ለዚህ ነውና መጠንቀቅ የሚያሻው ። የመኪና አደጋ እኮ በሌላ መገጨት ብቻ አይደለም ፤ ሌላዉን መግጨትም አለ ። ካል ተጠነቀቁ የቆመ መኪና መግጨትም ይመጣል ። ስንት ሰዎች ናቸው በገዛ እጃቸው ነድተው ከድልድይ እየዘለሉ ወንዝ የሚገቡ ” አለ ተስፋዬ ።

“ እነርሱማ የትራፊክ ፖሊስ የመሰለ ሰው ወደዚያ እየመራ ቸው ነው አሉ ! ” አለ አበራ ፤ ፈገግ እንደ ማለት ብሎ ።

“ እነሱ እነሱ ሰክረው ነው ። ልብ ብላችሁ እንደሆን የዚህ ዐይነቱ አደጋ ሁሉ ደረሰ የሚባለው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነው ” አለ ወንድይራድ ፤ ነገሩ ወደ ዋዛ ፈዛዛ በመመለሱ እየተደሰተ ።

“ነውና ! ኢጋንንት ከተማውን የሚወርሩት በዚያን ሰዓት አይደለም ! ” አለ አበራ ።

“ እሱን ተወው ። በሙሉ ብርሃን ፤ እጠራ ሜዳ ላይ — ሰውም መኪናም ሳይኖር ማንም ሳይነካቸው — ከመጠንቀቅ ጉድለት የተ ነሣ በገዛ እጃቸው የሚገለበጡ ስንት ሰዎች አሉ ” አለ ወንድይ ራድን እየተመለከተ ተስፋዬ — ያበራን ፌዝ ተወት አድርጐ ።

“ካልክስ ፤ ከመኪና መንገዱ ውጭ ፤ እግረኛው መንገድ ጠርዝ ላይ በጥሞና የቆመውን የመብራት ዕንጨት ፤ በመኪናው ተምትሞ የነቀለ እኔ የማውቀው አንድ ሰው አለ ። ብቻ ፤ ያደጋ መድ ረሻው እቅጣጫ ብዙ ስለሆነ ፤ እሱን ሁሉ ካሰብን መኪና መን ዳት አንችልም ” አለ አበራ ።

“ ባጭሩ ምንድር ነው የምትለው ፤ መጠንቀቅ አያስፈልግም ነው ? ” አለ ተስፋዬ ።

“የለም ፤ መጠንቀቅ የማይቀር ነው ። የሌላውን ሳይሆን የራ ስን አካልና ሕይወት ለማዳን ። ብቻ ፤ አደጋን ፈጽሜ እስወግዳለሁ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

አበራ አንዱ ሶፋ ላይ ተለጥጦ ተቀምጦ ፣ የተዘረጉ እግሮቹን አነባብሮ አንዲት አጭር መቀመጫ ላይ አሳርፎ ፣ እንደሚጸልይ ሰው እጆቹን አጋጥሞ በአውራ ጣቶቹ ጉራዱ አፍንጫውን እየጭ ዝቆ ፣ ሙዚቃ ሲሰማ ተስፋዬ አስተዋለውና ፣ "እንዴት ነው ፣ ዛሬ ምንም ፕሮግራም የለህም ? " ሲል ጠየቀው ።

" የለኝም . . . . . ' ያቺ አሮጊት ' ወደ ዐሥር ሰዓት ተኩል ላይ እደውልልሃለሁ ብላኝ ነበር ። እንደ ልማዷ ሰዓት አሳልፋለች። የሰዋን ስልክ እጠብቃለሁ ። "

"ምነው እባክህ ፣ ደብራቱን ነው እንዴ 'አሮጊት' የምትላት?" አለ ተስፋዬ የተቆጨባት በመምሰል ። ነገር ግን ፣ ዘወትር አበራን ያቺ አሮጊትህ ' የሚለው እሱው ነው ።

" ምን ማለትህ ነው ፣ ኻያ አምስት ዓመት ሲሆናት እኮ ነው ! " አለ አበራ ፣ በምጸት ።

" ታዲያ በኻያ አምስት ዕድሜ ሆኑ እንዴ አሮጊት የሚኮ ነው ? ተው ጡር አትናገር ፣ በሴት ልጅህ ይደርሳል ። አንተም ሴት ልጅ ወይፊት ይኖርሃል " አለ ተስፋዬ ፣ ማልሙጡን በመቀጠል ።

" አብጀለሁ እንዴ ልጅ የምወልደው — ያውም ሴት ልጅ ! "

" ቃለሚን ለማግባት ቆርጠህ አልነበረም ? ከቀለሟ ጋር ትጋብታችሁ ቢሆን ኖሮ እኮ ይኸኔ አንድ ሁለት ሴት ልጆች ታደርጉ ነበር ። ደግሞስ ፣ የልጅህን ጾታ አንተ ሆንክ የምትወስነው?"

" ኖሮን ያዝልኝ ። ደግሞ የሞተውን እንሥተህ እንደ ምክ ንያት አትስጠኝ ። "

" ምን ታውቃለህ ፣ ሌላ እሰዋን የመሰለች ታጋጥምህ ይሆ ናል ። "

" ይህ የመሸጋገሪያ ዘመን የምትሉት እስኪያልቅ ፣ እኔ ያንተ ወንድም እንኳን ልጅ መውለድ ሚስትም አላገባ ። እሱን ከተሻ ገርን በኋላ ያኔ ጠይቀኝ ። እኔም እስከዚያ አስብበታለሁ ። "



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ለመሆኑ መቼ ይመስልሃል ይኸ ዘመን የሚያልቀው ? እኔ ነፍስ ካወቅሁ ጀምሮ እንዲሁ እንደ ተሸጋገርን ነው ። መቼ ነው ተሻግረነው የምናርፈው ! "

" ምናልባት ዐሥር ዓመት ፣ ወይ በላይ ወይ በታች ። እንጃ ! "

" እስቲ ዐሥሯን ዓመት እንኳ ባሁኑ ዕድሜህ ላይ ደምራትና ውጤቱን ንገረኝ ። "

" ለምን ? " አለ አበራ ፣ ነገሩ ገብቶት ፊቱን በፈገግታ ለመሙላት በከንቱ እየጣረ ።

" አይ ፣ በዚያን ጊዜ የሚፈልግህ ይኖር እንደሆን ለማግመት !! . . . ዱሩ እያወቅሁት ምን አስጠየቀኝ ። አንተ እንደሆነ የምትኖረው ከዕለት ወደ ዕለት እያልህ ነው ። ስለ ነገ አታስብም ። ተሳስተህም ያሰብህ እንደሆን የሚታይህ ብርሃን ብቻ ነው " አለ ተስፋዬ ።

" አቤት ! አቤት ! አንተማ ስታስብና ስታቅድ አንጀት ስታርስ ! ለያውስ ስንት ዓመት ሙሉ የቀጠቀጥኸው ስለ ኢኮኖሚና ስለ ማቀድ አይደለ ! " አለ አበራ ፣ በፌዝ ።

" አሀ ! አንተ የተማርከውን የጋዜጣ ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል ነዋ ፣ ሁሉን ነገር ወደ ትችትና ወደ ንትርክ የምትቀይረው ! "

" አትሳሳት ፣ ወሬና ክርክር የጋራ ሀብታችን ነው ። 'ጋዜጠኛ ነገረኛ' የምትሉም የመሃይም አስተያየት ነው . . . . በል አሁን የቀጠርህ ሰዓት — " ብሎ የጀመረውን ዐረፍት ነገር ሳይጨርስ አግጣጫ ቀይሮ ፣ " ለመሆኑ ዛሬ አንተን ያዘዘባት ማን ነች ? " አለ አበራ ።

" ተድላና ደስታ ያዘዘላት በል ። . . . . ብርቱካኔ ናት ። "

" ሁሉአገርሽስ ? — አሁንማ እንደ ሸሚዝ ሳይሆን ፣ እንደ ክራባት ሆነ የምትቀያይራቸው ። "


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰማ ፣ በሩን ዝግ ብሎ እየዘጋ እጅብ ያሉትን ሰዎች አትኩሮ ቢመለከት ፣ ይደባደባሉ ። ሁለተኛውን መዝጊያ ሳይገጥም ቆመ ፤ ሐሳቡን ጥሎ ወሬ ማየቱን ቀጠለ ። ሁካታውና ጩኸቱ አየለ ። ሉሉታው በረከተ ።

አበራ ከቤት ወጥቶ ፣ “ ምንድር ነው ? ” ብሎ ጠየቀ ።

ተሰማ ፣ “ እዚያ ባቡር መንገዱ ላይ ሰዎች ይደባደባሉ መሰ ለኝ ” አለ ።

“ በል ዝጋውና ና ። አለበለዚያ ተባራሪ ድንጋይ እናትህን ይልሃል ። ”

“ እስታሁንስ የሚናረቱት በዱላ ይመስላል . . . . ብቻ ማማው በኋላ ምስክርነቱ ነው እንጂ ” አለና ተሰማ ፣ ለመጨረሻ ጊዜ እጀቡ ላይ ዐይኖቹን ሰኩቶ የሚበቃውን ያህል ከተመለከተ በኋላ ፣ በሩን ዘግቶ ለንብርቱ ለማውራት ወደ ማድቤት አመራ ።

ከበደ ብቅ ብሎ ፣ “ ስልክ ይፈልግዎታል ” አለው አበራን ። ራመድ ራመድ ብሎ እቤት ገብቶ ስልኩን ቢያነሣ ፣ ደብሪቱ ነች ።

“ እንዴት ነሽ ? ”
“ አለን ፣ ይመስገነው . . . . ”
“ ምክንያቱስ ? ” አለ ፣ ማንባሩ እየተቋጠረ ።
“ እሱ ሌላ ጊዜ ሊሆን አይችልም ? ”

“ መቼ ? ” አፍንጫው መነፋፋት ጀመረ ። ሲናደድ አፍን ጫው ይነፋፋል ።

“ ነገስ ? ”

“ እሱስ ፣ ከፈለግሽ አጥጋቢ ምክንያት ልትሰጫቸው ትችይ ነበር ። ”

“ አባክሽ ማምለጫ ሰበብ አትፈልጊ አይደለም ። ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ለማናቸውም ፤ ደኅና ሁኚ ” ብሎ ስልኩን ሲዘጋ ፤ አበራ ብስል ቀይ ገጹ ዱሮ ገና በንዴት ልውጥውጥ ብሏል ። በቀጥታ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ ። ራስጌ በቀኝ በኩል ካለችው ኮሞዲኖው ውስጥ አንድ ነገር አውጥቶ አደረት ኪሱ እየከተተ ከቤት ወጣ ።

“ እኔም ሽርሽር መሔድ አማረኝ ” አለ ወንድይራድ ፤ አበራን በረንዳ ላይ ደርሶበት ።

“ ምነው ተስፋዬን አላሰኘኸም አላልከውም ? ”
“ አሁን አሰኘኸ . . . ለመሆኑ ወዴት ነው ያሰብኸው ? ”
“ ወደ ደብረ ብርሃን አግጣጫ ። ”

“ እንግዲያው ፤ የኪ በር አውርደኝና ስትመለስ ከወደ ለገጣፎ አጠገብ ታገኘኛለህ ። ”

“ እሺ ፤ ና እንሒድ . . . ግን ፤ ለምን ይኸን እንደምታደርግ ያልገባኝ እንዳይመስልህ ! ” አለ አበራ ።

“ በላ የሰውን ሐሳብ ማንበብ እችላለሁ በለኛ ። ሳይኮሎጂ እንኳ የተማርኩት እኔ ነበርኩ ። እኔ ሳይኮሎጂስቱ ማድረግ የማል ደፍረውን ታዲያ አንተ ጋዜጠኛው ዘለህ ትገባበታለህ ? ” አለ ወንድይራድ ፤ የአበራን መቆጣት ከተረዳ በኋላ ወደ ሌላ አቅጣጫ ነገሩን እያመራ ።

አበራ ምንም ሳይመልስ መኪናው ውስጥ ገባ ። የደብሪቱ ቀጠሮ ማፍረስ እጅግ አናድዶታል ። ግን ፤ አሁን ንዴቱን ያባሰበት መናደዱን ከአንጋገሩ ደብሪቱ ማወቋን ማመኑ ነው ። የወንድይራድም አብሮት መምጣት መፈለግ አላስደሰተውም ። ብቻውን መሆን ፈልጎ ነበር — ስለ ደብሪቱ ለማሰብ ።

ደብሪቱ ቆንጆ አይደለችም ። ግን የደስ ደስ አላት ። ለአበራ ደግሞ በተለይ ጥርሶችዋ ያምሩታል ። ብዙ ሣቅና ፈገግታ ትወዳለች ፤ በተለይ ከአበራ ጋር ስትሆን ። ምንም እንኳ ለደብሪቱና በጠቅላላውም ለሰዉ ሁሉ — ለጓደኞቹም ጭምር — ስለርስዋ እስከ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ሴት አያሰችም ፤ ወንድ ነው ። "
" ወንዶች ለመሆኑ ይኸን ስልክ ያውቁታል እንዴ ! "

" ኡ ኡ እቴ ! የነጋዴዎች ምሥጢር ጠባቂ መኮኑ ነው ! "

" እንቺ ይኸ መላስሽ ፣ ምን ይሻለው ይሆን ? — " ብሎ ያሰበውን ተናግሮ ሳይጨርስ ስልኩ ወዲያው መልሰ ጮኸ ።

' የዚህ ቤት ስልክ አንዳፍታ አያርፍም ። ዘላለም እንደ ደወለ ነው ። ቅዳሜና እሑድማ ሲጮህ ነው የሚውለው ። ኮሬንቲ ዉን የሚጨርሰው እሱ ነው ' እያለች ብርቱ ስታነበንብ ፣ ከበደ ወደ ግሎን መሮጥ ጀምሮ ነበር ። " እባክህ ተወው ። በኋላ ይደውላሉ ከፈለጉ " ብትለውም እየሮጠ ሔዶ ስልኩን አነሣ ። ብርቱም መጥታ ምግብ ቤቱ ስትደርስ ቆማ ታዳምጥ ጀመር ።

" ሃሎ ! " አለ ከበደ ። ጥቂት ዝም ካለ በኋላ ፣ የቢቱን የስልክ ቁጥር ተናገረ ።

" የሉም ፤ ሁሉም ወጥተዋል ። "
" ማታ ሲመጡ እምነግራቸው መልክት እንዳለ ? "

" እረ በቁልቢጨ !! . . . የት ? " አለ እሬቱ ላይ ድንጋጤ በጉልህ እየተነበበ ።

" የት ናቸው — አሁን ? "

" እሺ — እሺ ። " ስልኩን ዘጋና ከዚያ ፣ እስልክ ማውጫዉ ላይ ያለችውን ደብተር አውጥቶ ያገላብጥ ጀመር ። ሰትምህርቱ ጀማሪ ስለሆነ ፣ የተበጫጨሩትን ፊደሎችና ቁጥሮች በቀላሉ መለየት ተሣነው ። ብቻ ፣ የሚይዘው የሚያደርገው ስላጣ ፣ ደብተሩን ከፊት ወደ ኋላ ፣ ከኋላ ወደ ፊት ያገላብጥ ጀመር ። ' ለማን ልንገር ፣ የትስ ልሒድ ? ' እያለ በሐሳብ ተጨነቀ ፤ ተጠበበ ። ዳሩ ግን ፣ ደብተሩን ከማገላበጥ ፣ እጁን ከማፍተልተል ሌላ ምንም ያደረገው ነገር አልነበረም ። ብርቱም ይኸ ሁሉ ሲሆን ደንገጥ ብላ ትመለከተው ነበርና ተጠግታ ፣ " ምንድነው ? " አለች ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ አሁን የዴወሉት ሰው ጌቶች‘የመኪና አደጋ አግኝቷቸዋል’ አሉ ። ወደ ትራፊክ ቢሮ ሔዱ ነው የሚሉት ” አለ ከበደ ።

“ ውይ . . . . ማንኛው ? ” አለች ብርቄ ።

“ ጋሼ በለጠ ። ”

“ ታዲያ ምን ይሻላል ? ”

“ አንዱን ጓደኛቸውን ባገኝ ብዬ ነበር ፤ በስልክ ። ”

“ ባሁን ሰዓት በቅዳሜ ምድር ማን ቤት ይገኛል ብለህ ነው ?” አለች ብርቄ ።

“ ምን ይታወቃል ፤ ድንገት ። ”

“ አይ ! ባክህ ቅዳሜ እንኳን መኪና ያለው ቀርቶ የሌለውም በሌይቸንቶና ባቶቡስ ሽርሽር ይሔዳል ። ባለቤት ቀርቶ የታደለ አሽከርና ገረድም ከየመቤቱና ጌታዉ ጋር ቅዳሜና እሑድ በመ ኪና ይንሸራሸራል ። እኔ ብቻ — ብቻ ነኝ ዘላለም ያልታደልኩ ። አንድ ቀን ለርሙ እንኳ ሰው ወስዶኝ የማላውቅ — ሽርሽር፤በመኪና” አለች ብርቄ ፤ እየተከዘች ።

“ አንቺ ደሞ አረመኔዋ ነሽ ! አሳዳሪያችን አደጋ ደርሶባቸው አንቺ ይሄን ነው አሁን የምታስቢው ? ” አላት ከበደ ፤ በመታ ዘብ ።

“ ታዲያ ምን እንዳስብ ትፈልጋለህ ? እረ ለኔ ማን ያስብል ኛል ? እኔ ራሴ ለራሴ ካላሰብኩ ። ደሞስ እኔ ለጌቶች ቸስብኩ አላሰ ብኩ ምን ፋይዳ እንዲሠራ ነው ? . . . . አሁን ያንተ ማሰብ ምን ይጠቅማቸዋል ፤ ጌቶችህ ? ” አለች ብርቄ ፤ እነጋገሩ እናደዳትና ።

“ እሱስ ውነትሽን ነው ። ምንም ማረግ አልችልም ። ቢሆንም ፤ መቼስ ሰው ለሰው መጥቀሙ የት ይቀራል ? ” አለ ከበደ ፤ እያሰበ ። ከዚያም ፤ ድምፁን ለዘብ አድርጐ ፤ “ አጠገባ ቸው ብሆን ኖሮ ደስ ባለኝ ነበር ። ጋሼ በለጠ ለኔ በጣም ደጊ ናቸው” አለ ከበደ ፤ ትክዝ ብሎ ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" በርከት አርገው ነበር ፣ ሁሉንም ነገር ሲገዙ ። እንዳያንስ ተረፍረፍ አድርገው ነበር የሚሠሩት ። "

" ውሃ ባናቱ አወጡ አይጨምሩበትም ነበራ ! " አለ ከበደ ፣ ፈገግ እያለ ።

" አይ የምን ውሃ ከልሶ ማንበጭበጭ ነው ? በዛ አድርጎ መሥራት ነው እንጂ ! " አለች ፣ ካንጀቷ ።

" እናንተ የምትበሉት ውስጥ ማለቴ አደለም እኮ ! የናንተ ከተጨለፈ በኋላ ለነጌቶች እሚቀርበው ውስጥ ማለቴ ነው ። "

" የለም ! የለም ! ለሁላችንም እንዲበቃ አርገው ነበር የሚሠሩት " አለች ብርቄ ፣ የከበደን ፈዝ ልብ ሳትል ። ገና ከት ዝታ ደመናዉ ውስጥ ጨርሳ አልወጣችም ።

" እንዲያው ጠዋት ማታ ግብር ትበሉ ነበር በይኛ ! "

" በጋሼ ብሩ ጊዜ ሁሉ ነገር በሽበሽ ነበር ። ምን ይሆናል ፣ አባረሯቸው — እሳቸውን የመሰለ ባለሙያ ! "

" ለመሆኑ ፍራንኩ እንዴት ወር ያደርስ ኖሯል ልጁ ? ባለ ቤቶቹም ቢሆኑ የሚያስጭኑት እህል የለ ፣ ሽምተው ነው ። የወር ደሞ ዛቸውን ጠብቀው ነው ። "

" አይ ሞኞ ! " አለች ብርቄ ፣ በዚህ የዋህና ደንቆሮ በምት ለው ሰው አስተያየት እየተደነቀች ። " የነሱ ደሞዝ የኔና ያንተ መሰለህ ? ከእነሱ አንዳቸው በወር የሚበሉትን ደሞዝ እኛ ባመ ትም አናገኘው ። ታዲያ ያ ራሱ የትና የት ነው ? ቁጠር ቢሉህ ቁጥሩ ይደናገርሃል . . . . ታዲያ ትንሽ ከነሱ ምግብ ብንበላ ምን እን ጎዳቸዋለን ? . . . እኔ ከሰው ይበልጥ አልበላ — ያው አንድ ሆድ ነው ያለኝ ። "

" እነሱም ሠርተው ፣ እኛም ሠርተን ነው የምናድረው ። ፈረ ንጅ አገር ሔደው ስንት ዓመት የተማሩት ብዙ ደሞዝ ለማግኘት ፣



@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ብላመላለሱ ብቻ ። እግዜር ያሳይህ ፣ ዐርባ ብር ! እኔ በሳት ተቃ ጥዬ ሠላሳ አምስት ብር ! ”

“ ተይው ገባኝ ። ከዚያ ከተላላኪ ወዳጅሽ ሰምቶሽ ነው ለካ በዚህ ሁሉ ነገር እንደዚህ ልቤን የምታደርቂኝ ። ዳዊት ደጋሚም እንደዚህ እያንበሰብሰው — የተማረው ። ”

“ ‘ዳዊት ደጋሚ’ ምን ያሰኝሃል ? እኔም እኮ ትንሽ ተምሬ ነበር ፡ እዚያ ደሴ ። ግን ዕድሉ ሰንኩል ሆኖ ነው ከተማሪ ቤት ከትንሽ ጊዜ በኋላ የወጣሁት ። ጌታው አቶ ሞት አባትና እናቴን ባንድ ዓመት ውስጥ አሳጥቶኝ ነው ፣ እንደዚህ ገረድ ሆኜ የቀረሁት ። የዕ ድል ጉዳይ ነው ! ” አለች ብርቄ ፣ ምርር እያለች ።

“ ታዲያ ያንች ዕድል ሰንኩል በሆነ ሌላው ሰው ምን ያርግ ትያለሽ ? ”

“ አንተንስ ጌቶችህ አሽከር ቀጠርን አይበሉ ፣ ጠበቃ ነው የገዙት ። ”

“ የምን ጥብቅና ፣ የምናገረው ለክሬ ነው ። እንኳ ብትሆኚ ፣ የበላሽበትን ወጪት ሰባሪ ነሽ ። በጃቸው በሌትሽ ጠጥተሽ ሾር ታስቢያለሽ ! ደግ አደለም ” አለ ከበደ ፣ እራሱን እየነቀነቀ . . . “ኧረ ለመሆኑ ይኸ ጋቢሽ ውነት የሥጋ ዘመድሽ ነው ? ወይስ ጋሼ ተሰማን ለማታለያ የፈጠርሽው ዝምድና ነው ? ”

“ ምንሽ ነው ልትለኝ ነው ደግ ? . . . . ዕድሌ ! ኮ ነው ። ሁሉም ምቀኛ ያዝብኛል ” አለች ፣ ዱብዳ ጥያቄው ያስደነገጣት መሆኑን ለመሸፋፈን እየሞከረች ።

“ ምቀኝነት አደለም ። ዘዴኛ ነሽ ማለቴ ነው ። ለራስሽ ታውቂበታለሽ ። ”

“ አንተም ካወቅህበት ደኅና መኖር ትችላለህ ። ብቻ አንተ ገና የገባህ አልመሰለኝም ። ለነጌቶች አሳቢ ዋና ሎሌ ነህ — ያሳደ ጉት ውሻ እንኳ — ” ስትል ፣ ከበደ ዞር ብሎ ሳታስበው በጥፊ ድር ግም አደረገባት ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ባቱ ነገር ያስብ ጀመር ። በተናገሩት ጊዜ ያላጤነው አንድ ነገር አሁን ትዝ አለው ። ‘ ሌላው ሁሉ ቀርቶብኝ ፣ ከሞቴ በፊት አያት ለመሆን ምናለ ብታበቃኝ ’ ያሉት በሰዝን ልቡናው አሁን ተሰማው ። በሐሳቡ በሮ ጀርመን አገር በርሊን ከተማ በቅጽበት ደረሰ ። ድምፁን ከፍ አድርጐ ፣ “አይሰማሙም” ብሎ ፈጥኖ ተመለሰ ። ከዚያ ፣ ብድግ ብሎ እመኝታ ቤቱ ያለችውን ትንሽ የንባብ ጠረጴዛ ኪሶች አንድ ባንድ ይበረብር ጀመር . . . . .



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሁለት

*በማግሥቱ*

ጠዋት ነው ። ከዳግማዊ ሚኒልክ ሆስፒታል በሥጋት የሚጠብቁት ሰልክ እስካሁን አልተደወለም ። በለጠ ፣ ተሰፋዬ ፣ አበራና ወንድይራድ ቁርሳቸውን ይበላሉ ። ጸጥታ በሞላ ቤቱ ሠፍኗል ። የሚሰማው ሹካና ቢላዋ ከሳሀን ጋር ሲጋጩ ፣ ወይም ማንኪያና ስኒ ወይ ሲኒና ማስቀመጫዉ ሲገናኙ ፣ የሚወለደው ድምፅ ብቻ ነው ። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ፣ ከበደ ከወጥቤት ወደ ምግብ ቤት ፣ ከምግብ ቤት ወጥቤት ሲመላለስ ፣ በመጫሚያዉና በወለሉ መገናኘት የሚፈጠረው ኳኳታና ሲጥሲጥታ ጸጥታውን ያደፈርሰዋል ። መጫሚያዉ የከበደን ክብደት መሸከም አቅቶት አቤቱታ የሚያቀርብ ይመስላል ። ከበደም ድምፁን ለማፈን በመጫሚያው ደረት እየረገጠ ወዲያና ወዲህ ሲመላለስ ፣ ለታዛቢ አቤቱታውን ለማጨንገፍ የሚጥር ይመስላል ።

እቤቱ ያሉት ሰዎች ሁሉ ምንም ባፋቸው ባይናገሩ ፣ ሁሉም ከየሐሳባቸው ጋር ይጫወታሉ — ከበደ እንኳ ሳይቀር ። ' እንዴት መጋጨታቸውን ሰምቼ አንድ ነገር እንኳ ሳላደርግ ቀረሁ ? በውነት መጥፎ ሰው ነኝ ። ከተማዉ እረመኔ አርጎኛል . . . . ቁም - ነገሩን ረስቼ በማይረባ ነገር ተታለልሁ . . . ፊታቸውን ሳየው ፣ ጋሼ በለጠ የሠራሁባቸውን በደል ፊቴን አይተው ፣ ውቃቢያቸው ነግሯቸው ፣ የሚያውቁብኝ ይመስለኛል ። ግን ፣ ምንም ለማድረግ አልቻልኩም ነበር ። ሳላስብ ቀርቼ እንኳ አልነበረም ' ይላል ከበደ ፣ በልቡ . . .

በለጠ ፣ ስለ ደረሰበት አደጋና ስለ ተንገላው ቀጠሮ ጸጥ ብሎ ከራሱ ጋር ያወጋል ። ' እርግጥ ፈጠን ብዬ ነበር እምነዳው ። ሆኖም



@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

“ አሁን የቡና ሰዓት ነው ፤ አምስት ሆኗል እኮ ” አለ ተስፋዬ ፤ ወደ በለጠ ዞር ።

“ አልሰማህም እንዴ ፤ ዛሬ እኮ እሑድ ነው ” አለ አበራ ፤ ተስፋዬን እየተመለከተው ።

“ ታዲያስ ? ” አለ ተስፋዬ ፤ ነገሩን ከቡናዉ ጋር ማዛመድ ሲጊዜው ግር ብሎት ።

“ ቢሮ አይደለህም ማለቴ ነዋ ! ”

“ በሠለጠኑት አገሮች በቅርበና በምሳ መኻል ቡና ፤ በምሳና በራት መኻል ሻይ ፤ ይጠጣል ” አለ ተስፋዬ በስጨት እያለ ። ቀጥሎም ፤ “ ሰዓቱም ፤ ለቡና ከቅትር በሬት ከአምስት ሰዓት እስከ ተኩል ፤ ለሻይ ከቅትር በኋላ ከዐሥር ሰዓት እስከ ተ ኩል ነው ” አለው አበራን ፤ በፌዝ ።

“ ምን ቁርጠኝ የሠለጠኑ ሰዎችን ልማድና ባህል አዘነጋለሁ ” አለ አበራ ፤ ፈገግ ብሎ ።

“ ይኽ ባህል ሊባል ይችላል ? ” ሲል ጠየቀ ወንድይራድ ።

“ ልማድ ይመስለኛል ” አለ አበራ ።

“ ልማድ ሁሉ ተደምሮ በጅምላ ሲሆን አይደለም እንዴ ታዲያ ባህል ተብሎ የሚጠራው ” አለ ተስፋዬ ።

“ እንዲህ ከተባለማ በዘመናችን የተለመደው አቢሮ ቡና መጋትም ያገራችን ባህል መሆኑ ነዋ ? ” አለ አበራ ።

“ አዎ — አዲስ እኛ የጨመርነው ” አለ ተስፋዬ ።

“ እርግጥ ያገር ባህል ነው ሊባል ይችላል ። ግን ፤ አዲስ እኛ የፈጠርነው አይደለም ። ይኸን ለመገንዘብ ፤ እስቲ በማናቸውም ሰዓት በየመንደሩ እንሒድ ። ወገኖቻችን ከአየል እስከ በረካ እያሉ እግን እያጨሱ ፤ ‘ የቡና ቁርስ ’ እየበሉ ፤ ቡና ሲያንቃርሩ እናገኛቸዋለን ። በልጅታችን ወቅት ፤ ‘ኑ ቡና ጠጡ በል ’ እየተ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ አሁን አይመቸኝም ፡ እንግዲ አለብኝ . . ይልቅ ማታ ራት ልጋብዝሽ ። ”

“ ማን ነች እሷዋ ? . . . አ — አዎ ። ”

“ ምናል ቃዲያ ። ራቃችንን በልተን ቀስ ብለን ለዳንሱ እን ደርሳለን ። ”

“ እሺ . . . በይ እስክዚያው ፤ ሰላም ። ”

ተስፋዬ የሚለውን ነገር ሲያሰላስል ነበርና ፡ እንዲቀጥል የሚ ጠበቅ መሆኑን ሲገነዘብ ፡ “ በደፈናው ከምንከራከር እስቲ አንድ ነገር ወስደን እንመልከት ። በአካባቢያችን ከሚነኑት ነገሮች አንዱ አሉባልታ ፤ ያልተጣራ ዜና ማዛመት ፤ ባጭሩ ከንቱ ወሬ ነው ። እንዲህ ዐይነት ሁናቴ እይሎና ሥር ሰዶ የሚገኘው መሃይምነት በሠፈነባቸው ኅብረተ - ሰቦች ዘንድ ነው ፤ ይላሉ ሊቃውንቱ ።

“ ይህ አባባል ፡ ትምህርትና ዕውቀት እየተስፋፉ ሲሔድ ይኸ ነገር እየመነመነ ሔዶ ይጠፋል ወደ ማለት ያደርሰናል ። ምክንያ ቱም ፡ አንደኛ ፤ ማናቸውንም ጉዳይ በጽሑፍ የማሥፈር ልማድ ከትምህርት ሊገኝ ይችላልና ። ሁለተኛ ፤ ዕውቀት ሲስፋፋ ‘ እን ዴት ? ምን ? ለምን ? ወዴት ? ’ የሚል የአስተሳሰብ ዝንባሌ ይፈ ጠራልና ።

“ በቃል የተነገረ ነገር ፣ ካንዱ ወደ ሌላው ሲሸጋገር እየተጨ መረበትና እየተጓደለት ስለሆነ ፡ መጀመሪያዉና መጨረሻዉ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ይሆናሉ ። ለማገናዘብና ለማጣራትም ያዳግ ታሉ ። በጽሑፍ ሲሆን ግን ፣ ይህ ችግር አይኖርም ። ትምህርት የተ ስፋፋበት ኅብረተሰብ ፣ ‘ እንዴት ? ምን ? ለምን ? ’ የሚሉ ጥያቄ ዎች ስለሚያበዛ ፣ ከንቱና ያልተጣራ ወሬ ማዛመት ይመነምናል የሚባልበት ስለዚህ ነው ።

“ እኛ ዘንድ ግን ፣ ትምህርት በተስፋፋ ቁጥር አሉባልታና ከንቱ ወሬ ፣ እንኳን ሊጠፋ — ኧረ እሱን እንተወው — እንኳን ሊመ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

አንዳንዱ ነገራቸው ታዲያ በጣም ያሥቀኛል ። ለምሳሌ ፤ የቀለምን ነገር እናብተውል ። ነጭ ቀለም ከጥቁር ይበልጣል እያሉ ይለፍፋሉ ። ግን ፣ በሙቀቱ ወራት ራቁታቸውን ፀሐይ ላይ ተሠጥተው ይውላሉ — ለመጥቆር ። እከሌ ወይም እከሊት ጥሩ ቡናማ ቀለም ሆኗል ወይም ሆናለች እየተባባሉ ይሞጋገሳሉ ። ባፋቸው ቢክዱም በግብር የሚገልጡት በቆዳቸው አለመደሰታቸውን ነው . . . ደግሞም ፣ ብዙዎቹን ቆዳቸውን ስታየው እውነት አላቸው ያሰኝሃል ” አለ አበራ ።

“ በላ አንተ ደግሞ የኛ ቆዳ ከነጭ ይበልጣል እያልክ ሰበክ ” አለ ወንድዬራድ ፣ ዝም ብሎ ሲያደምጥ ቆይቶ ።

“ እኔ ምን አሰበከኝ የሚበልጥ ይበልጣል ። ‘ ጥሩ ጠጅ ያላት ፣ አሻሻጭ አያስፈልጋትም ’ እንደሚባለው ነው ። ”

“ እንደውነቱ ከሆነ እኮ በቀለምና በዘር መኩራት ፣ ከታሪክና ከሥልጣኔ ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው ። በሥጋዊ ሥልጣኔ ወደፊት የተራመዱት ነጭ ወገኖች በለሆኑ ነው የቀረውን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱት ። ሀብታሞቹ እነሱ ፣ ኃያሎቹ እነሱ ” አለ አንሙናጉር ።

“ መናቁ በዕውቀት ብልጫ ቢሆን ኖሮማ ፣ እንዴት አንድ አውሮፓዊ ወይም አሜሪካዊ ነጭ ገጠሬ ወይም የሆቴል ቤት አሳላፊ ፣ ስንት ዲግሪ ያለውን ጥቁር ምሁር ሊንቅ ይችላል ? ግን ቢያደርገት ኖረዋል ። እኔ እኮ የማይገባኝ — በስመ ነጭ ሁሉ አልበርት አይንስታይን አይደለ ! ስንት ሚሊዮን ከብት ነጭ አለ — ደንቆሮ ! ” አለ አበራ ።

“ ታልክስ ፣ ንቀትና ኩራት የሚያጠቃቸው ዐላዋቂዎቹን ነው ። ያወቁ የጠየቁማ እንደዚህ ዐይነቱ ጥቃቅን ልዩነት መሠረታዊ እንዳልሆነ ያውቃሉ ። አንዱን ሰው ከፍ ወይም ዝቅ የሚያደርገው ፣ ችሎታውና ጠባዩ መሆኑን ዐዋቂዎቹ ያውቃሉ ” አለ አንሙናጉር ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

አጐናፍር ፈገግ ብሎ ፣ “ አሜሪካ ወጣት አገር ናት ። ደግሞም ሕዝቡ ከያለበት የመጣ ስለሆነ ፣ እስከዚህ ባህሉና ልማዱ ሥር የሰደደ አይደለም ። እንዲያውም ፣ አንድ ኅብረተሰብ አላት ለማለት መቻሉን እጠራጠራለሁ ። ማለቴ ፣ በዚህ ረገድ ከጥንታውያን አገሮች ጋር የምትወዳደር አይደለችም ። ስለዚህ ፣ አዲስ ነገር ለመቀበልና ለመከተል — ” ሲል ቀዝቀዝ ባለ አነጋገር ፣ ተስፋዬ ፈጥኖ አቋረጠው ።

“ መስኮብስ ? ”

“ በመሠረቱ የአውሮፓ አገር ናት ! ” አለ አጐናፍር ።

“ ወሬ ሀብት ሆኖ የሚሸጥ ቢሆን ኖሮ ፣ እኛ ሀብታሞች እን ሆን ነበር ” አለ ተስፋዬ ፣ በንዴት እየተብሰለሰለ ።

“ አሁን ገና አንጀት የሚያርስ ነገር ተናገርክ ። አንተ ብቻ ዛሬ ከንጋ ያፈሰስከው እንኳ ተለቅሞ ቢሸጥ አገራችን ትከብር ነበር !” አለ ወንድይራድ ፣ በምጸት ፈገግታ ፊቱን አጐናጽፎ ።

ተስፋዬ ክፉኛ ገላመጠው ። ወንድይራድ ግን ፈገግታው ቀጠለ ። ከዚያ አለንጋ ጣቶቹን ይጐነጉንና ይፈታ ጀመር ። ወንድ ይራድ እንዲህ ሲያደርግ ክርክር ሊያነሣ ነው ማለት ነው ። ሲያስብ ሲያነብና ሲጽፍ ጢሙን ይጐትታል ። ሲናገርና ሲከራከር ግን ጣቶቹን ይጐነጉናል ፤ ይተረትራል ። ይኸ የታወቀ ጠባዩ ስለሆነ ፣ አበራ ዐይን ዐይኑን እያየ የሚያመጣውን ይጠባበቅ ጀመር ።

“ እስቲ አንድ ነገር ሁላችሁንም ልጠይቃችሁ ። ዘወትር ወሬና ክርክራችሁ ፣ በሥልጣኔ ወደፊት ስለ መግፋት ነው ። የት ለመድረስ ነው ? ” አለ ወንድይራድ ።

“ የትም !! ” አለ ተስፋዬ ፣ በማመናጨቅ ።

“ እሠለጠኑት አገሮች ላይ ” አለ አበራ ፣ ወንድይራድ የሚ ያመጣውን እየተጠባበቀ ።

“ ለምን ? ” ሲል ጠየቀ ወንድይራድ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ጠማና ስኒህን ልይልህ " አለችው ብርቄ ከበደን ።

" ሁሌ ስኒ እንደ ዘቀዘቅሽ ። እንደዜ አይዝልሽ " አለና ከበደ፣ ቡናውን ፉት ይል ጀመር ።

ዘበኛው ተሰማ ፣ ' መንገድ ይልዎታል ' ብላው ተናዷል ። ወልደ ሥላሴን ግን ' ገንዘብ ታገኛለህ ' ስላለችው ለመጣበት ዓላማ የሚያመች ስለ ሆነለት ደስ ብሎታል ።

ከበደ ቡናውን ጨልጦ ስኒውን እየሰጣት ፣ " በይ መርዶ ውን ንገሪኝ " አላት ።

ብርቄ ስኒውን አጠገቧ ሕለው ሳህን ላይ ዘቀዘቀችው ። ቀጥሎ የቀረውን የቡና ዝቃጭ ለማጠንፈፍ እረከቡቱ ላይ ደፍታ አስቀመ ጠችው ። ጥቂት ቆይታ አንሣችውና ከምሯ ትከ ብላ አስተዋለችው። ስታስተውል ቆየች ።

" ምንው ዝም አልሽ ? እሱንም እንደኔው ' መንገድ ' ይለ ዋል ? " አለ ተሰማ ፣ ምሬት በተበረዘበት ፌዝ ።

" ወይስ የባሰ ጉድ ነው ? ' ጉድጓድ ይልሃል ' ብለሽ እንዳታ ሟርችብኝ ፣ ልባርጊ " አለ ከበደ ሥጋትና ፍራቻ በተቀየጠበት የውሸት ቀልድ ።

ወልደ ሥላሴ ግን ፣ በተጨፋኑ ፈገግታ ፊቱን አልብሶ በት ዝብት ይመለከታቸዋል ። ብርቄ የስኒ ማንበቡን ነገር በቁም ነገር ነው የያዘችው ።

" ብዙ ገንዘብ ታገኛለህ ይልሃል " አለች ብርቄ፣ ኖራ ኖራ ።

" ሁላችሁም ገንዘብ የምታገኙት ከየት መጥቶ ነው ? " አለ ተሰማ ፣ በታከተ ድምፅ ።

" እግዜር ላንዱ ሲሰጥ ከሌላው ወስዶ ነው ይባላል " አለ ወልደ ሥላሴ፣ ዛሬ ብርቄ ዘንድ የመጣበት ምክንያት ትዝ ብሎት ።

ከበደ በበኩሉ ደስ ደስ እያለው ፣ " ሎተሪ ይደርሰን ይሆ ናላ " አለ ። ሎተሪ ግን አልገዛም ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ለምንድነው አቦልና ሦስተኛ ብቻ ሲሆን የሚይዘው ? " አለች ብርቄ ፤ የማወቅ ፍላጎቷ ተቀስቅሶ ።

" አቦል ቡና እንደ ሕፃን ነው ። ሕፃን ንጹሕ ስለሆነ ፤ ይታ የዋል ። ሦስተኛዉ ደሞ ዕድሜውን አከትሞ ፤ ዐፈር ለመሆን እንደሚጠብቅ ሽማግሌ ነው ። ሁለቱ ውሸት አያውቁም ይባ ሉዋ " አለ ወልደ ሥላሴ ።

" የኔን ካላመናችሁ ተዉት ። እኔ አምንበታለሁ " አለች ብርቄ በመናደድ ።

ከዚያ ቡናው ተቀዳ ፤ ሁሉም ጠጡ ፤ ብርቄ እንደ ልማድዋ ስኒዎቹን ዘቀዘቀች ። ያንኑ መልሳ ተናገረች ። ተሰማ ስለ ደገመች በት የባሰውን ተናዶ ወጣ ። ከበደም ከእልፍኝ ተጠርቶ ወደዚያ ሲሔድ ፤ ብርቄና ወልደ ሥላሴ ብቻቸውን ቀሩ ።

" በይ ልሒድ " አለ ወልደ ሥላሴ ።

" ምን አስቸኰለህ ፤ ዛሬ እሑድ ነው ። "

" ዕቁብ አለብኝ . . . በያ ታዲያ ያን ያልኩሽን ? "

" እኔ ምንም የለኝ ። "

"ምን ታደርጊዋለሽ በወር ሠላሳ አምስት ብር እየተቀበልሽ ? "

" አሳዳሪነትህ ከቀረ ቆይቷል እኮ ! ረሳኸው መሰለኝ . . . በገዛ ገንዘቤ የፈለግሁትን ባደርግ አንተ ምን አገባህ ! "

" የለም ይኸን ማለቴ አይደለም ። እኔ ሠላሳ አምስት ብሬን ለቤት ኪራይ ፤ ለቀለብ ፤ ለዕቁብ . . . " ብሎ ሊቀጥል ሲል አቋርጣ ፤

" ለጠጅ !! " አለችው ።

" ምነው ስታውቂው ። እኔ ሰው ካልጋበዘኝ መች እጠጣና። ገንዘቡ እንዲያውም ዐመድ ነው ፤ ብን ብሎ ያልቃል ። ከዚያችው ላይ ተጠጥቶላትማ ምን ይኮናል ። ትንሽም የሚረዳኝ ብሪቱ ሽሮና



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ‘አበድሪኝ ?’ ” ብላ ኩት ብላ ሣቀች ። “ ይቺ ነች ጨዋታ ! ከመቼ ወዲህ ነው ደሞ እንዲህ የምትለው ? አንድ ጊዜ ከወሰድህ ወዲያ ለመሆኑ ትመልሳለህ እንዴ ? እንደ ልማድህ ፣ ‘ስጪኝ’ ብትል አይሻልም ? ”

“ አሁን የምጠይቅሽ ብድር ነው ” አለ አሁንም መልሶ ።

“ መቼ ልትሰጠኝ — ዕቁብ ስትቀበል ? ”

“ እዎ ፣ የቀረነው ሦስት ብቻ ነን ። ”

“ በዚህ በቁብ ከኔ እንኳ ስንቴ ወሰድክበት ። ከሌላውሳ የወሰድኸውን ያላንተና ያለእግዚር ማን ያውቃል ! ”

“ አሁን ታበድሪኛለሽ አታበድሪኝም ? ” አለ ወልደ ሥላሴ፣ ቁርጥ ባለ አነጋገር ።

“ ስንት ? ”

“ ምነው ቅድም ነግሬሽ — ዐሥር ብር ። ”

“ ይኸን ያህልስ የለኝም ። ግማሹን እሰጥሃለሁ ። ያውም ላመትባሉ ልብስ እገዛበታለሁ ካልኩት ላይ ቀንሼ ነው አምስት ብሬንም የምሰጥህ ። ሰማህ ? ‘ እሰጥሃለሁ ’ ፣ አላበድርህም ” አለች ብርቄ ።

ወልደ ሥላሴ ውስጡ ተነፈሰ ። የምትጐድለውን አምስት ብር ደግሞ የሚያሟላበት ዘዴ ፈጥኖ ተገለጠለት ። ግን ይኸን ዘዴ ሳይ ሠራበት አስቀድሞ እሷ እንድትሞላለት ጠንከሮ መከራከር ፈለገ ። “ መልካም ፤ አምስቱን ስጪታ ካደረግሽው የቀረውን በብድር ስጪኝ ” አላት ።

“ አሬ አባቴ ይሙት ፣ ቅዱስ ገብርኤልን ቀይ ሶልዲ ከዚህ በላይ አልሰጥህም ” አለችው ፣ ቈርጥ አድርጋ ።

“ እንግዲያው ያምስት ብር ሎተሪዎች እሱኝ ፣ ግገርኝ ። ”

“ ያንት ገድ ሲኔ ሆኖኝም አያውቅም ” አለችው ፣ እያሰበች ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሦስት

## ወንድይራድ ተፈራ

ተስፋዬ ገና ጠዋት ቢሮ እንደ ገባ ፤ ‘ ወደ ገጠር ሊዛወር ነው ’ የተባለውን ወሬ እርግጠኛነት ለማጣራት ፤ በቀጥታ እተክበሩ እቶ ድፋባቸው ዘንድ ሔዶ እባቸውን ራሳቸውን ለመጠየቅ ቃጥቆት ነበር ። ነገር ግን ፤ ወሬውን ቀድሞውኑ ለግሁ ብሎ ሹክ ያለለት ፤ ዘርፉ የሚባለው የሥራ ባልደረባው ሃይ ሃይ ብሎ አከላከለው። ግን ፤ በሌላ በብዙ በኩል ሞክሮ አንድ የሚጨበጥ ነገር ሳያገኝ ስለቀረ፤ ‘የጠላት ወሬ ነው ’ ወደ ማለቱ አዘነበለ ። እድሮበት የነበረውን ሥጋት ተስፋዬ ከልቡ እውጥቶ ጣለው ።

እሁን በልቡ ውስጥ ያለው የብርቱካን ነገር ነው ። ዕጮኛዋ ልታስመስለኝ ሞከረች ብሎ በመፉጠት ፤ ዛሬ ማታ ሲኒማ ሊወስዳት ቀጥሯት የነበረውን ፤ ምክንያት ፈጥሮ እፍርሷል ። ‘ ጥፋቱ የገዛ እራሷ ነው ’ እለ በሐሳቡ ። ‘ መጀመሪያውኑ “ እኔ ካንቺ ሴት ጋር ለመቆራኘት ዓላማ የለኝም ” ብዬ ካስጠነቀቅኋት በኋላ ፤ “ፍቅር ያዘኝ” የምትለውን እቲሆ ባቲሆ እልቀበልም። ለመሆኑ ሴቶች ከመቼው ነው ፍቅር የሚይዛቸው ? ’ ብሎ በልቡ ተደነቀ ። በብር ተካን ፈንታ ትርንጎን ሲኒማ ይዞ ሊሔድ ጋብዟት እሺ ብላለች ። እሱንና ትርንጎን ያስተዋወቀቻቸው ብርቱካን እራሷ ናት ።

ይኸን እያሰበ ፤ በለጠ እሱን ወደሚጠብቅበት ሥፍራ ተስፋዬ ፔገሮውን ጋለበ . . . . . .

በለጠ በበኩሉ ፤ ዛሬ ሥራ ሳይገባ ነው የዋለው ። መጀመሪያ መኪናውን እስንቅቶ ጋራዥ ካስገባ በኋላ ፤ ሳይወላውል



@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

መሻት ። ያንን ሲያገኙ እንደገና እንደገና ሌላ መመኘት ፣ እጅ መዘርጋት . . . . ይኸ ሁሉ የት ለመድረስ ፣ ምን ለማግኘት ነው ? ሩቅ ሆኖ የሚያምረው ፣ ያለ የሚመስለው ፣ ቀርበው ሲያዩት አስከፊ ነው ፣ ሲጨብጡትም ጉም ነው ። ስለዚህ ፣ ሕይወት ትርጉም የሌላት የቀን ቅዠት ናት ። የሚታሰበው ሐሳብና የሚፈጸመው ድርጊት ሁሉ ባዶና ከንቱ ነው ።

'ሁሉ ከንቱ' የሚለው ወንድይራድ ኻነሆ ለጊዜው አይሎ ፣ በወረቀት ሰፍሮ በኤንቨሎፕ ተደፍኖ የተቀመጠው ውሳኔ ጸና ።

' እሁን ' አለ ወንድይራድ ፣ በድንገት የቀኝ ኋሊት ዞሮ ፣ ወደ ቤቱ መመለሻውን አግጣጫ ይዞ ፣ ' አንድ ልበ ድፍን ፣ ቆዳ ደንዳና ፣ በውስ የሚተራመሰውን ሐሳብ ቢሰማ ፣ ከስለት ይበልጥ አንጀት የሚቆርጥ ሣቁን ይለቅብኛል . . . አንዱ ባንዱ ሲሥቅ ጀንበር ጥልቅ ! - . . . . . . .

* * *

ከበደና ብርቄ እማድ ቤት ናቸው ። ብርቄ ቡና ቆልታ ትወቅጣለች ። ጀበናው ተጥዶ ፣ ውሃው ይፈላል ። " ጨርሶ ከልቤ አልወጣ አለ " አላት ከበደ ።

" ምኑ ? - የስኒው ነገር ? " ስትል ጠየቀችው ብርቄ ።

"እእ!"

" እኔ አልነገርኩህም ? አንተ የሰው ነገር አትሰማም እንጂ !" አለች ብርቄ ፣ ድል አድራጊነት እየተሰማት ፣ " እያሳስትም ሰልህ። ስኒው የሚለው አንዱ መሬት ጠብ አይልም ። "

" ይገርማል እኮ ! "

" ብቻ ፣ እንደዚህ ቶሎ መድረሱ ደግሞ አያስገርምም ? "

" እሱን እኮ ነው የምልሽ ። "

" ጋሼ ተሰማ ግን በጣም አሳዘኑኝ . . . ብቻ ፣ እበዙት እኮ ፣ ስንት ቀን ተመከረው አይሰሙም " እያለች ፣ ቡናውን ወቅጣ ጨረሰች ። እጀበናው ጨመረችውና ዕጣን ፍሊጋ ተነሣች ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ምን ይሻለኛል እንቺ እያለሽ ። በሽታዬ እንቺ . . . " አለ ተሰማ ፣ ቆጣ ብሎ ።

" ምን አጠፋሁ እኔ ? " አለች ብርቄ ፣ ደንገጥ ብላ ።

" ምን አደረግሁ ! ' መንገድ ይልሃል ' እያልሽ ስታሟርች ብኝ አልከረምሽም ? " አላት በንዴት እየጋለ ። ራስ ምታቱም በተጨማሪ ያበሳጨዋል ።

" ሰኒው ያለውን እንበብክ እንጂ ሌላ ምን አልኩ ? "

" ምናባትሽ ታንቢያለሽ ፣ ታሟርቻለሽ እንጂ ! ! "

" በንጉሥ አይስደቡኝ ! በሕግ አምላክ ! . . . . . . . . "

በዚህ ጊዜ ፣ በተሰማና በብርቄ መካከል ቆመና ፣ " ይተዉ እባክዎ ፣ ጋሼ ተሰማ ። እቢ ምን ታውቃለች ብለው ነው ? " አለ ከበደ ።

" ማወቋ መቸ ነው፣ ማሟረቷ ነው እንጂ . . . ሰውየው ፣ ' በእልሜ ጭራ ይገፍ ዝንብ እሽ ስል አደርኩ' ቢለው ፣ እልም - ፈቺው 'ልትቆመጥ ነው' ብሎ አሟርቶበት አልተቆመጠም እንዴ ! ! ታዲያ ሰውየው ምን ሆንክ ቢሉት ' እልም - ፈቺ ቆመጠኝ ' አለ ይባላል ። አሁንም ፣ ይቺ ፣ ' መንገድ ይልሃል ፣ መንገድ ይልሃል ' እያለች ስታሟርት ብኝ ፣ ይኸው ከደኅና ሥራዬ ወጣሁ — መንገድ ይበልሽ የጐዶቲዉ ገብሬል ! ! "

" እኔ ጠጅ ተጋቱ ብዬዎታለሁ እንዴ ታዲያ ! " አለች ብርቄ፣ ከበደ መካከላቸው መቆሙ ድፍረት ሰጣትና ። " አሁንስ አበዙት ! ምነው እቴ ፣ ኤድጭ ! "

" በሽታ ይጋትሽና ደሞ እንዴት ትናገራለች ! " አለና ተሰማ፣ ከበደን ሳያስበው ገፍትሮት በልፎ ፣ አከታትሎ በጥፊ አንድ ሁለት ጊዜ አጮላት ። ብርቄም ሳታስበው ነበርና የሆነው ፣ የመጀመሪያዉ ጥፊ ሲያርፍባት በርግጋ ወደ ኋላ እንደ ተለጠጠች ፣ ሁለተኛዉ ስላገኛት ፣ ሚዛኗን አሳጥቶ ፣ ከነበርጩማዋ በጀርባዋ ወለሉ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ኢጋኸ ሕግ አለ ። አንተም ብትሆን አይተሃል ፤ ለማተብህ ስትል እውነቱን ትመሰክራለህ ። ”

“ ይልቅስ እራስሽ እንዴት ነው ? ተጐድተሻል ? ” አላት ፤ የነገሩን አቅጣጫ ለውጦ ።

“ ምን ተርፌያለሁ ! ”

“ እስቲ ልይልሽ ? ”

ነጭ ሻሽዋን ፈታች ። ራስዋን በብርሃኑ በኩል አድርጋለት ፤ ከኋላ ተመለከተው ። ጠጉሯ አጭር ስለሆነ ፤ በጣቷ ያመለከተች በትን ቦታ ገላልጦ ለማየት አላወከውም ። ትንሽ ቁስል ናት ። ደሟም ቆሟል ። ከበደን በጣም ያስደነቀው ፤ ነጭ ሻሽዋን ለማሰር ስትል ከመቸው ራስዋን ታጥባው እንደ ነበረ ነው ። እንዳልተጐዳች ካረጋገጠ በኋላ ትከሻዋን ያዝ አድርጐ ፤ “ በይ ዐርፈሽ ተቀመጭ ፤ ደኅና ነሽ ” አላት ።

“ ምን ደኅና ነኝ ፤ ቁስሉን አያየኸው ? ”

“ ፖሊስ ይኽን ቢያይ ‘ አትቀልጅ ’ ነው የሚልሽ ። እኔም ፖሊስ ብሆን የምለው ይኽንኑ ነው ” እያለ ትከሻዋን እየዳሰሰ ያግባባት ጀመር ። ያ ሁሉ ጩኸትና ድንፋታ ሰከነ ። ከበደ ይኸኛው እንደ ተሳካለት ከተገነዘበ በኋላ ፤ “ በይ እንግዲህ ይኽንን ጠጡኝ እያለ የሚለምነንን ቡና እኔ ከእልፍኝ ስኒ አምጥቼ በኋላ እንጠጣዋለን ” አላት ።

ትዝ አላት የቡናው ነገር ። ለካስ ቡናው ተረስቶ ኖሯል ! ዕጣኑ ጨሶ አልቋል ። ቡናውም ከትሞ ቀዝቅዞአል ። ምድረ ስኒ ግን ደቅ ቋል ።

“ የዚህ የጥቁር ቡና አምላክ ይይላቸው ! እኝህ ከፉ ሰው ” አለች ብርቄ ፤ እንደገና ነገር ለመጀመር ።

“ በይ በኔ ይሁንብሽ ። ሁሉንም ተዪው ” አለና ከበደ ፤ ወደ ርሱ ሳብ አርጐ ጉንጯን ሳም አደረጋት ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" እንደሳቸው ቢሆን ግን — " ስትል አቋርጦ ፤ " እንደዚህ ነው እንጂ ! ጐሽ የኔ ሸጋ " አላትና ወጣ ። እውጭ ላይን ይዞአል ። ተሰማን እጐጆው አጠገብ ተክዞ አገኘው ። ያስፕሪኑ ነገር ትዝ አለ ውና ፤ ተመልሶ ካንድ ብርጭቆ ውሃ ጋር ይዞለት ሔደ ።

" ታዲያስ ? " አለው ከበደ ።

" ምን ታዲያስ አለው ? "

" ምን አሰቡ ? " አለው ፤ አስፕሪኑንና ውሃውን እየሰጠው ።

" ምን አስባለሁ ? " አለ ተሰማ ፤ እየተቀበለ ።

" እንዴ ! ይቅርታ ይለምኗ ። እንዲያው ዝም ይላሉ ? . . . ይልቅ ቶሎ ይግቡና ፤ ' የዛሬን ይማሩኝ ' በሏቸው ። "

" ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ አሳልፈውልኛል ። አሁንስ በጄ አይ ሉኝም ። አፈን በከንቱ አላጠፋም ። እኔ እህል ውሃዬ ከዚህ ቤት ያለቀው ያቺ ክይሲ የተቀጠረችለት ነው ። እኔ ጥቁር ሰው ኩኮቤ አደለም ። ገፊዬ እንደ ሆነች ገና ስትመጣ ዐውቄዋለሁ ! " አለ ፤ የመ ማበት አበሳ የማይታሰፍ መሆኑን በማመን ።

" እባክዎ ይሒዱና እጫማቸው ላይ ወድቀው ይለምኗቸው ፤ አይጨክኑብዎትም ። "

" ተወኝ እባክህ ፤ አይሆንም ። አሁንስ አንዳቸውም እሺ አይ ሉኝ ። ከንቱ ነው ። እኔ ዱሮውኑ ዐውቄዋለሁ ፤ እህል ውሃዬ አል ቆአል ። "

" ይልቅ ፤ ' ሒደው ከእንግዲህ ወዲህ አይለምደኝም ፤ የዛሬን ' ይተውኝ ይበሏቸው ። "

" ውሸት አታናግረኝ ፤ ' ጠጅ እተዋለሁ ' ብዬ አልናገርም ። ብፈ ልግም አልችልም እንጂ ! "

" ምን ያረግልዎታል ? ከሥራዎ ፤ ከጤንነትዎ ይበልጣል ጠጅ ? "


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ይኽ የሆነው ወንድይራድ ሳያስበው ድንገት ስለ ነበረ ፣ ለጊዜው የሚያስበውና የሚለው ተሳነው ። ብቻ ፣ በዘልማድ እግሩን ለማሸሽ ሞከረ ። ነገር ግን ተሰማ ጥርቅም አርጎ ይዞታል ።

“ ምን መሆንህ ነው ? ”

“ ይማሩኝ ፣ ጥፋተኛ ነኝ ” አለ ተሰማ አሁንም ።

“ እንዴ ጡር ልታደርግብኝ ነው ፣ እግሬ ላይ የምትወድቀው ? ተነሣ ባክህ — በል እኮ ልቀቀኝ ! — በል እሺ ! ”

“ ይቅር — ”

“ እሺ አልኩህ እኮ ! እሺ ! እሺ ! ” ብሎ ወንድይራድ ወተወተ ። የሽማግሌዉ እግሩ ላይ መውደቅ መንፈሱን አሸበረው ።

ተሰማ ፈጽሞ አይሆንም ብሎ ያመነው ነገር እንዲህ ባንዴ በመሆኑ በጣም ደስ አለው ። “ ዋጋዎን በሰማይ ያገኙታል ። እኔማ በምን ዐቅሜ መክፈል እችላለሁ ” አለ ከወደቀበት እየተነሣ ።

“ ትችላለህ ” አለው ወንድይራድ ።

“ እዬ ! እንዴታባቴ አርጌ ። ብችልማ ምናባቴ ቀርጦኝ ። ብቻ አልችልም እንጂ ። የኖንተን ውለታ ሊከፍልልኝ የሚችል አንድዬ ብቻ ነው ። ”

“ አንተው ትችላለህ — ይኸን መጠጥህን በመተው ! ”

ተሰማ አጥቱ ፈሰሰ ። ተስፋው እንደገና መነመነ ። ውለታዬን ለመክፈል መጠጥህን አቁም ያለውን ዱብ ዕዳ መመለስ አለበት ። ስለዚህ ጥቂት ጸጥ ካለ በኋላ ፣ በትካዜ ዝግ ብሎ “ እዬ ጌታዬ እሱንስ — ” ብሎ ሳይጨርስ ፣ እበሩ ጥግ እውጭ ሆኖ ያዳምጥ የነበረው ከበደ ፣ ተሰማ ‘ ይኸን ማድረግስ አልችልም ’ ብሎ ነገር ሊያበላሽ ነው ብሎ ፣ በሩን እንኳኩቶ ዘው አለ ።

“ ምንድር ነው ? ” አለው ወንድይራድ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ግን ፣ ስሜቱን እልቡ ውስጥ አርቆ ቀብሮ ፣ ሌላ ወሬ ሲያወራላት ባጀ ። ይኸን ያደረገበትን ምክንያት አሁን እያስታወሰ ፣ ‘ ምክንያቱም እጅግ ደፍሬ ላንዲት ደቂቃ ፣ ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ ያሰብኩ ጊዜ ፣ ያገኘሁት መልስ ርኅራኄ ስላልነበረው ነው ። ነገሩን ያኔ ስመለከተው ፣ ባጭሩ እንደሚከተለው ሆኖ ታየኝ ። ልጅቱ እራሟ እሳት ወይም የላትም ። ካላት ነገሩ ባጭሩ ተቆረጠ ። ከሌላት እስዋን የመሰለች ወጣት አዲስ አበባ የታጀበው ተኩላ ገና እኔ ትምህርቴን ፈጽሜ ወደ አገሬ ከመመለሴ በፊት ይናጠቃታል ። ስለዚህ ፣ እፌን ከማጠፋ በሰላም ተሰነባብተን ነገሩን እንደሚጣፍጥ ሕልም መቁጠር ይሻላል ብዬ ነገሩ በዚሁ አቆመ ’ አለ እጐናፍር ፣ በሐሳቡ ።

ሆኖም ፣ አሁን ፈልጐ ያለችበትን ሁናቴ ማወቅ ፈለገ ። ‘ መቼ ነው ውጭ አገር ተመልሳ የሔደችው ? አሁን እንዴት ትሆን ? ሌጣ ናት ወይስ አግብታለች ? . . . . ’



@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አራት

### “ ሐሙስ የቀን ቀዱስ ”

በመሥሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያሉት ሠራተኞች ፥ ምስት ዘበኞች ፥ ሁለት አትክልተኞችና አንዳንድ የቢሮ ጽዳት ሠራተኞች ናቸው ። እጅና እግር የሚቈርጠው የሌሊት ብርድ ፥ ለፀሐይዋ ሙቀት ሥፍራ እየለቀቀ ገለል በማለት ላይ ይሁን እንጂ ፥ ጨርሶ አልሔደም ። ስለዚህ ዘበኞቹ አሁንም ገና ከሌሊቱ ሙሉ ትጥቃቸው ጋር ናቸው ። ወፋፍራም ነጠላዎቻቸው ሥር ሙሉ የቀን ልብስ እንደ ለበሱ ናቸው ። አንዱ የሹራ መጫሚያ ፥ ሁለቱ የባስቲክ ቡት መጫሚያዎች አድርገዋል ። የቀሩት ደግሞ ከሞቃት ቤቶቻቸው የመጡት ጠዋት ስለሆነ ፥ ብርዱን በሙሉ ትጥቅ እንደሚጋፈጡት ጠላት ባይቈጥሩትም ፥ እነሱም በቀን ልብሳቸው ላይ ነጠላ ደረብ ማድረጋቸው አልቀረም ።

የቢሮ ሠራተኞቹ መምጫ ሰዓት ገና ስለሆነ ፥ ሰዎቹ ተሰብስበው ፀሐይ እየሞቁ ያወጋሉ ። ሽምግል ያሉት ዘበኛ ፥ ተረካቢዎቹ የቀን ዘበኞች ስላልመጡላቸው ይነጫነጫሉ ፤ ይበሳጫሉ ። ባለቤታቸው ታመዋል ። ወረፋ ሳይበዛ በጠዋት ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ወስደው ለማሳካም አቅደው ነበር ።

ሽማግሌዉ መቁነጥነጣቸውን አይቶ እንደኛዉ አትክልተኛ ፥ “ ለምን እርስዎ ወደ ቤት አይሔዱም ? እነሱ ሁለቱ ያስረክቡ ” አላቸው ።

“ አላስረከበኝም እሱ ብሎ ይከሰኛል — አስተዳዳሪው ላይ . . . ከንፉ እንኳን ይህን ያህል ምክንያት አግኝቶ ትንሽ ነገር ነው የሚፈልገው ” አሉ ሽማግሌዉ ዘበኛ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ታዲያ ቢከስዎስ ? ‘ እሱ በጊዜ አልመጣም ’ አይሉም እንዴ ፣ እርስዎ ? ” አለ ሁለተኛው አትክልተኛ ።

“ ጊዜውስ ገና ነው ። ከዚህ ቀደም ተካሰን ፣ አስተዳዳሪዉ የቀን ዘበኛ በሁለት ተኩል ይግባ ብለው በይነዋል ” አሉ ሽማግሌው ።

“ ታዲያ ይኸ ትክክል ፍርድ ነው እንዴ ? እርስዎ ማታ ከዐሥራ ሁለት ጀምረው ፣ ሌሊቱን ሁሉ በብርድ ተኮራምተው አድረው ፣ ደሞ ጠዋት እንደገና እስከ ሁለት ተኩል ? ” አለ የመጀመሪያው አትክልተኛ ።

“ እሱስ ለኔም ጊዜ ያው ነው ። ተራዬ ሲደርስ በሁለት ተኩል ነው የምገባው ። ብቻ ትላንት ማታ ፣ ‘ እባክህ በአንድ ሰዓት ተረከበኝ ። ሚስቴን አሟታልና አኪም ጋ እወስዳታለሁ ’ ብዬው እሺ ብሎኝ ነበር ። ታዲያ ይኸው እስካሁን አልመጣም ” አሉ ፣ እየተቁነጠነጡ ።

“ ምናልባት አንድ ነገር አግኝቶት እንዳይሆን ? ” አለ ባለ ሸራ መጫሚያው ዘበኛ ።

“ ምን ያገኘዋል ። እንዲያው ረስቶት ይሆናል እንጂ ! ” አሉ ሽማግሌው ዘበኛ ፣ ተክዘ እያሉ ።

“ ምን ይታወቃል ? ወይ ጐረቤት ሰው ሞቶ ይሆናል — ስንት ነገር አለ ! ” አለ ሁለተኛው አትክልተኛ ።

“ ምንም ሆነ ምን ፣ እኔን ምንም አልበጀኝ ” ሲሉ ሽማግሌው ፣ አንድ አምስት የሚሆኑ ሰዎች አጥር ግቢው ገብተው እያ ወሩ ቀስ ብለው ወደ ዘበኞቹ ዘንድ ያዘግማሉ ። ሽማግሌው ዞር ብለው እንደ ዘበት ባይናቸው ቃኙዋቸው ። ከመካከላቸው አንድም የቀን ዘበኛ የለም ። ሁሉም የጽዳት ሠራተኞችና አንዳንድ ተላላኪዎች ናቸው ። ሽማግሌዉ ከሰዎቹ መካከል አንደኛዉን መለየት አቃታቸው ። ዐይናቸው በመድከሙ መስኢቸው ፣ ቀረብ ሲል ለመለየት ፣ ዐይናቸውን ከላዩ ሳይነቅሉ ይመለከቱት ጀመር ። ነገር ግን ፣


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

የአገሎናፍርን ደረጃና ማዕረግ ለመረዳት ፣ የሱን ዋና መሥሪያ ቤትና እንዲሁም የሌሎቹንም አቋምና አከፋፈል መመልከት ይጠቅማል ። በየመሥሪያ ቤቱ የፕሮቶኮሉ አኪያሔድ እንደሚከተለው ነው ።

አንደኛ ፡ ጠቅላይ ሹም
ሁለተኛ ፡ ጠቅላይ-ሹም-አከል
ሦስተኛ ፡ ምክትል ጠቅላይ ሹም
አራተኛ ፡ ረዳት ጠቅላይ ሹም
አምስተኛ ፡ ዋና ሹም
ስድስተኛ ፡ ምክትል ዋና ሹም
ሰባተኛ ፡ ረዳት ዋና ሹም
ስምንተኛ ፡ ሹም
ዘጠነኛ ፡ ምክትል ሹም
ዐሥረኛ ፡ ረዳት ሹም
ዐሥራ አንደኛ ፡ ኃላፊ
ዐሥራ ሁለተኛ ፡ ምክትል ኃላፊ
ዐሥራ ሦስተኛ ፡ ረዳት ኃላፊ

በየመሥሪያ ቤቱ ካንድ ጠቅላይ ሹም በላይ አይኖርም ፤ ከዚህ በታች ማዕረግ ያላቸው ግን ሁለትም ሦስትም ሊኖሩ ይችላሉ ። እንዲያውም ፡ ደረጃዉና ማዕረጉ ዝቅ እያለ ሲወርድ ፣ የሹሙም ቁጥር ይበዛል ። ስለዚህ ፣ እንዲጋጣሚ ሆኖ አንድ ሆኑ እንጂ ፣ በአጐናፍር መሥሪያ ቤትም ሁለት ወይም ሦስት ጠቅላይ-ሹም አከሎች ሊኖሩ ይችሉ ነበር ። ምክትል ጠቅላይ ሹማምንት ግን አንድ አምስት ያህል አሉ ።

አገሎናፍር የዘኮፍሉ ረዳት ዋና ሹም ነው ። ከበታቹ አንድ ዐሥር ሰዎች ከበላዩ ምክትል ዋና ሹሙና ዋና ሹሙ አሉ ። ስለዚህ በማዕረግና በሥልጣን በከፍሉ ሦስተኛ መሆኑ ነው ። ይችን ማዕረግና ደረጃ ያገኘው መሥሪያ ቤቱ በገባ ባጭር ጊዜ ውስጥ ስለሆነ ፣ ባንድ ካንድ የሥራ ባልደረቦቹ ላይ ፣ የቅናትና የምቀኝነት መንፈስ ማሳ



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

መጻሕፍት ናቸው የሚላቸውን እያነሣ ቀጋ ቅናሽ እያደረገ ግዛኝ ብሎ ወጥሮ ያዘው ።

" ወዳጄ ፤ እኔ የምፈልገው መጽሐፍ የለህም " አለው አጐናፍር ፤ በመታከት ።

" ምንድነው እርስዎ የሚፈልጉት ፤ ጌታዬ ? "

" 'ጦቢያን' ነው የምፈልገው ወይም 'ልብ ወለድ ታሪክ' የሚባለውን ፤ በአፈወርቅ ገብረየሱስ የተጻፈውን ። "

" እሱስ የለኝም " ካለ በኋላ ፤ " የእንግሊዝኛ ጥሩ ጥሩ አለኝ " እለና ልጁ እንደገና እያነሣ ማሳየቱን ቀጠለ ።

" አይቼዋለሁ ። ብቻ እኔ እሱን አልፈልግም " አለው አጐናፍር ፤ ቁርጥ ባለ አነጋገር ።

" ያማርኛም ፤ ይኸ በጣም ጥሩ ነው ። ሰው ሁሉ ሰሞኑን የሚገዛው ይኸን ነው " አለ ልጁ ፤ ትስፋ ባለመቁረጥ ።

" አንብቤዋለሁ " አለው አጐናፍር ፤ በዝግታ ።

" ይችንስ ? — እችም በጣም ጥሩ ነች " አለ ልጁ ፤ ቶሎ ያን መልሶ ሌላ ደግሞ እንሥቶ — በማይሞት ተስፋ ።

በዚህን ጊዜ የቡና ቤቱ ልጅ ማኪያቶውን ይዞ መጥቶ ነበርና ፤ የያዘውን ላጐናፍር እየሰጠ ፤ " አንተ ! ምን ደንበኞቻችን ታስቸግራለህ ፤ አትሔድም !? " አለው ።

መጽሐፍ ሺያጩም ዞር ብሎ በንቀት እየተመለከተው ፤ " ዝም ብለህ ቡናህን አታሳልፍም ? አንተን ማን ጠራህ ? ምን ታጐበጉባለህ ? እኔ እሳቸው አሳየኝ ብለውኝ ነው " አለው ፤ ፍጹም ዋሽቶ ።

" እንዳንተ እየዞሩ ሰው ከማስቸገር የኔ ቡና ማሳለፍ አይሻልም ? የኔ ሥራ ከአንተ ሱቅ በደረቴነት ያነሰ ሥራ ነው ? በል ሒድ አሁን !! "


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ በተማሩት መካከል ይኸ ሊገጥማት አይችልም ” አለ አጐናፍር ፡ ከክርክሩ ጥልቀት መውጫ መንገድ እያሰላሰለ ። የቀረውን አጭር ጊዜ በክርክር ለማሳለፍ አልፈለገም ።

“ ‘ ተማረ ’ በሚባለው ወጣት ይብሳል እንጂ ። ሌሎቹንስ ምና ልባት ልንፈርድባቸው አይገባም ይሆናል ። የሚመሩት በዚያው በሚያውቁት በለመዱት ስለሆነ ። እኔ የምፈርደው ተምሬአለሁ ፡ ዐውቂያለሁ በሚለው ወገን ነው ። ”

“ ታውቂያለኽ ፡ እንደኛ ትውልድ ስድብና ወቀሳ የበዛበት ሌላ የነበረ ወይም ያለ አይመስለኝም ። የዱሮዎቹ ፡ ‘ የዘመኑ ልጆች ብላሾች ናቸው ’ ይሉናል ። እኛ ራሳችን ‘ አንረባም ’ እን ላለን ። በውነት ይኸ ሁሉ ሊደርስብን ይገባል ? ወንዶች ብቻ ማለቴ አይደለም ፡ ሴቶቹንም ነው ” አለ አጐናፍር ፡ አርእስቱ ነገሩን ቀይሮ ።

ልጅቱ ክርክር ውስጥ ሰጥማ ፡ ስለ አጐናፍር ለማወቅ ያቀደች ውን ረስታው ነበር ፤ አሁን ግን የወሬዉን አግጣጫ ሲለውጥ መቆ ጠሉን ትታ ፡ ወደ መጀመሪያዉ ዓላማዋ የምትደርስበትን ዘዴ ማሰ ላሰል ጀመረች ። እስካሁንም ስትከራከር ልብ ሳትል ራስዋን ያጋለ ጠች መሰላት ።

አጐናፍር ዝምታዋን ተገንዝቦ ፡ ክርክሩን ዘዴ በጐደለው አኳኋን ማቆሙን አመነ ። ስለዚህ ፡ የጀመረውን ተወና ወደ ምግቡ ዞረ ። ለካ ምግቡ ተረስቶ ኅይበላ ቀዝቅዞአል ። “ በችጋር ገደልኩሽ አይደለም እንዴ ? ” አለና አሳላፊ መጥሪያ ደወሉን እያከታተለ ደወለ ።

አሳላፊው እየሮጠ መጣ ። ምግባቸው እንዳልተነካ ተመል ክቶ ፡ “ አልተስማማዎትም ? ” አለ በትሕትና ፡ ፊቱ ላይ ግን ሥጋት እየታየ ።

“ የለም ፡ ምግቡ ምንም አልጐደለው ። ብቻ ፡ ቀዘቀዘብን ሳንበላው ። ሌላ ብታመጣልን ? ” አለው አጐናፍር ። ልጁ ትንሽ አመነታ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ግድ የለም ። የዚህን እኮ እከፍላለሁ " ሲለው ፣ እሳላፈው ይዞ እየሮጠ ሔደ ።

" ችጋር እለቅን አይደለም እንዴ ! " አለ አጐናፍር ፣ ልጁ ይዞ እንደ ሔደ ።

" እኔ ነኝ — "

" የለም ፣ እኔ ነኝ ፣ ክርክሩን ስከታተል የምሳውን ነገር ያስረ ሳሁሽ " አለ አጐናፍር ። ከዚያ ዝምታ ተከተለ ።

" አውሮፓ ለብዙ ዘመን ተቀምጦ ለመጣ ሰው አዲስ አበባ ችን እንዴት ነው ? " አለችው ፣ አዲስ አርእስት እንሥታ ።

" አባክሽ የኔ ኑሮ ምንም እዚህ ከተራ ኑሮ የሚለይ ነገር የለበትም ። ' ይመሻል ይነጋል ፤ እንዲህ እንዲህ ሲሉ ፣ ጊዜ ሞት ይደ ርሳል ' ነው የኔ ኑሮ ። "

" ምነው ! ምነው ! ከተማችንን እንዲህ የሚሰለች ከተማ አስ መሰልከው ? ለወንዶች በጣም የሚመች ከተማ ነው ፤ መጥፎም ቢሆን ለሴት ነው እንጂ ! እንዲያውም አንዳንድ የውጭ ታዛቢዎች ፣ ' የወ ንዶች ዓለም ' ብለው ሠይመዋት በስሟም አይጠሯት " አለች ፣ ለማወቅ ወደ ፈለገችው ጉዳይ አግጣሚ ነገሯን እያመራች ።

"እኔ እንኳ በተለይ በዚህ አግጣሚ አልሔድኩም ነበር ። ቢሆንም ፣ አንቺ ባልሺው እንጻርም ከሔድን ፣ ለወንድ የሚመች ከሆነ ፣ ለሴትም ይመቻል ። ለሴት ካልተመቸ ለወንድም አይመችም ማለት ነው ። "

" ይኸ የሚያስኬድ እንኳ አይመስለኝም ። ይሁንና ፣ ባጭሩ በዚህ ረገድም ቢሆን እኮ መሪው ወንድ ነው ። "

" እሱ ዱሮ ቀረ ። አሁን ወንዱ ሴቱ ሆኗል ። የከተማ ሴቶቻ ችን ዐይናውጣ ሆነዋል " አለ ፣ በፈገግታ ።

" ታዲያ ሥራህን እንደዚህ ሲያቃልሉልህ ምን ያስከፋሃል ! ደስ ሊልህ ይገባል እንጂ ! " አለችው በምጸት ፤ ግን እንደ ርሱው

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያ ጸጥ ብለው ምሳቸውን ጨረሱ ፡ አሳላፊው ተጠርቶ ሲመጣ አጕናፍር ጠየቀው ። ልጁ መጀመሪያ ሳይበላ ቀዝቅዞ የተ መለሰውን ምግብ ዋጋ ሳይደምር ፤ የተበላውን ምግብ ዋጋ ብቻ አስበ ነገረው ። አጕናፍር ፤ ላሳላፊው ጠቀም ያለ ጉርሻ ሰጥቶት ተነሥ ተው ወጡ

እመኪናው ውስጥ ሆነው አንዳንዴ ብቻ ሲነጋገሩ ፤ አብዛ ኛውን ጊዜ ግን ፤ ከየግል ሐሳባቸው ጋር እየተጫዋወቱ ወደ መሥ ሪያ ቤቷ አቀለቀሉ ። ምንም እንኳ የሥራ ሰዓቱ ቢያልፍም ፤ አጕ ናፍር ለመጀንኛ የማትመቸውን ፎክስዋገኑን የሚነዳ ዝግ አድርጐ ነው ። እመሥሪያ ቤቷ አጥር ግቢ ሲደርሱ ፤ ወጣቷን ለቅዳሜ ቀጠሮ ጠየቃት ።

" ቅዳሜ አይመቸኝም ። ቀጠሮ አለብኝ ። "

" ታዲያ መቼ እንገናኝ ? "

" ከቅዳሜ ሌላ ነጻ ነኝ ። "

" ዛሬ ከሥራ በኋላ ለምን አንገናኝም ? "

" ከአንዲት ጓደኛዬ ጋር ቀጠሮ አለኝ ። "

" እሷ ደግሞ ሁልጊዜ ነው እንዴ ! የቅዳሜ ከሰዓት በኋላው አይበቃትም ? " አለ ቅዳሜ ከማን ጋር እንደ ተቃጠረች ለማወጣ ጣት ።

" አይ ቅዳሜ ከሷ ጋር አይደለም የተቃጠርኩት ፡ ከሌላ ሰው ጋር ነው " ብላ መንገዱን ዘጋችበት ።

ከማን ጋር ብሎ መጠየቅ ነበር ስለ መሰለውና ' አጥብቆ ጠያቂ የእናቱን ሞት ይረዳል ' እንደሚባለው ፤ የማይሆን ነገር ምናልባት እንዳይሰማ በመፍራትም ፤ አጕናፍር ነገሩን እዚሁ ላይ ተወው ።

ልጅቱ ለማውጣጣት መሞከሩ ገብቷታል ። በሙከራው ተደ ሰተች ። ግን ፤ በለጠ ከሚባል ወጣት ጋር መቃጠሯን ለመግለጽ እንዴት ትችላለች ?


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰማ ጥያቄዉን ሲጠብቅ፥ "ለምንድር ነው የምትጠጣው?" የሚል ቦምብ ወንድይራድ ጣለበት።

" ኧረ እኔ ከነጋ ምንም አልቀመስኩ ዛሬ ።"

" የለም ፤ ዛሬ ማለቴ አይደለም ። ኧረ ፤ እንዲያው በሌላው ጊዜ ?" ተሰማ እራሱን እያከከ ዝም አለ ።

" በል እኮ ንገረኝ ። ችግር አለብህ ? "

" ከድኻ ችግር መች ይጠፋል ። "

" ለዚህ ነዋ የምትጠጣው ? "

ተሰማ አልገባውም ። አንገቱን አቀርቅሮ እንደገና ራሱን አከክ አከክ ማድረግ ጀመረ ።

" ነው ? "

" ምኑ ፤ ጌታዬ ? "

" በል ተወው ፤ የተግባባን አልመሰለኝም " አለ ወንድይራድ ።

ተሰማ በልቡ ፤ ' ምንድን ነው የሚሉት እኝህ ሰውዬ ? ችግርንና ጠጅ መጠጣትን ምን አገናኛቸው ? ሰው የሚጠጣው ከወዳጅ ከዘመድ ጋር ሆኖ ሳለም ለደስታ ነው ። ለችግር ? ሀብታም ጠጅ የሚጠጣው ምን ተቸግሮ ነው ? የለም ፤ አግርኛቸው አልገባኝም ' እያለ መንገዱን ወደ ጉጀው አዘቀዘቀ ።

ተሰማ ወደ ዘበኛ ቤቷ ሲንቆረቆር ወንድይራድ እያስተዋለው ፤ ' ለተሰማ ጠጅ መጠጣት ልማድ ነው ፤ ዓላማ የለውም ። . . . " ችግር ከደሃ መቼ ይጠፋል " አለ ። በምሬት አይደለም ያለው ። ያለውን ፤ የኖረውን ፤ የሚኖረውን ሕይወት እውነታ ለመግለጽ ነው እንዲህ ያለው ። ችግር ሲልም የሀብት እጦትንና ፤ ማጣት የሚያስከትለውን ጣጣ ማለቱ ነው እንጂ፣ እኔ ችግር የምለውን ዐይነት — ማለት ፤ በውስኪና በኮኛክ ለማስጠም የሚሞክሩትን ዐይነት ችግር—



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህን ጊዜ ወንድይራድ የባሰውን ሠጋ፣ ስለ ኸማግሌው ነገር ። “ ምነው ፣ ምን አዲስ ነገር መጣ ? ” ሲል ከበደ ኮኛኩን አመጣ ፡ “ ለኔም ጨምርልኝ ” አለው ወንድይራድ ።

አበራ ኮኛኩን ጠቀም አድርጐ ከተጐነጨ በኋላ ብርጭቆ ውን አስቀመጠው ። ፊቱን በሁለት እጆቹ ሦስት አራቴ ሞዠቆ ፣ ዝም አለ ። ወንድይራድ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ እንደ ለቀቀ ዛሬ ጠዋት አበራ ሰምቷል ። ወንድይራድ እስካሁን ለምን እንዳልተናገረ ገርሞታል ፤ በተለይ ደግሞ ለርሱ ለምን እንዳልነገረው ። ምክንያቱም ፣ ወንድይራድ ከሁለቱ ጓደኞቻቸው ይበልጥ ‘ እኔን ያቀርበኛል ፣ ይቀርበኛል ’ ብሎ አበራ ያምናልና ። ይሁን እንጂ ፣ አበራ አሁን ልቡ የሚሸበረው ስለዚህ ጉዳይ አልነበረም ።

“ ምነው ? ዝም አልክሳ ? ”

“ እባክህ ዛሬ እንደበት የሚያሲዝ ነገር ገጠመኝ ” አለና አበራ ነገሩን ዝግ ብሎ ጀመረ ። ወንድይራድም በጥያቄ አላቋረጠውም ።

“ ምሳዬን ከደብራቱ ጋር ምንቃምር ይፋት ነበር የበላሁት ። እዚያ እነማንን አየን ይመስልሃል ? አጐናፍርንና ቃፈረችን ! ! ”

‘ ማንች ቃፈረች ? ’ ብሎ ወንድይራድ ሲጠይቅ ከቆጣ በኋላ ፣ በለጠ የመኪና አደጋ የደረሰበት፣ የአንዲት ወጣት ቀጠሮ ለማክበር ሲጣደፍ መሆኑ ትዝ አለው ። እስካሁን ስሟ ቃፈረች መሆኑን አያውቅም ነበር ። “ አዲሷ የበለጠ እንትን መሆኗ ነው ? ” አለ ወንድይራድ ፣ ለማረጋገጥ ።

“ አዎ ። ”

“ ካደጋው ወዲህ አላገኛትም ነበር ? ”

“ ኸረ ለፊታችን ቅዳሜ ተቀጣጥረናልና መኪናህን እንድትሰጠኝ ብሎኛል ! ”

“ ምናልባት አንዳንተና እንደ ደብራቱ ስምምነት አድርገው እንደሆን ? ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ምነው በግርህ ፤ መኪናህ ተበላሸች እንዴ ? " አለው ባለ መኪናዉ ወጣት ፤ በወንድይራድ ደረጃ ያለ ሰው መኪና እንዲኖረው ግዴታ እንደሆነ ሁሉ ።

" የለኝም ፤ ለሽርሽር በግሬ ወደዚያ ዐልፌ መመለሴ ነው ። "

" ልውሰድሃ ፤ ግባ ። "

" እግዜር ይስጥልኝ ። . . . ይገርምሃል ዛሬ እሰወትሮው በግር መራመዱ አደከመኝ " አለ ወንድይራድ ። ቀጥሎም ፤ " እዚህ አስ ተማሪ ነህ እንዴ ? " ሲል ጠየቀው ወጣቱን ።

" የለም ፤ እንደ ዲሬክተር ቢጤ ነኝ " አለ ፤ ፈገግ ብሎ ።

" ይቅርታ ፤ አላወቅሁም ። "

" ምን ይቅርታ መጠየቅ ያስፈልገዋል ፤ ስንት ዓመታችን ሳንገናኝ " አለ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ።

" አዎ ፤ ጊዜውስ ብዙ ሆነው ፤ ዐሥር ዓመት አይሆነውም ? "

" ኧረ ይበልጣል ። "

" እዚህ ከተዛወርክ ስንት ጊዜ ሆነህ ? "

" ሁለተኛ ዓመቴን ይዣለሁ ፤ ግን ዐሥር ዓመት የሆነኝ ይመ ስለኛል ። ከተማሪ ጋር መዳረቁ ልብ ያቆስላል ። "

" እኛም ተማሪዎች የነበርን ጊዜ ይሄኔ የኛም አስተማሪዎችና ዲሬክተሮች እንደዚሁ አማረውብን ይሆናል ። "

" በበኩሌ ይኸው የተበደርኩትን እከፍላለሁ ። ግን እባክህ እኛ እንደዚህ አናስቸግርም ነበር ። አይመስለኝም ። "

" ዘወትር ይኸው ነው እባክህ ። ሁልጊዜ ያለፈው ወይም የሚ መጣው አሁን ካለው የሚሻል ፤ የሚልቅ መስሎ ይታያል ። ሆኖም ፤ እኔም እንዳንተው ነው የሚሰማኝ — ከኛ ያሁኖቹ ሳይብሱ አይቀ ሩም ። ለታላቆቻቸው ያላቸው አስተያየት ዱሮ እኛ ከነበረን የተለየ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

አልባሌነትና ያለ ክራባት መሆኑ ሹም ያለመሆኑ ምልክት መሰለው ። ዋና ሹሙ ከእንግዶች ጋር ናቸው ። ጸሐፊዋ ዘንድ ቢገቡ እሷ ታገናኝዎታለች ። ቀጠሮቸውን እሷ ናት የምታውቀው ” አለ ተላላኪዉ ፣ በበሩ ላለማስገባት ጠንክሮ ።

“ እንግዲያው እንግዶቹ እስኪወጡ እዚች እጠብቃለሁ ” አለ ወንድይራድ ፣ የማያውቀው ንዴትና እልህ ይዞት ።

“ እዚህ መቆም ክልክል ነው ። ”

“ ማነው ‘ ደጅ አትጥና ’ ብሎ የከለከለው ? ” የሚያውቀው ሰው ቢያየው ኖሮ ‘ ወንድይራድ ምን ነካው ? ’ ይል ነበር ።

“ ጌታዬ ለምን ያስቸግሩኛል ። እኔ ብቀጣ ምን ይጠቀማሉ ! ለርስዎም ጸሐፊዋ ቢሮ ቢያርፉ ይሻልዎታል ” አለ ተላላኪዉ ፣ በልመና ድምፅ ።

“ መቼ ነው ለመሆኑ የተቀጠርከው ? እንግዳ ነህ መሰለኝ ” አለው ወንድይራድ ፣ ኮስተር ባለ አነጋገር ።

ይኸኔ ተላላኪው ሠግቶ ፣ “ ማን ብዬ ልንገራቸው ? — ግን ፣ ከሰዎች ጋር ናቸው ” አለ ፈጠን ብሎ ደግሞ ።

“ ወንድይራድ ” አለው በግመናጪት ።

“ እሺ ፣ እዚሁ ይጠብቁ ” ብሎ ለመክፈት እያመነታ ፣ በሩን ያዘ ።

ወንድይራድ መጀመሪያ ትንሽ እንደ መናደድ ብሎ ነበር ። ኧረ ጥሶትም ሊገባ ቃጥቶት ነበር ። አሁን ግን ፣ ተላላኪው ‘ እኔ ብቀጣ ’ ያለው ነገር ተሰምቶት ፣ በራሱ አድራጎት ወንድይራድ ተገረመ ። ‘ ሰውዬው የተቀጠረበትን ተግባር ፈጸመ እንጂ . . . ’ እያለ ራሱን ሲታዘብ ፣ ተላላኪው በፍጥነት በሩን ከፍቶ “ ይግቡ ብለዋል ” አለው ።

“ እግዜር ይስጥልኝ ” ብሎ ፣ ተላላኪው ከፍቶ በያዘለት በር ወንድይራድ ሲገባ ፣ ተስፋዬ ወደ በሩ በኩል እየመጣ ፣ “ ወንዴ ከየት መጣህ ? ” ብሎ ጨበጠው ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ወንድይራድ እቢሮዉ ውስጥ ያሉትን ሰዎች አይቶ ፣ " እው ነትም እንግዶች አሉብህና — " ብሎ ወደ ውጭ ለመመለስ አሰላ ።

" የለም ፣ የለም ቁጭ በል ፣ እኛ ጨርሰናል " አለ ተስፋዬ ። ተነሥተው ለቆሙት ሰዎች ፣ " በሉ እንግዲህ በዚህ በተባባልነው መሠረት ይሞከር ። እኔ በበኩሌ የሚያዋጣ ይመስለኛል ። " ሰዎቹ እጅ ነሥተው ወጡ ።

" ይኸውልህ ፣ እነዚህ ፣ የመሥሪያ ቤታችንን ባልደረባ ሁሉ የሚ ፈውስ ሻይ ፣ ቡና እና የመሳሰለውን የሚያቀርበው ቡና ቤት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች ናቸው " አለ ተስፋዬ ፣ ደረቱን ነፍቶ ።

" ታዲያ ጉባኤው አንተ ቢሮ የሚሆንበትስ ምክንያት ፣ ግኅ በረተኛ ነኝ እንዳትለኝ ።"

" ብሆን ምናለበት . . . ግን አይደለሁም ። ' መጣኔ-ሀብት ' እንደ መሆኔ መጠን ' የድርጅቱ አማካሪ ' ነኝ " አለ እየሣቀ ።

" አበልም አለኝ በለኛ ! " አለ ወንድይራድም ፣ ፈገግ እያለ ።

" አዎ ፣ እርግጥ ። ቡናና ሻይ በነጻ ነው የማገኘው ። ስለዚህ ፣ በነጻ በማግኘቴ ለቡናና ለሻይ ከማወጣት የማድነው ገንዘብ ነው ከነርሱ የማገኘው አበል ። "

" ለምን ምክርህን በነጻ አትሰጣቸውም ? "

" ለምን በነጻ ? ምን አይተህ ። ቡና ቤቱ ደርጅቶ በርከት ያለ ገቢ ማግኘት ሲጀምር ፣ ቀጥታ የገንዘብ አበል እቀበላለሁ " አለ ተስፋዬ ፣ በቁም ነገር ።

" ስንት ሊሰጡህ ይችላሉ ? ይልቅስ ስም ከሚሆንብህ የአበሉ ነገር ይቅርብህ ። "

" ለምንድር ነው ስም የሚሆንብኝ ? ለምሰጠው አገልግሎት ዋጋ ስለ ተቀበልሁ ? እንግዲያው ፣ ዋናዉ ነገር እዚህ ላይ ነው ። እነ ዚህ ሰዎች ቡና ቤቱን በዘመናዊ የንግድ ዕቅድ እንዲይዙት ያስፈ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ነገ ሠላሳ ሣንቲሙን ካላመጣህ አልምርህም ፤ እከስሃለሁ ” ብሎ ፤ አንኳኩቶ አጕናፍር ቢሮ ዘው አለ — ቡናዉን ይዞ . . .

አጕናፍር ፤ አምስተኛዉን ገጽ አርሞ መጨረሱ ላይ ነበር ። ሁሉን ነገር ትቶ ቡናውን ተቀበለ ። ወዲያው ወንድይራድ ፤ ገብሬ በሩን ከፍቶለት ገባ ። አጕናፍርም ተነሥቶ እየጨበጠው ፤ “ ከየት ተገኘህ ? ሀረፍ በል ። ልጁ ሳይሔድ ፤ ቡና ወይ ሻይ ? ” አለው ።

“ እሺ ። ”

የቡና ቤቱ ወጣት ፡ “ ለሌላ ሰው ያመጣሁት ቡና አለ ” ብሎ ፤ ቀድቶ ሰጠው ።

አጕናፍር ፤ “ ስንት ነው ያለብኝ ? ከዚህ በፊት ያልከፈልኩ ህም አለ ፤ አይደለም ? ” አለው ።

“ አዎ ፤ የጠዋት አንድ አለ ። ከዚህ ጋራ ሦስት ነው ። ”

“ በል ከዚህ ላይ ለራስህ ያንድ ቡና መጠጫ ጭምር ቀንስ ” ብሎ አጕናፍር ፤ አንድ ብር ሰጠው ።

ልጁም ብሩን ከተቀበለ በኋላ ፤ መልስ ለመፈለግ እኪሱ ውስጥ እጁን እየሰደደ ፤ “ ጌታዬ ፤ ተላላኪዎ በዱቤ የጠጣበትን ሳንቲም አልከፍልም ብሎ ከደሞዜ ሊያስቆርጥብኝ ነው ። ልጥራውና እንዲ ከፍለኝ ይቆጡልኝ ” አለ ። ይኸን ይበል እንጂ ፤ ገብሬን ለመጥ ራት አልሞከረም ።

“ የሱንም ጭምር ከሱ ላይ ውሰድ ” አለ አጕናፍር ።

እጅ ነሥቶ ፤ በሩን ዘግቶ ከወጣ በኋላ ፤ ገብሬን ቀረብ ብሎ ፤ “ በል ነገ ይዘህ እንድትመጣ ። አለበለዚያ ታውቀዋለህ ምን እንደ ሚደርስብህ ” ብሎ ዝቶበት ሔደ ። ገብሬ ተበድሮም ቢሆን ከፍሎ ፤ ከዚህ ከነገረኛ ልጅ መገላገል ቀረጠ ። በዱቤ ቡና ምክንያት ለተ ከበሩ ጠቅላይ ሹሙ ተላላኪ የመሆን ዕድሉ እንዲደናቀፍበት አል ፈለገም ......


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ዱን ያውቀዋል ። በቅርብ ጊዜ ረዳት ጠቅላይ ሹም ሆኖ የተሾመ ነው ። ሁለተኛውንም በመልክ ያውቀዋል ። እሱም ረዳት ጠቅላይ ሹም ነው ። ሆኖም እንደ ዘበት ሰላም ካላቸው በኋላ ፡ ተስፋዬን ፡ “ ከአጕናፍር ጋር በለጠን እቤት ልንወስደው መሔዳችን ነው ” አለው ።

“ ምነው ደኅና አይደለም እንዴ ? ” አለ ተስፋዬ ጥቂት ደንገጥ ብሎ ።

“ ‘ ብርድ ብርድ ይለኛል አለ ” አለኝ አጕናፍር ። ትኩሳት ይዞታል ማለት ነው ። ከአጕናፍር ጋር በዚያው እቤት መሔዴ ነው ፤ ልልህ ነው የመጣሁት ” ብሎ ወንድይራድ ፡ ሰዎቹንም ሰላም ሳይል ወጥቶ እብስ አለ ።

ተስፋዬም ወደ ስልኩ ሔዶ ጸሐፊውን ፡ “ አቶ በለጠን አገናኚኝ ” ብሏት ፡ ወደ ቆሙት የሥራ ጓደኞቹ ዘወር ብሎ ፡ “ ቆዩ አትሒዱ ፡ ነገሩን ሳጣራ ” አላቸው ።

ወጺያው ጸሐፊው ፡ “ አቶ በለጠ ቀርበዋል ” አለችው ።

“ በለጠ ፤ ምነው ምን ሆንክ ? ” አለ ተስፋዬ ፤ ሥጋት እፊቱ ላይ እየታዩ ።

“እንዴት ነው የሚያደርግህ ? . . . ‘ ብርድ ፤ ብርድ ? ’. . . ለምን ሐኪም ቤት አልወሰድህም ? . . . እንዴ ትኩሳት ዋናው ሕመም አይደለም ፤ ምልክቱ እንጂ ! ስለዚህ ሐኪም ቢያይህ ይሻላል . . . ”

“ እዎ ። አጕናፍርና ወንድይራድ አሁን አብረው ወጡ ! ወዳንተ ለመምጣት . . . . . . . መልካም እንግዲያው — ግን እርግጠኛ ነህ ? ተው ልምጣና ልውሰድህ ። እዎ ፤ አሁን እዚህ ሲነግረኝ መጥቶ ነበር . . . መ — — ልካም ። እቤት በቀጥታ ነው የምመጣው ፤ እዚያው እደሃለሁ ። ”

“ እንዴት ነው ፤ ደኅና ነው ” አለ አዲሱ ረዳት ጠ/ሹም ።

“ ደኅና ይመስለኛል ” አለ ተስፋዬ ፤ የወንድይራድ አኳኋን ትዝ እያለው ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ያለፈው ቅዳሜ የመኪና አደጋ የደረሰበት አይደለም ? ” አለ ነባሩ ረዳት ጠቅላይ ሹም ።

“ አዎ ። ”

“ ይገርምሃል ። አይተርፍም ሲባል ነበር እኮ መጀመሪያ የሰ ማሁት ” አለ ብርሃኔ ፣ አዲሱ ረዳት ጠቅላይ ሹም ።

“ እኔስ ከዚያ የባሰም ሰምቼ ነበር ። በሦስተኛው ቀን አንዳች ነገር አልሆነም የሚል ወሬ ደሞ ሰማሁ ” አለ ዘርፉ ፣ ነባሩ ረዳት ጠቅላይ ሹም ።

“ ሰዉ ወሬውን ከየት እንደሚያመጣው ነው የሚገርመኝ ” አለ ብርሃኔ ፣ አዲሱ ረዳት ጠቅላይ ሹም ።

“ እሱ ደኅና ነው ፤ ሰዉ ዝም ብሎ ነው ሲዘባርቅ የሰነበተው ። ይልቅ አሁን ይህን ጉዳይ ምን ማድረግ ይሻላል ? ” አለ ተስፋዬ ወደ ቀድሞው ነገራቸው ተመልሶ ።

“ ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም ይባላል ። እኔም የሰማሁ ትን ነገርኩህ ። መውሜውን መፈለጉ ያንተ ፋንታ ነው ” አለ ዘርፉ ፣ ነባሩ ረ/ ጠ/ ሹም ።

“ እሱማ ነው ። ብቻ ጉባዔው ውስጥ የምትገኘው አንተ እንጂ እኔ አይደለሁም ። ስለዚህ ፣ እዚያ ልታግዘኝ ትችላለህ ” አለ ተስፋዬ ።

“ መሞከሬማ የት ይቀራል ። ብቻ ፣ ብቻዬን ሰውየውን ልቋ ቋማቸው አልችልም ማለቴ ነው እንጂ ። ታውቃቸዋለህ ፣ አንዴ ከተ ነሡ የፈለጉትን እስኪያገኙ እንደማይተኙ ” አለ ዘርፉ ።

“ እኔም እኮ የጉባዔው ተካፋይ እንድሆን ታዝዣለሁ ። እኔ እንደዚህ ዐይነት ነገር መኖሩን ግን ጨርሶ አልጠረጠርኩም ነበር ። ለማናቸውም የኔንም ድጋፍ ታገኛለህ . . . ይኸው እዚህ እንኳ ሁለት ደጋፊዎች አሉህ ማለት ነው ። ኧረ ለመሆኑ የኰሚቴው አባሎች ስንት ናቸው ? ” አለ ብርሃኔ ፣ ወደ ዘርፉ ዞር ብሎ ።

“ ከነሊቀ መንበሩ አምስት ። ”

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑ ነው ። በተለይ የአባቱ ታላቅ ወንድም ቁጣ ፤ ‘ ከደሃ ልጆች ጋር አብሮ እየዋለ የነሱን መሠሪ ሐሳብ ይከተላል ፤ እንደ ገደል ማሚቶ ያስተጋባል ፤ ለጠሰኛ ራሳቸውን ጥብቅና ከወሰዱ የድሃ ሞልቃቆች መንጋ መኻል ገብቷል ’ ነው — ምሬታቸው ። የአባቱ እናት ቅሬታ ግን ፤ ያለ ዕድሜው የሚያገረጅፈውን መላ የሌለው ጢሙን ለምን ያሳድጋል ነው እንጂ ፤ ‘ ይኸ ስለ ጢሰኞች ቅብጥርስ የሚለው ፍሬከርሲኪና ሌላ ሌላ የልጅ ነገሩ፣ ነፍስ ሲያውቅ ትዳር ሲይዝ የሚቀር ነው ’ የሚል ነው . . . . . . . . . .

“ እኔ ምንም አልፈልግ ። ”

“ ታዲያ እንዲሁ ቁጭ ልንል ነው ? እባክሽ አንድ ነገር ጠጪ ። ”

“ እንዲያውም ፤ ሜክስኮ አደባባይ እንሒድና እኔ ቡና ልጋብዝሽ ” አለች ታፈረች ።

“ እኔ የተሻለ አሳብ አለኝ ። ራታችንን እዚህ በልተን ቡና ውን እዚያ እንጠጣ ። ”

“ ጥሩ ። ”

ዘነመች መጥሪያዋን ደውላ ገረዲቱ ስትመጣ ፤ “ ሰማሽ ? ” አለቻት ።

“ እመት ። ”

“ እራታችሁን ጨረሳችሁ ? ”

“ የለም ገና እየሞቀ ነው ። ”

“ እንግዲያው ፤ እኛ እንቸኩላለንና ቶሎ የኛን ስጪን ። ቶሎ በይ ! ”

“ እሺ ” ብላ ገረዲቱ ወጣች ።

“ በያ ወስፋት የሚከፍት አንድ ነገር እንጠጣ ። ምን ይሻል ሻል ? ” አለቻት ታፈረችን ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ምን ትጠይቂኛለሽ ፣ ከጠጣሁማ ያችኑ ማርቲኒዩን ስጪኝ ።"

መጠጡ እንደ ቀረበ ፣ "በይ እንጂ ትልቁን ወሬ ንገሪኝ ?" አለች ዘነመች ።

" እስከዚህ አይደለም እኮ " አለች ታፈረች ፣ ማርቲኒዋን ፉት እያለች ።

" አንድ ሁነኛ ሰው ማግኘት ፣ በከተማችን ፣ ባሁኑ ጊዜ ፣ ቀላል አይደለም እኮ ፣ እርግጥ ከተገኘ ። "

" ብዙም ባይሆን ደኅና ሰው ዐልፎ ዐልፎ የት ይጠፋል ። ብቻ እንዳጋጣሚ ሁለት የሚኳኋኑት አብዛኛውን ጊዜ አይገጣጠሙም እንጂ " አለች ታፈረች ።

" አሁን እናንተ የምትኳኋኑት ተገናኝታችኋል ? " አለች ዘነ መች ፣ በምጸት ።

" ይመስለኛል " አለች ታፈረች ፣ ተከዝ እያለች ።

" የለም አንቺ ልጅ ! ባንድ ቀን ፍቅር ያዘሽ መሰለኝ " አለች ዘነመች እያዘነች ።

" እስከዚያስ አልደረስኩም ። "

" ማነው እሱ ለመሆኑ ? "

" የምታውቂው አይመስለኝም ። "

" እኔ የማላውቀው ወንድ እዚህ ከተማ ውስጥ ብዙ ያለ አይ መስለኝም " አለች ዘነመች ፣ እርግጠኛነት በተሞላበት አነጋገር ። እንዲያውም ፣ ' የማላውቀው ብዙ ያለ አይመስለኝም ' ስትል ' የማ ላውቀው አንድም የለም ' በሚል መንፈስ ነበር ።

ጥቂት ዝም ካሉ በኋላ ፣ " ማን ይባላል ? " አለች ዘነመች ።

" አጐናፍር " ብላ ፣ ታፈረች የሚሠራበትን መሥሪያ ቤት ነገረቻት ።

" አጐናፍር ማ ? "


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ እንዴት ? ” አለች በነመች ጆሮዋን አቆቁራ ፤ ‘ እሱን ባላ ውቀውም የሱን ዐይኖቶቹን ብዙ ዐውቃለሁ ’ ለማለት ያሰበችውን ጥላ ።

“ ምንም ነገር የለማ ። ”

“ ታዲያ ስለምን ኖሯል፣ እስካሁን ልባችንን እንደዚህ ስናቆ ስል የነበረው ? ”

“ አንቺ ነሻ ለዚህ ያደረሺው ። ”

“ በይ እቴ ፤ ራታችንን እንብላና ያቺን ቡና አጠጪኝ ። ”

“ ጥሩ ” አለች ታፈረች ።

በዚህን ጊዜ ገረዲቷ ሮጥ እያለች ገባች ። “ ጌቶች ስልክ ላይ ናቸው ! ወደዚህ ላዞርልዎት ? ” አለች ።

“ ‘ አለች ’ አልሽ እንዴ ? ” አለች ዘነመች በቁጣ ።

“የለም ድምፃቸውን ስላወቅሁት፣ ገና ሳይጠይቁኝ ‘ ጌታዬ ላንድ ደቂቃ ይጠብቁኝ ፤ የጣድኩት ገንፈለብኝ ’ ብያቸው ነው የመጣሁት ።”

“ ታዲያ ዛሬ ማታ ማንም ቢደውል የለሁም ብዬ አልነገር ኩሽም ? ለምናባሽ ይመስልሻል፣ ስልኩን ከዚህ ዘግቼ በዚያ በዕቃ ቤት በኩል የከፈትኩት ! ? አሁንም የለሁም ፤ ውጪ ወጥቻለሁ ። ’

“ እንዳንድ ቀን እንዳይቆጡኝ ላጣራ ብዬ ነው ” ብላ ገረዲቱ ፣ እያጉረመረመች ፤ በሆዷ እየተሳደበች ወጣች ።

“ ይኸውልሽ አንዱ ቤትና ትዳሩን የሚወድ ነው ። ቸር ሰው ነው ። የቤቱን ኪራይ እሱ ነው የሚከፍልልኝ ። አንድ ሰባት ልጆች አሉት ” አለች ፤ በማፌዝ ።

“ እኔ መቼም የማልስማማበት ነገ እንደሆነ ታውቂያለሽ ። ካልጠፋ ወንድ ፤ ካገቡት ጋር መወዳጀትስን ምናለ ብተይ ? ”

“ ካገባ ወንድ ጋር መሔድ ብዙ ጥቅም አለው ። ጉዱ እንዳይ ታወቅበት ስፈልግ፣ መልካም ታዛኸሽ ይሆናል ። ደግሞ፣ ሲሳይም


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ጊዜ ዘነመች ከቶኛ ደነገጠች ። ያስተማሪዉ አርጩሜ ትዝ አላት ። ጀርባዋን ይቆንቆናት ጀመር ። ሆኖም ፣ መሸበሯ እን ዳይታወቅ እየጣረች ፣ “ አንዳንድ ጊዜም ልክ አሁን አንተ እንዳደ ረግኸው እየነገረኸኝ ደብዳቤዎቿን ታጽፈኛለች ። እጅ ጽሕፈታ ችንም እንዳልከው በጣም ስለሚመሳሰል ፣ እኔ የጻፍኩትን እሷ ከጻፈ ችው መለየት ያስቸግራል—ሁለታችንንም ደኅና አድርጐ ለሚያውቅ ሰው እንኳ ። ”

“ ቀጣፊ ! ” ሲላት በርግጋ ብድግ አለች ። “ ቁጭ በይ !” አላት ፣ በትእዛዝ ድምፅ ።

እመነታች ። “ ሮጠሽ የምታመልጪ መስሎሽ እንደሆነ ፣ ተሰፋ ቁረጭ ! በድንጋይ ነው ኰቴሽን የምሰብረው ! ” አላት ። ዘነመች ትምል ትገዛት ጀመር ፤ “ ቁጭ በይ ነው የምልሽ ዛሬ ! ” አላት አሁ ንም በቁጣ ትእዛዝ ። ቁጭ አለች ።

“ ይኸኔ ደብዳቤዎቹ ሁሉ እዚህ ቦርሳሽ ውስጥ ይሆናሉ ።”

“ እግዚአብሔርን ምንም የለ ። ”

ቦርሳዋን ነጥቆ ፣ ውስጡ ቢፈልግ ደብዳቤዎቹን አጣ ። ግን ፣ ከታ ፈረች ተላከ የተባለውን ደብዳቤ ረቂቅና ፣ ቀለሙ የሚመስለውን ብዕር አስተዋለ ። “ ይኸን እንቺ አደለሽም የጻፍሺዉ? እውነቱን ብትናገሪ ይሻልሻል ! ” አላት ።

“ ነኝ ” አለች ሌላ መውጫ እንደሌላት ስትገነዘብ ።

“ ደብዳቤዎቼን አንዱንም አልሰጠሻትም ። አይደለም ? ”

“ የመጀመሪያዉን ስወስድላት . . . እምቢ ስትል ጊዜ . . . እኔ ላንተ አዝኘ . . . ተስፋ ትቆርጥ ” ስትል ፣ አቋርጦ ፣

“ ቀጣፊ ! ” አላት ፣ በቁጣ ።

“ ሙት ሙት ! ”

“ እኔ አልሞትም ፣ አንቺዉ ድርቅ በይ ! ! . . . ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

"ሰቃውን ሁሉ እንዳሻሺ፤መብራቱንም አጥፊ ፤ በሩን ዝጊ ። እኔ መቀ ኛቴ ነው ። አንድ ረብሻና ጩኸት አልፈልግም" አለቻት ። ዱሮ ገና ውስኪው በደም ሥሯ መሠራጨት ጀምሯል ። ብርጭቆዋን ሞልታ መኝታ ቤቷ ገባች ። አልጋዋ ላይ ቁጭ እንዳለች ደኅና አድ ርጋ ተጎንጭታ ብርጭቆዋን ኮሞዲኖው ላይ አደረገች ። የቀን ልብ ሷን አውልቃ ፤ የሌሊት ልብሷን አጠለቀች ። አልጋዋ ውስጥ እንደ ገባች ፤ ከውስኪዋ እንደገና አንድ ተጎነጨች ። ወደ ፊት ለፊቷ ቀና ብላ ስትመለከት ፤ሀይኖቿ እግርግዳው ላይ እተሰቀለው የማርያም ሥዕል ላይ ዐረፉ ። እዚያው ተሰክተው ቀሩ ። ጥቂት እንደ ቆዩ ሥዕሉ እየደበዘዘ ከግድግዳው ጋር ተዋሀዶ አንድ ሆነ . . .


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አምስት

‘ብርሲ ክነቃ . .’ .

ማድቤት ፣ ብርቄ ለሁለተኛ ጊዜ ቡና አፍልታለች ። ከበደና ቀስማ ቁጭ ብለው እያወጉ ቡናውን ይጠጣሉ ። ተስማ ፣ በከበደ አማካይነት ፣ ከብርቄ ጋር ‘ይቅር ለእግዚአብሔር’ ተባብለዋል ። ብርቄ እንደ ልማዷ ስኒዋን መመልከቷን ቀጥላለች ። ብቻ ፣ ዛሬ ስኒው ‘መንገድ’ ያለው አይነት ስለሆነ ፊቷን አጥቁራለች ። በልቧም ተስማ መሔድ ሲኖርበት ይቅርታ ተደርጐለት በመቅረቱ ፣ ‘የሱ ጦስ ነው ወደኔ የዞረው’ ብላ አምናለች ። ነገሩ በጣም አበሳጭቷታል።

ከበደ እልቧ ውስጥ ያለውን ሳያውቅ ፣ “ብርቄ ! ምነው ዝም አልሽ ? ስኒው ምናለ ? ” አላት ።

“ ምን ያረግልሃል ! አንተ አታምንበት ።”

“ ይልቅስ ንገሪኝ ። ከገንዘቡ አካፍሊኝ እንዳልልሽ ነው የፈራሽው ? ገና እጅሽ ሳይገባ እንዲህ የሳሳሽለት ፣ ኋላማ ምን ልትሆኝ ነው ? ”

“ ሲወጣልኝ አምስት ብር እሰጥሃለሁ ” አለች ብርቄ፣ ‘በልቧ ምነው ይኸ ሰው ቢተወኝ’ እያለች ።

“ አምሳው ሺም ቢወጣልሽ ፣ ይኸን ብቻ ነው የምትሰጪኝ”

“ መቼ አነሰህ፡ ምን አውጥተህበታል ? ” አለች ብርቄ ።

“ አቤት ስስት ! ” አለ ከበደ ፣ በዜማ ።

“ በሙሉ ለመውሰድ ከፈለግህ ፣ ለምን ሎተሪዉን ራስህ አትገዛም ? ”



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" እባክዎ እኔ እንደ ሆንኩ የዕድሌን አላጣም ። ደግሞ ፣ ምናለች በሉኝ ፣ የዛሬው ሎተሪ ይደርሰኛል ። በሕልሜ ታይቶኛል ። ትላንት ሌሊት በሕልሜ አንድ ዐሐይ የመሰሉ ሽማግሌ በትልቅ ስልቻ ሙሉ ሙልሙል ተሸክመው መጥተው ፣ ለኔ አንድ ባንድ እያወጡ ሲሰጡኝ ብንን አልኩ " አለች ብርቄ ፣ ደስ ደስ እያላት ።

" እንዳፍሽ ያርግልሽ " አለ ተሰማ ።

" አሜን " አለች ፣ ከልቧ ።

በዚህን ጊዜ የውጪው በር ሲደበደብ ሰሙ ። ከዚያ ተከትሎም ፣ የልፍኙ የመጥሪያ ደወል ተደወለ ። ስለዚህ ፣ ተሰማ ወደ ውጪው በር ፣ ከበደ ወደ እልፍኝ ተሯሩጠው ሔዱ ።

እውጪው በር እንደ ደረሰ ፣ ተሰማ ትንሿን በር ከፈተ ። የቤቱ ባለቤት አሽከር ነው ።

" ምነው ወዳጄ ደወሉን መደወሉ አይሻልም ? ለምን እንደዚህ ታንኳኳለህ ? ጌቶች ተኝተው ነበር ፣ ቀሰቀስካቸው ! "

አሽከርየው ተሰማን አየት አድርጎ መልስ ሳይሰጠው ፣ " ጌቶች ካሉማ መልካም ነው ። ይኸን ደብዳቤ ቀኛማች ለምሳ ሲገቡ እንዲደርሳቸው ' ወስደህ ስጥ ' ብለውኝ ነበር ። ታሉ ልስጣቸውና መልሱን ወዲያው ይገፎ እሔዳለሁ ። ጐሽ ፣ ከመመላለስ ዐረፍኩ " አለ ፣ ገሚሱን ለተሰማ ፣ ገሚሱን ለራሱ ።

" አምጣ ፣ ሲነሡ እሰጥልሃለሁ ። "

" ምነው አሁን በር አንኳኩተህ አስነሣሃቸው አላልከኝም? "

" ' ቀሰቀስካቸው ' ነው ያልኩት ። ቢነሡም እኔ እሰጣቸዋለሁ ፣ ስጠኝ ። መልሱን ነገ ናና ውሰድ ። "

" ለምንድር ነው እኔ ጉብኜ የማልሰጠው ። እሆሆሆ ! ! ' በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት ' አለ ሰውዬው ፣ እንደኔ ዐይነት ነገር አጋጥሞት . . . . ሰማህ ጌታው ፣ ቤቱና ሀብቱ እኮ የቀኛማች ነው ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ቃማን አሽከራቸው ነኝ ። ቤቴ ነው ። እኔ ተከልክዬ ማን ሊገባ" እያለ ሊቆጥል ሲል ፣ ተሰማ አቋረጠ ፣

" ይኽ ሁሉ ንግግር ምን ያረጋል ። እስካለንበት ድረስ ቤቱ የኛ ነው ። የምንኖርበትም በብላሽ አይደለምና ፣ እስካለንበት የምናዝበት እኛ ነን ። ይልቅስ ወረቀቱን አምጣ !! "

" የለም ሳንቲ አልሰጥም 'በጃቸው ስጥ' ነው የተባልኩት ። ! "

" ለየትኛዉ ጌትኝ ? . . . ምነው አሁን ለምሳ ሲመጡ እንዲያገኙት ወስደህ አድርስ ነው የተባልኩት አላልከም ? "

" ብልስ ቃዲያ ! አሁን መኖራቸውን ሳውቅ ፣ በጃቸው ነው የምሰጠው ስለስ ጊዜ ! ግን ያዘኛል ! "

" ወንድሜ ለነገር ነው የመጣኸው ? እኔ ብዙ ሥራ አለብኝ ፣ ትሰጠኝ እንደሆነ ስጠኝ ፥ አሰጠኝ እንደሆን ይዘኸው ሒድ ! " ብሎ ተሰማ ፣ በሩን ዘግቶ ቀረቀረ ።

አሽከሩ መልሶ መላልሶ በሩን በኃይል ያንኳኳ ጀመር ። ውሻዉ ከቤቱ ወጥቶ ፣ ሰንሰሉን ለመበጠስ እየቃጣው ፣ እየዘለለ ይጮህ ጀመር ። ተሰማም ፣ አሽከርየውን ማንኳኳቱን እንዲያቆም ፥ አለበለዚያ ውሻዉን ፈትቶ እንደሚለቅበት አስጠነቀቀው ። አሽከርየው ማንኳኳቱን ተወ ። ውሻዉ ግን ጩኸቱን ቀጠለ ። ከበደ ፣ ምን ነገር እንደሆነ እንዲያጣራ ቃዘ ፣ ከሣሎን አበረንዳ ላይ ወጣ ። አሽከርየዉም ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ መልክቱን ተሰማ አልቀበል ያለው አስመስሎ ይናገር ጀመር ።

" ምንድነው ጋሼ ተሰማ ? " ብሎ ከበደ ጠየቀ ።

" 'መልክት ከቤቱ ጌታ ይገባል' ነው የሚለው " አለ ተሰማ ፣ ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ ፣ ወደ ውሻዉ እያመራ ።

" ታዲያ ለምን አይቀበሉትም ? " አለ ከበደ ፣ የበረንዳውን ደረጃ ወርዶ ወደ ውጪዉ በር እየመጣ ።

" አልሰጥም አለኝ ። "

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

የላቀ ሥልጣን ፡ ማዕረግና ኃይል ለማግኘት ፣ እንዲሁ እንደ ቃተተ ይኖራል ። በቃኝ እሚልበት ደረጃ ሳይደርስ ፣ ሞት ይጠልፈዋል ። ችግሩ ይልቅ ይኸ ነው ። ”

“ ግዴለም ። ለክርክራችን ያህል ሁሉንም አገኘ ። ደረሰበት እንበል ። እኔ ከዚያ በኋላስ ? ነው የምለው ። ”

“ ተዝናንቶ መደሰት ነው ! ዓለምን መቅጨት ነዋ ! ”

“ ፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ መጀመሪያ እንደ ሔድኩ ፣ የጀመርኩት ትምህርት ‘ ኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት ’ የሚል ነበር ። ያኔ አንደኛዉ መጽሐፍ ውስጥ ያነበብኩት ምሳሌ ፣ እስከ መቼም ከልቤ አይጠፉም ። ጸሐፊዉ ለኢኮኖሚ ልማት መሰናክል ናቸው የሚላቸውን ፣ ልማዶችና አስተያየቶች ሲተች ነው ፣ ምሳሌው የመጣው ። አንድ ምዕራብ አፍሪቃ ሀገር ፣ አንድ አውሮጳዊ ፣ አንድ አፍሪቃዊ የፍሬ ዛፍ ሥር ተኝቶ አየውና ቀረበው ።

አውሮጳዊው ፡ ‘ ዛፍ ሥር ከመተኛት ለምን እላዩ ያለውን ፍሬ ለቅመህ ገበያ ወስደህ አትሸጥም ’ አለው አፍሪቃዊዉን ።

ያም ዛፍ ጥላ ሥር ጋደም ብሎ እንደ ተዝናና ፣ ‘ ለምን ? ’ አለው በጭሩ ።

‘ ገንዘብ ታገኛለሃ ’ ሲል መለሰ አውሮጳዊዉ ።

‘ አገኘሁስ ? ’

‘ የፈለግኸውን ትገዛለህ ፣ ቀሪውንም ታጠራቅማለህ ። ’

‘ አጠራቅሜስ ? ’

‘ የራስህን ሱቅ ትከፍታለህ ።

‘ ሱቅ ኖሮኝስ ? ’

‘ ነጋዴህ ትልቅ አስመጭና ላኪ መሆን ትችላለህ ። ’

‘ ትልቅ ነጋዴ ሆኜስ ? ’

‘ በንግድ ሥራህ ሳቢያ ዓለምን ትዞራለህ ፤ ብዙ ትልቅ ሰዎችም ትተዋወቃለህ ! ’


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

የምሰጥህ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው ። አንድ ጊዜ እንኳ ፣ ከእ ንግዲህ ወዲያ ፈልጌህ ብትጠፋ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንደምገደድ አስቀድመህ እንድታውቀው ” አሉት ነገራቸውን ቁርጥ አድርገው ። አጐናፍርም ለመናገር ቃጣቶ ነበር ። በኋላ ግን ሐሳቡን ለውጦ በሩን ከፍቶ ወጣ ።

አጐናፍር እየተበሰጨጨ ተመልሶ እቢሮው ሲገባ ፣ ‘ ላቶ አጐናፍር ’ የሚል ላዩ የተጻፈበት አንድ ፖስታ ጠረጴዛዉ ላይ አየ ። ብድግ አድርጐ ቀዶ እውስጡ ያለውን ፤ እሁለት የታጠፈ ብጣሽ ወረቀት አወጣ ። አነበበው ። ደግሞ አነበበው ። የተጻፈውም የሚከተለው ነው ፤

“ ልጅ አጐናፍር ፣ ጤና ይስጥልኝ ! የሚበጅህን የምታውቅ እንደሆነ ታፈረች ባንኳውን ተዋት ። ካልተውክ ብዙ እንቅልፍ አታገኝም ፣ ወይስ ብዙ እንቅልፍ ታገኛለህ ልበል ! ”

በጽሕፈት መኪና ነው የተጻፈው ። ቀንም ፣ ፊርማም ፣ አድ ራሻም የለውም ። አገላብጦ አየው ። ከማን እንደ ተላከ ፣ በማን እንደ ተጻፈ ለማወቅ የሚያስችል ምንም መረጃ የለውም ። አጐናፍር እንቦልኩን አየው ። ቴምብር የለበትም ። ስለዚህ መጥሪያውን ደወለና ገብሬ ገባ ።

“ ይኸን ወረቀት ማነው እዚህ ያስቀመጠው ? ”
“ እኔ ነኝ ። ”
“ ማን ሰጠህ ? ”
“ እዚህ እውጭ ካሉት ጫማ - ጠራጊዎች አንዱ ነው ።”
“ ታውቀዋለህ ፣ ታስታውሰዋለህ ? ”
“ አዎ ። ”
“ ጥራው ። ”
“ እሺ ። ”
ልጁ ተጠርቶ መጣ ።
“ አንተ ነህ ይኸን እንቦልክ ወረቀት ያመጣኸው ? ”
“ አዎ ፣ ጌታዬ ። ”
“ ከየት አመጣኸው ? ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ የሰጡኝ አንድ ሰውዬ ናቸው ። ‘ ይኸን ላቶ አጕናፍር ስጥ ልኝ፤ እኔ ቸኩላለሁ ’ ብለው ሰጡኝ ” አለ ልጁ ፤ ወረቀቱን እንዲያ ደርስ የተሰጠውን ጉርሻ ያውቅብኝ ያሆን ብሎ እየሠጋ ።

“ እንዴት ዐይነት ሰው ነው ? በመኪና ኖሯል ? ምን ዐይነት መኪና ? ” እያለ አጕናፍር አጣደፈው ።

“ ደኅና አርጌ አላየኋቸውም ። ብጆ ፤ ቀይ ናቸው ። በመርቼ ዲስ ነው የሚሔዱት ፤ ሰማያዊ መርቸዲስ ” አለ ልጁ ።

“ በል እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። ደኅና ዋል ” አለ አጕናፍር።

“ አጠፋሁ እንዴ ጌታዬ ? ” አለ ልጁ በሥጋት ።

“ የለም ! የለም ! ! ምንም አላጠፋህም ” አለ አጕናፍር ፈጠን ብ ።

ልጁና ገብሬ ወጡ ። አጕናፍር እንደ ኢያሱ አቀማጥሎ እቢ ሮው ውስጥ ይንጐራደድ ጀመር ። ምንም ያህል ሳይቆይ ፤ ተሳላኪው፤ እንደ ልቡ ፤ መጥቶ ‘ ዋና ሹሙ ይፈልጉሃል ’ አለው ። አጕናፍር፤ ዋና ሹሙን ካያቸው ቢያንስ ዐሥር ቀን ያህል ዐልፎት ስለ ነበረ፤ ለምን እንደ ጠሩት መላ መጣል አልቻለም ።

ሲገባ ኖር ብለው በትሕትና ተቀበሉት ። ተቀመጠ ። “ ጠቅ ላይ - ሹም - አከሉ አሁን ደውለውልኝ ነበር ” አሉ ዋና ሹሙ። አጕናፍር ዝም አለ ፤ የሚከተለውን እየጠበቀ ።

“ አዘጋጅ ያልኩትን ማስታወሻ ሳያዘጋጅ ቀረ ይላሉ ። እን ዴት ነው ? ” አሉ ዋና ሹሙ ።

“ እኔ መቼ ደረሰኝና ። ነገሩ መኖሩንም ዛሬ ጠዋት ከላቸው እፍ ለመጀመሪያ ጊዜ መስማቴ ነው ! ! ” አለ አጕናፍር ።

“ እንዴት ? አቶ ጀንበሬ አልሰጠህም ? ” አሉ ዋና ሹሙ ።
“ የለም ፤ አልሰጡኝም ። ”

“ እኔ ፤ ከጠቅላይ - ሹም - አከሉ እንደ ተቀበልኩ ላንተ ስጥ ብዬ ምነው ሰጥቼው ” አሉና ዋና ሹሙ ስልክ አንሥተው ደወሉ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ብርሃኔ ፣ ቀጠሮ አለብህ እንዴ?" አለ ተስፋዬ ወሽመጡ ተበጥሶ ፣ በቅያሜ ።

" የለብኝም ። "

" እንግዲያው አውሮፕላን ማረፊያ ምግብ ቤት ምሳችንን እንብላ — ልጋብዝህ ። "

" ደስ ይለኛል " አለ ብርሃኔ ።

" በኔ መኪና እንሒድ " አለ ተስፋዬ ።

ብርሃኔ ግን ' በኔዋ ' ካልሔድን ሞቼ እገኛለሁ አለ ። ተስፋዬም ስለ ስብሰባው ዝርዝሩን ለመስማት ስለ ነበር የቸኮለው ፣ ብርሃኔ መኪና ውስጥ ዝም ብሎ ገባ ። ጸጥ ብለው አጥር ግቢውን ወጡ ።

" እንድሔድ ተፈረደብኝ አይደለም ? " አለ ተስፋዬ ፣ መሪር ፈገግታ ፊቱ ላይ እያሳየ ።

በቀጥታ ወደፊቱ መንገዱን እያየ ፣ " አዎ ፣ ኮሚቴው ወስኗል፣ ለተከበሩ ጠቅላይ ሹሙ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲቀርብ " አለ ብርሃኔ ። ምንም አስተያየት ሳይጨምር ጸጥ ብሎ መኪናውን ወደ አዲሱ አውሮፕላን ማረፊያ አስፈተለከ ። ተስፋዬ ጸጥ ብሎ ከመኪናዋ ውጭ የማይመለከቱ ዐይኖቹን ወርውሮ በሐሳብ ባሕር ይዋኝ ነበር ።

የነገው ቀጠሮ አዲሱ መሥሪያ ቤት ሥራ የሚያስገኝለት መሆኑን ተጠራጠረ ። ብዙ እንቅፋት ታየው ። ዋናው የሹመቱ ጉዳይ ነው ። ያንድ መሥሪያ ቤት የክፍል ዋና ሹም ሆኖ ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት እንደዚሁ ሔዶ መቀጠር የማይሆን መሰለው ። ዝውውሩ በኦፊሲየል መሆን አለበት ። ይኸን ለማድረግ ደግሞ ብዙ ጣጣ ስላለው ፣ ሹሙ እሱን ለመርዳት ሲል፣ በነገሩ ምን ያህል ለመግፋት እንደሚፈቅድ እርግጠኛ አይደለም ። ስለዚህ ፣ የሚያዋጣው የመንግሥት ያልሆነ ድርጅት ብቻ ፣ መስሎ ታየው ። ለጊዜው ይኸንን ሁሉ ሐሳብ ከአእምሮው አስወግዶ፣ ስለ ስብሰባው ለማወቅ ፈለገ ። እስካሁንም ሲያመነታ ነበር ፣ ወደሱ ከመግባት ሌላ ሌላ ሐሳብ የሚያመጣው ። ምክንያቱም ባንድ ፊት ምን እንደ ተባለ እን


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

"ሁለተኛዉ እንካ ስላንቲያ መጀመሪያ ሰው እንምረጥ ወይስ ክፍሎቹን እንመድብ ነበር ። እዚህ ላይ አቶ ደርቤ ፣ ' ሰው ከመ መረጡ በፊት የክፍሎቹን ዐይነት ፣ ብዛትና ለእያንዳንዱ ክፍል የሚያስፈልገው ሰው ቁጥር ፣ ሊኖረው የሚገባው የትምህርት ደረ ጃና የሥራ ልምድ ፣ መወሰን አለባቸው ። ከዚያ በኋላ ፣ ይኽ ለዚህ ይመጥናል ተብሎ ሰው ሊመረጥ ይቻላል አሉ ።' ብቻ ምናለፋህ በመ ጨረሻ የአቶ ደፋባቸው ድምፅ አይሎ በሳቸው ሐሳብ መሠረት ቀጠልን . . . "

ከዚያ ጉብተው የተዘጋጀ ጠረጴዛ አጋጥሟቸው ተቀመጡ። የምግብ ዝርዝር ወረቀቱን አገላበጡ ። ተስፋዬ የሚፈልገውን ዱሮ ወስኗል ። ወረቀቱን የሚያየው ለልማድ ነው ። አሳላፊው እርሳስና ወረቀቱን ይዞ ቀረበ . . . . .

" ምን ልታዘዝ ? "

" ለኔ አንድ ሾርባ - ሚኒስትሮኒ - እና የጭቅና ጥብስ አምጣ ልኝ ። በኋላ ቡና እፈልጋለሁ " አለ ተስፋዬ ።

" ለኔም እንዲሁ ፤ ብቻ ሾርባውን ፣ የቲማቲም አድርግልኝ " አለ ብርሃኔ ።

" ምነው ያ ዘርፉ መጥቶ ቢሆን ኖሮ ! ይኸን የተጠበሰ እን ጉል ነበር የምጋብዘው ! " አለ ተስፋዬ ።

" ያልተጠበሰው አይሻልም ? " አለ ብርሃኔ ። አሳላፊው እየ ጻፈ ጆሮውን ጣል አርጎ የሚያወሩትንም ያዳምጥ ኖሮ ፣ ፈገግ አለ ። ጽፎ ከጨረሰ በኋላ ፣ "አንድ ሚኒስትሮኒ ፣ አንድ የቲማቲም ሾርባና ፣ ሁለት ጭቅናና ሁለት ቡና " አለ ።

" አዎ ። በል ፈጠን በል ! " አለው ተስፋዬ ፣ ኮስተር ባለ ድምፅ ።

ፊቱ በፈገግታ ሞልቶ የነበረው ልጅ ፣ ተስፋዬ እንዲህ ሲለው ፊቱ ወዲያው ቅጭም አለና ፣ ተስፋዬን አየት አርጎት የታዘዘውን ለማዘዝ ሔደ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ያለው እንዲቆይ ፣ መሻሻልንና ለውጥን የምንቃወም ፣ ዛሬ ማለቅ ያለበትን ይደር ፣ ይቆይ ባዮች ሆነን እንድንታይ አደረጉ ። ፍጹም ሥፍራ የተቀያየርን መሰለና ቋጭ አለ ። በመጨረሻ ሁላችንም 'አሜን' ብለን ተቀብለን መጣን ” አለ ብርሃኔ ፣ አንድ ነገር ግድ ረግ ተሰኖት ፣ ሁለት ዐይኑ ፈጥጠው እያዩ ፣ ረግረግ ውስጥ የሚሰጥም ሰው ስሜት እንደ ተሰማው ፣ ከፊቱ ላይ እየታየ ።

“ አይ ተስፍሽ ፣ አንድ የሚከራከርልሽ ሰው እንኳ አልነበረም ! ” ብሎ ተስፋዬ ፣ መሪር ሣቅ ሣቀ ።

“ እሱስ በመጠኑ እኔ ተከራክሬልህ ነበር ። ብቻ ደጋፊ ጠፋ።”

“ ዘርፉስ ? ዝም አለ ? ”

ብርሃኔ ዝም አለ ፣ የተጋባችውን የሾርባ ሣህን በዝግታ በማንኪያዋ እያንኳኳ ።

“ ምነው ? የምታሳጣው መስሎህ እንደሆነ ፣ አሁንም ቢሆን በዝምታህ አሳጥተኸዋል ። ይልቅስ ያደረገውን ንገረኝ ” አለ ተስፋዬ ።

ጥቂት ከተከዘ በኋላ ፣ “ እባክህ እኔ ሰው ቢቃኝ ። ዘርፉን ተወው” አለ ብርሃኔ ።

“ ንገረኝ ፣ ምን አለ ? ”

“ እሳቸውን ነበር የሚደግፈው እባክህ ። ከስብሰባው በፊት ያሉት ነገር አለ ። ጠዋት ከቢሯቸው ስገባ ፣ ያገኘሁት እሱን ብቻ ነበር ። ሰፋ ላይ ፊት ለፊት ቁጭ ብለው ሲያወሩ ነበር ። እኔ ስገባ ዝም አሉ ። እኔ ከገባሁ በኋላ እሳቸው ወጣ ብለው ነበር ። ያኔ ፣ ‘ እባክህን ትላንት የተባባልነው ነገር የሚሆን አልመሰለኝም ። ሰው ዬው ቆርጠዋል ። ስለዚህ ፣ እሱንም ላላድነው ዕድገቴንም እደና ቅፌ ከሁለቱም ሳልሆን እቀራለሁ ። እንደኔ ፣ አንተም ብትሆን ባት ቃወም መልካም ይመስለኛል ’ አለኝ ። እኔ ምንም ልለው አልቻል ኩም ። እሳቸውም ወዲያው ተመልሰው ገቡ ። ሌሎችም መጥተው ስብሰባው ተጀመረ እልሃለሁ ። ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ምክትል ጠቅላይ ሹም እንድትሆን አደርጋለሁ ብለውት ይሆናል ። ይኸ ወላዋይ ፣ በሁለት ቢላዋ በል ! "

ብርሃኔ ዝም አለ ።

" አልሰማኸውም ትናንት ፣ ' አንዳንዴ ወንድ ይውጣኝ ብዬ ነው ፣ ነግ በኔ ነው ' እያለ ሲወሻክት ። የታባቱ የሞት ! ! "

ብርሃኔ አሁንም ዝም አለ ።

" ዱሮውንስ እኔ ነኝ እንጂ፣ የማልረባ ከሱ ጋር መመሳጠሬ ! "

የብርሃኔ ዝምታ ቀጠለ ።

" የታባቱ ፣ የለማኝ ልጅ ! "

ብርሃኔ ጸጥ አለ ።

" ምክትል ጠቅላይ ሹም ቢያደርጉት ምን የሚሆን መሰለው። ከብትነቱ አይለቀው ! "

" ተስፋዬ ፣ ይኸ ሁሉ አሁን ምንም የሚለውጠው ነገር የለም። ስለዚህ ፣ የሚበጀውን ነገር ማድረግ ነው ። በኔ አስተያየት ያለህ ምርጫ ሁለት ነው ፤ ማለት ፣ ዝም ብለህ ገሙ ጉፋ መሔድ ፤ ካልፈ ለግህ ፣ አንድ ፣ መሥሪያ ቤቱን ለቀህ መውጣት ፤ ሁለት ፣ ጠቅ ላይ ሹሙ ዘንድ ራፖሩ ደርሶ ሳይወሰን ሔደህ በጠቅላይ - ሹም አከሉ ላይ አቤቱታ ማቅረብ ነው ። ከዚህ በፊት ግጭት እንዳደረ ጋችሁ ስለሚያውቁ ፣ ጠቅላይ - ሹም - አከሉ ስላንተ ሲያነሡባቸው ይጠነቀቃሉ " አለው ብርሃኔ ።

ተስፋዬ የብርሃኔን ምክር ጠንቅቆ አደመጠ ። የነገሩ አካሔድ ገባው . . . . ጭቅናው መጣ ። ሁለቱም ጸጥ ብለው ተያያዙት ። ከየግል ሐሳባቸው እየተጨዋወቱ ጭቅናቸውን ጨረሱ ።

" ከልብ ላመስግንህ ይገባኛል ። የኔን ጦር እንሥተህ ከመከራ ከርሀም በላይ ስለ ሰጠኸኝ ምክር " አለ ተስፋዬ ።

" አንተን ላመስግን እንጂ እኔ ፣ ስለ ግሩም ምሳህ " አለ ብር ሃኔ ፣ ፈገግ ብሎ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያወራ አገኘ ። ተስፋዬ ልዩ ጸሐፊዉን ግን እንደገባ ጠይቆ ፣ ማንም ለጊዜው እንዳልገባና፣ ከውጭ የሚመጣ ባለ ቀጠሮ እንዳለ ተረዳ። ተስፋዬ ከልዩ ጸሐፊዉ ቢሮ ወጣ ።

ተላላኪዉን እንዳላየ ሆኖ፣ አንኳኩቶ ጠቅላይ ሹሙ ቢሮ ዘው አለ ። ተላላኪዉ ፣ ወልደ ሥላሴ፣ አይቶ እንዳላየ ሆነ ። ተስፋዬ ቢሮ እንደ ገባ እጅ ነሣ ።

" እንደምን ዋልህ " አሉ ።

" እግዚአብሔር ይመስገን " ብሎ ፣ አሁንም እጅ ነሣ ። ዝም አሉ ።

" ጌታዬ ይፍቀዱልኝ ፣ ችግሬን ልናገር ። "

" ደግሞ ከማን ተጋጨኸ ? . . . ስምን ሞያ ሳያንስህ ጠባይ ህን ማሳመር አቃተህ ? " አሉት ጠቅላይ ሹሙ ።

" ጌታዬ ጉዳዬን ሳልናገር ፣ አስቀድመው በኔ ፈረዱብኝ !? "
" በል እሺ ፣ ልስማው ። "
" ጌታዬ ፣ እኔ የተከበሩ አቶ ድፋባቸውን — " ሲል አቋርጠው፣

" በቃ ። ይኸን መስማት አልፈልግም . . . የስንት የበላይህ የሆነውን ተንጠራርተህ ትጋሜለህ ? . . . አልሰማም " አሉ ቆርጥ ፣ ባለ ቃል ።

" አባቸው ናቸው እንጂ፣ እኔ የስንት የበታቾቻቸውን፣ ከከፍተኛ ቦታቸው ወርደው ሊተናኮሉኝ የሚጥሩ ። "

" በቃህ ፣ አልኩህ ። "

" ጌታዬ፣ የበላይ የበታቹን ሲከስና ሲቀጣ ' ይሁን ' የበታች ግን የበላዩ ሲበድለው 'ችሎ ይቀመጥ' ማለትዎ ከሆነ ፣ ይኸንኑ ማወቁ ብቻ፣ ለኔ በቂዬ ነው ። ለጌታዬ ሳላሰማ አንድ እርምጃ መውሰድ ጥሩ አልመሰለኝም ነበርና ነው ። ሆኖም ፣ ችግር እንዳለብኝ ፣ ዝርዝሩን ባይሰሙኝም ፣ ከዚህ ቀደምም ያውቃሉ ። ሰውዬዉ እኔን ለማጥፋት ታጥቀው ተነሥተዋል ። ይኸን ብቻ ይገንዘቡልኝ " ብሎ ቆኝ ጓሊት ዞሮ ወጣ ። በቁጥታ ወደ ቢሮው ሔደ . . . . . . ።



@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳያስበው ቀኝ እጁን ዘርግቶ ጠረጴዛው ላይ የነበረውን ግራ እጇዋን ዳሰሰው ። እጇዋ ቀዝቅዟል ።

" እጅሽ እንዴት ቀዝቅዟል ። በረደሽ እንዴ ? " አለ አጐናፍር ፥ ፀሐይዋ ቀኑን ሙሉ በርታ መዋልዋንና ፥ ሰዓቱም ለዘጠኝ ሐያ አምስት ጉዳይ መሆኑን ሳያስብበት ።

" ደኅና ነኝ ። አልበረደኝም " አለች ታፈረች ።

" ፈረንጆች ናቸው ወይስ የኛ ሰዎች ፡ 'አንድ ሰው እጁ ሲቀዘቅዝ ፥ ልቡ ሙቅ ነው ማለት ነው' የሚሉት ? " አለ ፈገግ እያለ ።

ዝም አለች ። ግር ብሎት እጇን ለበሰበ ። የቧ እዚያው ቀረ ። ልብ ሲል ጊዜ ፥ ለካ ክትፎ ሲበላበት ቅባት በነካው እጁ ነው ፥ የዳሰሳት ! እጇዋን ሲያይ የጁ ቅባት ቀብቷታል ። " ይቅርታ ። ቅባቱን ለቀለቅሁሽ አይደለም እንዴ ? " አለ አፈር ብሎ ።

" ምንም አይደለም " አለች ፡ በዚህ ቅር እንዳላላት ለማሳየት ፈገግ ብላ ።

" ምንም አልበላሽ ፤ አልጣፈጠሽም መሰለኝ ? "

" እሱስ ጥሩ ነው ። ብቻ . . . ወስፋቴ ተዘግቷል ። "

" ምነው ? " አለ ፡ ነገሩ ያልገባው መስሎ ፡ እና ከርቧ እንዲመጣ ።

" ይኸ ነገር መንፈሴን በጠበጠውና — " ብላ ቆመች ፥ ከልቧ እየተከዘች ።

" በውነቱ ፥ ዋናው ነገር እኛ የምናስበው ነው እንጂ ፥ የስምየለሽ ደብዳቤዎቹን ነገር እስከዚህ ልንጨነቅበት አይገባም " አለ አጐናፍር ፤ ነገሩን እስከዚህ ግልጽ ሳያደርግ ።

ታፈረች ግን ነገር ልቧ ገብቶ ስለ ነበር ፥ ያጐናፍርን ነገር ለመተንተን ጊዜ አልነበራትም ። ሆኖም ሰምታዋለች ። " አንድ ልነግርህ የሚገባኝ ነገር አለ ። ብዙ ዝብዝብ ይበዛዋል ። ግን ፍሬ ነገሩን እንድገልጥልህ ሕሊናዬ ያስገድደኛል " አለች ታፈረች ፤ መንፈሷ እየተጨነቀ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ እስከ ሰባት እዚህ ነበርኩ ” አለ አጐናፍር ፤ ተስፋዬን እን ደዚህ ያቁነጠነጠው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ የነበረው ጉጉት እጅግ ከፍ ያለ ቢሆንም ፤ እሱን ትቶ ፤ “ ቡና እንጠጣ ? ” ብሎ መጥ ሪያውን ደወለ ። ገብሬ ዘው አለ ።

“ ሁለት ቡና አምጣልን ” አለ አጐናፍር ።

“ የለም ። ለኔ አንድ ቀጭን ሻይ አምጣልኝ ” አለ ተስፋዬ።

ገብሬ ሊያመጣ ሲወጣ አጐናፍር የሚለው ጠፋው ። ተስ ፋዬ ጥቂት አሰብ ካደረገ በኋላ ፡ “ ሰሞኑን በመሥሪያ ቤታችን ሲዶለት የነበረውን ሁሉ ሰምተሃል ? ” አለው አጐናፍርን ።

“ ምን ልጂ ? ” አለ አጐናፍር ፤ አዲስ የሹም ሽር ወሬ ፤ መን ፈስ የጀመረ መስሎት ።

“ ምንም አልሰማህም ? ” አለ ተስፋዬ ፤ በመደነቅ ።

“ የለም ፤ ምንም አልሰማሁም ። ”

‘ ሰሞኑን ምን እንደ ተደገሰሰት ሳያውቅ ፤ ለፋሲካ ወደ ቁራ እንደሚነዳ በሬ ጊዜውን እየጠበቀ ቁጭ ብሏል ። ደግሞም ፤ ዛሬ ፊቱ ሁሉ አብርቷል ። አምሮበታል ፡ እንዳሰቡት በሬ ። አይ ሞኝ ! ’ ብሎ አዘነለት ። ተስፋዬ የበላይነት ስሜት ተሰማው ።

“ እንንግዲያው ልንገርህ ። ዛሬ ጠዋት የከፍተኛ ሹማም ንት ጉባዔ ተደርጐ አንድ ሰባት የሆኑ የመሥሪያ ቤታችን ዝቅተኛ ሹማምንት — ” ብሎ ዐረፍተ ነገሩን ሳይጨርስ ፤ አስነጠሰው ።

አጐናፍር በሆዱ ፤ “ እንዲሾሙ ተወሰነ ። ከነሱ ውስጥ አንዱ እኔ መሆኔ ነዋ ! ” ብሎ ደስ አለው ። ቃፈረኝ ገዶ ነች አለ ። ተስ ፋዬም ለምን እንደዚህ እንደ ፈለገው ገባው !

ተስፋዬ ደጋግሞ ካስነጠሰው በኋላ ፤ ከኪሱ መሐረብ አው ጥቶ አፍንጫውን አብሶ ፤ ወሬውን ለመቀጠል ሲያስላ ስልኩ ተደወለ ። ምክትል ጠቅላይ ሹሙ ናቸው ። አጐናፍርን ፤ ‘ ቢሮዬ ና ’



@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ራቸውን አላወቀችም ነበር ። የነገ ቀጠሮአቸው መኖሩንም አታውቅም ነበር ። ትሁንዘር በለጠን የምታውቀው ሁለቱም እንግሊዝ አገር ተማሪ የነበሩ ጊዜ ነበር ። በለጠንና ታፈረችን ያንለት ስትጋብዝ ለዳንስ ጨዋታው ሁለቱን በማቀናጀት አልነበረም ። እንዲያውም ያኔ እንግሊዝ አገር የነበሩ ጊዜ ፣ ትሁንዘር ራሷ ፣ እጅግ ጠብቆ የተጠበቀ ፣ እጅግ ርቆ የተቀበረ ፣ ዝንባሌ ነበራት — ወደ በለጠ ። ግን ፣ ብዙ ሳይቆይ ፣ ሳያድግ ያኔውኑ አዘያው ሞተ ። እንዷን ሌላ ሰው ፣ በለጠ ራሱ ፣ ዝንባሌዋ መኖሩን ልብ ማለት ቀርቶ ፣ አላለመውም ።

ስለዚህ ፣ የበለጠን ወሬ ለታፈረች ደውላ ስትነግራት ፣ ልክ እንድ ተራ ወሬ እንደምትነግራት ቈጥራው ነበር ። ታፈረችም ያንለት እሷ ቤት መተዋወቃቸውን እንደምታስታውስ ነግራት ፣ ትሁንዘርን ስለ አሟሟቱ ሁኔታ እንደ ዘበት ጠይቃት ነበር ። ትሁንዘርም ፣ ‘ የሴት ነገር አለበት ’ የሚባል ወሬ ጭምር የሰማች መሆኗን ገልጻላት ነበር ፣ ስልኩን የዘጋችው ።

ዜናዉ በታፈረች ላይ የፈጠረው ስሜት ፣ ትሁንዘር ከገመተችው የራቀ ነበር ። መጀመሪያ ፣ ‘ ሞት ’ የሚለውን ቃል ስትሰማ ፣ በውስጧ ያለፈ እንግዳ ስሜት ፣ በእሮይታ መሳ ለመሳ የተበረዘ ጣፋጭ ደስታ ነበር ። ግን ፣ አፍታ ሳይቆይ ፣ በቅጽበት እንደ መጣ በቅጽበት በነነ ። ጸጥ ብላ ብዙ ቆየች ። በመጨረሻም የበለጠ ሞት በሷና በእጕናፍር የወደፊት ግንኙነት ላይ ፣ ከፉ ጥላ እንደ ጣለበት አመነች ...


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስድስት

## ልክ በሳምንቱ

ቀኑ ቅዳሜ ፣ ሰዓቱ ስምንት ተኩል ግድም ነው ። አያሌ የመኪና ተከታይ አጅቦት ፣ በለጠ ደበላ የመጨረሻ ጉዞዉን ከጥቂት ሰዓታት በፊት የሴፍ ቅጥር ግቢ ፈጽሟል ። ሸኚዎቹ ሁሉ እዚያው ትተውት ሲመለሱ ፣ ብዙዎቹ አጐቱን ተከትለው ቤታቸው መጥተዋል ።

አሳዳጊ አጐቱ ንጋዴ ናቸው ። መጀመሪያ የበለጠን መንፈስ ለጥብቅና የቀሰቀሰውና ፣ የሕግ ትምህርትም እንዲማር መነሾ ምክንያት የሆነው ፣ የኚሁ ያጐቱ በርስትና በንግድ ሥራቸው ሳቢያ ፣ ዘወትር ፍርድ ቤት አስከትለውት መመላለስ ነበር ። ከእንግሊዝ አገር ተመልሶ ፣ የጥብቅና ቢሮ ከፍቶ ከነበረበት ጊዜ እንሥቶ ፣ ያጐቱ ባላጋራ ሁሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዘሩ እየጠፋ ፣ አጐቱ በሰላምና በጸጥታ የንግድ ሥራቸውን እስከ አሁን ቀጥለዋል ። ስለዚህ ፣ ‘ የኔ ጠበቃ የኔ ጋሻ ! የኔ መከታ . . . ’ እያሉ የሚያለቅሱት ይኸንኑ እያስታወሱ ነው እንጂ ፣ እንዲያውም በዘልማድና ለይስሙላ አይደለም ። ጠዋት በለጠን ሲሸኙ ፣ ሌላም አንድ ነገር በሐዘናቸው ውስጥ ጣልቃ ገብቶባቸው ነበር ። ይኸውም ፣ አስከሬኑን የተከተለውን የመኪና ብዛት አስተውለው ፣ እሳቸው ቀናቸው ደርሶ ሲሞቱ በለጠ በሕይወት ቢኖር ኖሮ ፣ እነዚህ ሁሉ ባለመኪናዎች ለበለጠ ሲሉ የርሳቸውን አስከሬን ያጅቡ እንደ ነበር አስበው መቆጨታቸው ነው ። ‘ ከእንግዲህማ ወዲያ ለማን ሲሉ እሬሳዬን ያጅባሉ ? በዕድርተኞቼ ብቻ ’ — ብለው በልባቸው በነገሩ ለቅጽበት እጅግ አዘኑ ። ሆኖም ፣ አባቱ በአርበኝነት ከሞቱበት ወቅት እንሥቶ ፣ በለጠን አባት ሆነው ያሳደጉት ከመሆኑም በላይ ፣ ወንድ ልጅ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ለምን በጉ በጉውን ትተሽ ከፉ ከፉውን ታስቢያለሽ ልጄ ?” አለ ከበደ ።

“ ጠርጥር ለከፉ ነገር አስቀድሞ መዘጋጀት ያስከፋል ? ”

“ ቢሆንም ፡ እንደዚህ አይባልም ። አሁን ሐዘን ላይ ሳሉ እን ደዚህ ማሰባችንን ቢያውቁ፡ በጣም ያዝኑብናል ። እኛም እነሱ እዝ ነውብን አይቀናንም ። ”

“ይልቅስ እኔ ሴት ከፍቼ ብነግድ ተኔ ጋር ሆነህ ታግዘኛለህ ?”

“ እሽከርሽ ፡ ባልሽ ወይስ ምንሽ ሆኖ ? ” አለ ፡ እነጋገሯ አስ ገርሞት ።

“ ባልነቱ ላይ እንኳን አትንጠራራ” አለች ብርቄ፡ አምልጧት!

ከበደ እጅግ ተናደደ ። “ ምን! ላንቺ አንሼሽ ? አንቺ ለኔ በዝ ተሽብኝ! በምን እኮ ! በጨዋ ልጅነት ? ” አለ ቆጣ ብሎ ።

ብርቄ ነገር መበላሸቱን ዐወቀች ። ለመጣላትና ከበደን ለማስ ቀየም አልፈለገችም ። “ እኔ እንደዚህ አልነበረም ያሰብኩት ፡ ያል ኩት ” አለች ።

“ኋላ ምንድር ነው ያሰብሽው ፡ ያልሽው ?” አለ ፡ ዐይኑን እያ ፈጠጠ ።

“ ግድየለም ይቅር ። እኔ ነኝ ጥፋተኛ ። ሆዱ ነገር አይጻጥር !

ተሰማ ወልደ ሥላሴን ይዞ መጣ ። ብርቄ በጣም ደስ ብሏት ተቀ በለቻቸው ።

“ ይኸው አምጥቼልሻለሁ ” አላት ወልደ ሥላሴ ፡ አንድ የተ ጣጠፈ ወረቀት ከኪሱ እያወጣ ። ብርቄ ፡ ከከፍኗ የሎተሪ ቲኬቶቿን ይዛ ፈጥና መጣች ። ወልደ ሥላሴ አንዱን ተቀብሎ ፡ እወረቀቱ ላይ ካሉት ቁጥሮች ጋር አስተያየው ። ካንደኛ እስከ ሦስተኛ አሸናፊ ዕጣዎች ማህል ቁጥሩ የለም ። ከዚያ የመጨረሻ ቁጥሩን እሁንጠ ረገዙ ውስጥ ካለው ጋር ማስተያየት ቀጠለ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

እየሠጋ ፡፡ "በሚቀጥለው ሙከራሽ ያለ ጥርጥር ይወጣልሻል" እያለ ወተወተ ፡፡

"አዎ ደስ ይበለኝ እንጂ! ይኸን ሁሉ ሳገኝ ፡፡ ለምን ደስ አይለኝም ፡፡ ይለኛል እንጂ!" አለች ብርቄ ዝግ ፤ ዝቅ ባለ ድምፅ—በምሬት ምፀት ፡፡ "ስንቱ መቶ ሁለት መቶ ብር እያወጣ ያንቺን ያህል እንኳ ሳያገኝ የሚቀር አለ" አለ ክበዶ ፡፡

ብርቄ ምንም መልስ አልሰጠችም ፡፡

"እሱስ ሺ ቤትም አውጥተው የከሠሩ ሞልተዋል" አለ ወልደ ሥላሴ ፡፡ አሁንም ብርቄ ዝም አለች ፡፡ አትሰማቸውም ፡፡

እጅግ መበሳጨቷን በመገንዘብ እነ ተሰማ ፤ 'ቃል የገባሽልንን ድርሻችንን አምጪ ፤ የገብሬልንም ድርሻውን ክፈይ' ብለው ሊቀልዱ አልፈለጉም ፡፡

"ለሞኑን የሚወጣው ሎተሪ አለ ?" አለች ብርቄ ፤ ሁሉንም ትታ ፡፡

"አዎ ፤ ጥምቀትን ምክንያት በማድረግ አንድ መደበኛ ያልሆነ ፤ ልዩ ሎተሪ ተዘጋጅቷል ፡፡ ባለመቶ ሺ ነው እረ!" አለ ወልደ ሥላሴ ፡፡ ግን ፤ 'ግፊ አትግፊ' ለማለት አልደፈረም ፡፡

"በቃ! ከሱ በዚህ ሁለት ብር ትኬት እገዛለሁ ፡፡ ከወጣ ወጣ፣ ካልወጣ ግን ፤ እኔ ብርቄ እርም ይሁንብኝ ሎተሪ ሁለተኛ አልገዛም" አለች ነገሯን ፤ ቁጥር አድርጋ ፡፡

"ወደፊት አትግዢ ግዴለም ፡፡ ግን አትማዪ ፡፡ መሐላ መጥፎ ነው!" አለ ተሰማ ፡፡

ብርቄ ግን በዐይኑ ሕሊናዋ ታያት ፤ ተሰማት ! እንዴት የኃጋሪ ደሞዟን እንደምታገኝ ፡፡ ጭስና የአከንባሎ እንፋሎት ዐይኗን ሲያሞጨሙጨው ፤ የሳቱ ወላፈን ቅልጥሟን ሲያቀልጠው ፤ የኃለ ምጣድ እጅዋን ሲጠብሰው ፤ የሳቱ ሙቀት መላ ሰውነቷን በላብ ሲያጥበው ፤ በዚያ ላይ ያንዳንድ እመቤቶች ስድብና ቁጣ ሰውነቷን ሲያሸማቅቀው ፤ እንጀቷን ሲያሳርረው ፡፡ ተሰማት ፤ ታያት ፤ ይኸ ሁሉ !



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

‘ ፍራንኩ እንደዚሀ ነው የሚገኘው ። ታዲያ ለምንድርነው ለማንም የምገብረው ? ’ አለች በሐሳቧ ። ለተሰማ ግን ድምፗን ከፍ አድርጋ ፣ “ አይ ተንግዲህ ወዲያ ‘ ቃሏን ሽራ ትገዛለች ’ ብለው ነው? ሽረ እኔ ገብርኤልን ! አልገዛም ” ብላ በተኮሳተረ ቃል መለሰች ።

“ እሱስ ይሁን — አትግገር ። ብቻ አትማይ ። የመሐላን ነገር እኔ ዐውቃለሁ ” አለ ተሰማ ። እንደዚሁ ሲከራከሩ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ፣ ዕጣን ተጨሶ ቡናው ተቀድቶ ይጠጣ ጀመር ።

ብርቱ ፣ በሐሳቧ አንድ ስታመነታበት የነበረን ነገር አሁን ወሰነች ። በሎተሪ በኩል ወደ እመቤትነት ሰገነት ለመውጣት የነበራት ተስፋ አሁን ጨርሶ ስለ ሞተ ፣ ወልደ ሥላሴን ለመታረቅ በሐሳቧ ወሰነች ። . . . . . . . . .


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሰባት

### አሑድ

ተስፋዬ በሌሊት ተነሥቷል ። እነ አበራ ስላልተነው ፤ ይቅበጠ በጣል ። እርግጥ ፤ እንደ ሌላው ጊዜ ቢሆን ፤ እሑድ እንደዚህ በጠዋት የሚነሣ የለም ። ቁርስም የሚበላው ወደ አራት ፤ አራት ተኩል ባይ ነው ። ‘ የዛሬው እሑድ እንደ ሌላው እሑድ ስላልሆነ ፤ እንቅልፍ ሊይ ዛቸው አይገባም ’ ባይ ነው ፤ ተስፋዬ ። ምክንያቱም ፤ በጠዋት በሰጠ አጐት ቤት ሔደው ፤ አብረዋቸው ተቀምጠው እንግዳ መቀበል አለ ባቸውና ። ተስማምተው ነበር ፤ በዚህ ።

እንደዚህ ሲንቆራጠጥ ፤ አኩል ሰዓት ያህል ከቆየ በኋላ ፤ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ግድም ሲሆን ፤ ተስፋዬ የአበራን በር አንኳኩቶ ፤ “ አቤ አቤ! ረፈደ እኮ ! ” አለ ፤ ድምፁን ጥቂት ከፍ አድርጎ ።

“ እእ ? ” የሚል ድምፅ መለሰለት ። ከዚያ የእንቅስቃሴ ድምፅ ተሰማው ።

“ ተነሥ ። ረፈደ ! ”
“ እሺ ። ስንት ነው ? ”
“ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ዐልፏል ። ረፍዷል ። ”
“ እሺ ። ተነሣሁ ” አለ አበራ ።

ከዚያ ፤ ተስፋዬ ወደ ወንድይራድ ሙሻታ ቤት በር ሔዶ ፤ እያን ንኳኳ ተጣራ ፤ ምንም መልስ አጣ ። አሁንም አንኳኳ ፤ ተጣራ ። ምንም ! ‘ እንዴት ዐይነት እንቅልፍ ነው የያዘው ’ አለና ፤ ድምፁንና ማንኳኳቱን ከፍ አድርጎ ፤ ሊቀሰቅሰው ሞከረ ። ግን የሚያገኘው መልስ ጸጥታ ብቻ ሆነ ! ጆሮዉን እበሩ ቁልፍ ማግቢያው ላይ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ብቻ ፣ እኔ እንጃ ባክሽ ። የማስበው መላቅጡ ጠፍቶኛል "
አለች ታፈረች ፣ ጥቂት ካመነታች በኋላ ፣ ከዘነመች ጋር በጉዳዩ ለመወያየት ወስና ። ግን ዝም ስላለች ፣

ዘነመች፣ " ለምን ዝም ብለሽ ካንዱ አትጀምሪም ? " አለቻት።

" የቱን ብዬ ከየት ልጀምር ? " አለች ፣ ለዘነመች ሳይሆን ለራሷ ።

" ከአጐናፍር ጋር ተጣላሽ ? " ብላ ጠየቀች፣ ዘነመች ።

" የለም፤ አልተጣላንም ። "

" ታዲያ ምንድር ነው እንዲህ ያስጨነቀሽ ? የበለጠ ሞት ነው ? "

" በከፊል ፡ አዎ ። "

" እንዴት ? " አለች ዘነመች ፣ ግራ መጋባት ፣ መደነቅና የማወቅ ጉጉት አንድነት በተዋሐዱበት ድምፅ ።

" የበለጠ መሞት ከአጐናፍር ሊያቆራርጠኝ ነው ። "

" አልገባኝም ። "

" ታስታውሺለሽ፡ እንትሁንዘር የኔን ከአሜሪካን አገር መመለስ ምክንያት በማድረግ እቤታቸው ያደረጉትን የራትና ዳንስ ግብዣ" ብላ ጠየቀች ዘነመችን ።

" አዎ ። የዛሬ ሦስት ነው አራት ሳምንት ? እኔ እንጃ ፣ በለጥኛቸውን' 'ታፈረች፣ በተመለሰች በስንት ዘመኗ ብያት ነበር። አዎ ፣ አስታውሳለሁ ። "

" እዚያ ግብዣ ላይ ነው በለጠን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ፣ ያወቅሁት ። ብዙ አወራን ፣ ብዙ ደነስን ። ብዙ ያናደደኝ ነገር ቢልም ቢያደርግም ፣ በመሠረቱ አስደሰተኝና ተቃጠርን ። የቀጠሮው ዕለት አደጋ አገኘው ። ከዚያ በኋላ ሁለተኛ ተቃጠርን ። በመካከሉ አጐናፍርን አገኘሁት ። በለጠም ትናንት በሁለተኛው ቀጠሮአችን ቀን ተቀበረ " ብላ ልትቀጥል ስትል ፣


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ታፈረች ለመሔድ ልቧ ቆመ ። ግን እውነተኛውን ምክንያት ዘነመች እንድታውቅባት አልፈለገችም ። ስለዚህ አቅማማች ።

ዘነመችም ይኽን ተገንዝባ ፤ “ በይ ባክሽ ቁጭ በይ ። ደግሞም የጀመርሺውንም ጨርሽልኝ ” አለች ።

“ ምን ብዬ ልጨርስልሽ ። አጐናፍርን ሲያቀብጠኝ ስለ በለጠ ጠይቄው ፤ ‘ አብሮ አደግ ጓደኛዬ ነው ’ አለኝ ” አለች ታፈረች ።

“ እንዴ ! ነገርኩት እንዳትይኝ ። ”

“ አይ ፤ አልነገርኩትም ። ካንዷት ጓደኛዬ ጋር ‘ ነገር ያለው ’ ነበር ፤ ያስመሰልኩት። ”

“ አልጠረጠረም ? ”

“ የለም ። ምንም አልጠረጠረም ። ”

“ እዬ ? ”

“ ሙች ! ” አለች ታፈረች ፤ እርግጠኛ ሆና ።

“ ያስገርማል ። ብዙዎቹ የኛ ወንዶች እንደዚህ አይደሉም ። ”

“ ያንለት እኔ ‘ከሌሎቹ የተለየ ነው ብልሽ’ አሻፈረኝ ፤ አልሰማም አላልሽም ? ” አለች ታፈረች ፤ ረታሁሽ በሚል ድምፅ ።

“ እኔ ፤ አሁንም ቢሆን አለመጠራጠሩን እጠራጠራለሁ ። ”

“ አይ አንቺ መቼም አትረቺም ። ይሁንና በበኩሌ ፤ በማናቸውም ነገር ቢሆን የሚያምነኝ ይመስለኛል ” አለች ታፈረች ።

“ መልአክ ፤ ጻድቅ ነው ማለት ነው—እንደዚህ ከሆነ ። ብቻ እንጃ ! ”

“ ምንም ሆነ ምን ለኔ ተስማምቶኝ ነበር ። ”

“ ‘ነበር’ ? ለምን ‘ነበር’ ? ”

“ በበለጠ ምክንያት ሳንለያይ አንቀርም ። ያ ዱርዬም ስምየለሽ ወረቀት እየጻፈ ያስቸግረኛል ። ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ስምንት

### የተረፈው ተገኘ

የበለጠ ሠልስቱ ስለ ነበረ ፣ የቅርብ ወዳጅና ዘመድ በሌሊት መቃብሩ ቦታ ደርሶ ተመልሷል ። አበራና ተስፋዬ ፣ ከሌሊቱ በዐሥራ አንድ ሰዓት ተነሥተው በቀጥታ መቃብሩ ቦታ ሔደው ነበር ፣ ከሌሎቹ የተቀላቀሉት ።

ዛሬ ሰኞ ነው ። ሦስት ሰዓት ሲሆን ሥራ መግባት አለባቸው። አንድ ቦታ ቆመው ቡና ለመጠጣት ወስነው ፣ ዝግ እያሉ ነድተው፣ ራስ ሆቴል ደረሱ ። እዚያ ገብተው የሚፈልጉትን አስመጡ ።

ከዚያ ተስፋዬ ተነሥቶ እቤት ደወለ ፣ ስለ ወንድይራድ ጉዳይ ሰው ደውሎ እንደሆነ ለመጠየቅ ።

ከበደ ፣ ካንድ ፖሊስ ጣቢያ የተደወለ መሆኑንና ፣ ‘ በፍጥነት እንድትመጡ ’ የሚል መልእክት እንዳለ ተናገረ ። ተስፋዬ ለአንድ ሁለት ጓደኞቻቸው ደውሎ ይኸንኑ ዜና ካስተላለፈ በኋላ ፣ አበራ ወዳለበት ክፍል ተመልሶ ነግሮት አብረው ተነሡ ።

ፖሊስ ጣቢያ ደርሰው ማን እንደሆኑ እንዳስታወቁ፣ ወደ አንድ ሙቅ እለቃ ዘንድ ተወሰዱ ። እሱም አበራ በላይና ተስፋዬ ሙሉነህ መሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ፣ አንድ ኤንቬሎፕ ቀደም ቀደም ለሚለው ለተስፋዬ ሰጠው ። ሁለቱም ገና እጅ ጽሕፈቱን ሲያዩ የወንድይራድ መሆኑን ተገንዝበዋል ። ከመደንገጡ የተነሣ ፣ ተስፋዬ ኤንቬሎፑን በደንብ መክፈት አቅቶት ፣ በሚንቀጠቀጥ እጅ እንዳይሆን አድርጎ ሸረከተው ። እውስጡ ያለውን ወረቀት አውጥቶ ፣ ሁለቱም



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

መርምሮ ጠይቆ ፣ ዐውቆ ፣ ወዶ አልመጣ ። ከመጣ በኋላ አላለቅም አልሑድም እምቢ አሻፈረኝ የሚልበትስ ?

" በተስይ አበራ ታስታውሰው ይሆናል ። ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የነበርን ጊዜ ለግጥም ውድድር የተነበበልንን ። የዊሊያም ሼክስ ፒር ፍጡር ፣ ሐምሌት መስፍን ዴንማርክ ያለውን ያነበበ አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት የገጠመውን ፣

'መኖር አለመኖር
ጥያቄው ይኸ ነው' ብሏል ሼክስፒር ።
ምነው ባገኘሁት እነግረው ነበር ፤
ካለመኖር መኖር ሳይሻል አይቀርም ፣
ከመኖር ተስፋ አለ ፣ ካለመኖር ምንም ።

" ጥንታዊ ገጣሚ ቢሆን ግን ይኸንኑ ጉዳይ በሌላ መንጽር ነበር የሚመለከተው ። ምን አልባት እሱ ቢሆን እንዲህ ብሎ ይገጥም ይሆናል ።

'መኖር አለመኖር ፣
ይኸ ነው ጥያቄው ብሏል ሼክስፒር ።
ወየው ባገኘሁት እነግረው ነበር ፣
ካለመኖር መኖር ጨርሶ አይሻልም ፣
ጣር አለ ከመኖር ፣ ካለመኖር ምንም ።'

" የሁለቱም መሠረታዊ ነገር ያው ነው ። ተስፋ ። የምን ተስፋ? ሀብታም ለመሆን ፣ ትልቅ ለመሆን ፣ ትልቅ ነገር ለመሥራት ?— ሀብታም ለመሆን አለበት ። ጣር ። የምን ጣር ? ሀብታም ለመሆን ፣ ትልቅ ለመ ሆን ፣ ትልቅ ለመሥራት ከሚደረገው ትግል የሚመነጭ ? — ነውና ። ሁሉም ይሁን ። ግን ለምን ?

" ሀብታም ተሆኖስ ? ትልቅ ተሆኖስ ? ትልቅ ሥራ ተሠርቶስ? ከዚያ በኋላ ፣ ምን ? አብዛኛው ሰው እነዚህን ሁሉ እስኪያደርግ ሞት ስለሚቀድመው ፣ ጥያቄው ትርጕም የለውም ፣ ወይም አለ ቦታ ውና አለጊዜው ነው የተጠየቀው ይባል ይሆናል ። ግን እዚህ 'እሁ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ያውኑ ያወቁ ከነተሰፋዩ ሌላ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ቢሆኑ ነው ። ከሰሙት አንዱ አጐናፍር ነው ።

እነሆ የወንዶች ገናን ፣ አበራ እንደበቱ ተዘግቶ ፣ ተሰፋዩና የቀ ሩት ጓደኞቻቸው በበለጠና በወንድይራድ ኃዘን ተከማትረው አሳ ለፉት ።

*     *     *

ታፈረች እቢሮዋ ቁጭ ብላ አንድ ፋይል ለማንበብ ትሞክ ራለች ። የሚሆንላት አልሆነም ። ቀልቧን ሰብስባ ሥራዋን ለመ ሥራት የምታደርገው ሙከራ እስካሁን ምንም ውጤት አላስገኘም።

አጐናፍርን ፣ ከዓርብለት ወዲህ አላገኘችውም ። አልደወለላ ትምም ። ዛሬ ሥራ ይገባል ብላ ስለ ገመተች ፣ 'ይደውልልኛልም ' ብላ አስባ ነበር ። ነገር ግን እስካሁን አልደወለም ። ልቧ ቢከጅልም ፣ እሷም አልደወለችለትም ።

የምታደርገው ቅጡ ጠፍቷት ቁጭ እንዳለች ወደ ስድስት ሰዓት ላይ ስልኩ ተንቃጨለ ። ጥቂት ልቧ እንደ መሸበር እያለ ፣ ስልኩን አንሥታ ፣ " ሃሎ ? " አለች የሚጠይቅ በሚመስል ድምፅ ።

" ዘኔ እንደምን ዋልሽ . . . የበለጠ ጓደኛ ? ማን የሚባለው ? . . . አላውቀውም . . . የለም አልሔደም . . . የምን ጉድ ደግሞ ? "

ከዚያ ዝም ብላ ታዳምጥ ጀመር ። ፊቷ እየተቀየረ ሔደ ። ፍር ሃት ዐይኖቿን ሞላው . . . . . . . .


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዘጠኝ

### የሁለተኛዉ ሠልስት ዕለት

ካመት በዓል ቀጥሎ የሚውል የሥራ ቀን ፣ ‘ የሥራ ቀን ፣ ’ ሊባል አይገባም ። ምክንያቱም ፣ በዚህ ቀን አያሌ ሰዎች ልዩ ልዩ ሰበብ ከሥራቸው ያስቀራቸዋልና ነው ። በርትተው ቢሮ የሚደርሱትም የመሥራት ፍላጐት ስለማይዛቸው እንድ ፋይዳ አይሠሩም ።

ቢሆንም ፣ አንዳንድ የሥራ ጊዜዉን ለማስታጐል ሕሊናው እሺ የማይለው ፣ ወይም ጊዜ የሚያሳልፍበት ሌላ ከቢሮ የተሻለ ሥፍራ የሌለው ፣ ወይም የቢሮን ውስጥ መመሳጠርና የነገር ጦር ነት የሕይወቱ ግብ ያደረገ ፣ በማናቸውም ቀላል ሰበብ ከቢሮው አይ ቀርም ። ለዚህ ሰው ፣ የመሥሪያ ቤቱ ማኅተም ያዥ በመቅረቱ ደብዳቤዉ ወይም ማዘዣው ወጪ ለመሆን ባይችል ፣ ወይም ጸሐፊ ወይ መዝጋቢ ባለመኖሩ ነገሩ ውሎ ቢያድር ፣ ቁም ነገሩ አይ ደለም ። ዋናው ነገር እቢሮ በሰዓቱ መገኘቱ ነው እንጂ ፣ ቢሮ ከተ ደረሰ በኋላ የሚሠራ መኖር አለመኖሩ አይደለም ።

የዛሬው የገና ማግሥት ፣ ያው እንደ ሌሎች ዓመት ባሎች ማግ ሥት ነው ። ከትናንቱ ገና በዓል ጋር ‘ ጨርሶ አልተያያዙም ’ በሚባሉ ሰበቦች ፣ አያሌ ሰዎች ሥራ ለመግባት ሳይችሉ ቀርተዋል ። ቢሆንም በሥራ ገበታቸው ላይ የተገኙ ብዙ አልታጡም ። ትናንት የገና በዓል በመሆኑ ፣ ሳምንታዊዉ ፣ የማክሰኞ ፣ የጠቅላይ ‘ ሹማምንት ጉባዔ ለዛሬ ተዛውሮአል ’ ተብሎ ባለፈው ሳምንት ተነግሮ ነበር ። ዳሩ ግን ፣ እንደገና ወደ ዓርብ ‘ ተዛውሯል ’ ስለ ተባለ ፣ የተከበሩ ጠቅላይ ሸሙ ቀጥታ ቢሯቸው መጥተዋል ። ጠቅላይ - ሹም - አከሉ ፣ አቶ ደፋባቸውም በዚህ አጋጣሚ በጣም ተደስተው ፣ በዛሬዋ ጀንበር የተከፋዩትና የአጕናፍርን ዕድል ለማስወሰን እጅግ ቸኩለዋል ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

መጡለት ፣ ሳይንሾካሾኩበት አሳለፉትም ። እሱም ይኸን ሁሉ ተገንዝቧል ። ደግሞም እንደማይቀርለት ዱሮውንም ዐውቆታል ። ስለዚህ በተቻለው መጠን አይቶ እንዳላየ ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ አስመሰለ።

አቢሮው ሲደርስም፣ ከወትሮው የላቀ ትሕትናና መሽቆጥቆጥ ከተላላኪዉ እስከ ጸሐፊዉ ጠበቀው ። ቢሮው ገብቶ ተቀረቀረ ። ሰዓቱን ቢመለከት ስድስት ሰዓት ተኩል ሆልፏል ። አጉናፍር ቢሮ መሔድ ታሰበው ። ስልክ ደውሎ መኖሩን ለማረጋገጥም መጀመሪያ ቃጥቶ ነበር ። በኋላ ግን ሳይደውል ዝም ብሎ ለመሔድ ወስኖ ፣ ተነሥቶ ወጣ ።

አጉናፍር ቢሮ ሲደርስ አጉናፍር መውጣቱን ገብሬ በትልቅ ትሕትና ነገረው ። ተሰፋዬ እንደገና ወደ ቢሮዉ አመራ ። ቢሮዉ ገብቶ ምንም ያህል ሳይቆይ ብርሃኔ በችኮላ ዘው አለ ።

" እንዷን - " አለና ብርሃኔ ባጭር ቆመ ። ተሰፋዬን ቅዝቅዝ፣ ጭር ፣ ጉስቁልቁል ብሎ አየው ። ስለዚህ " እንደምን ዋልክ ?" አለና ዝግ ብሎ ሔዶ ጨበጠው ።

" ቢሮህ መጥቼ ነበር " አለ ተሰፋዬ በዝግታ ።

" አዎ ፣ አልነበርኩም ። ዘርፉ ዘንድ ነበርኩ " አለ ብርሃኔ።

" ዛሬ ደግሞ ምን ይቀሳፍታል ? " አለ ተሰፋዬ ፣ አስተያየት በመሰንዘርና ጥያቄ በመጠየቅ ማህል ድምፁን እንጠልጥሎ ።

" ምክትል ጠቅላይ ሹም በቅርቡ ሊሆን ነው የሚባል ወሬ ሰሞኑን መወራት ስለ ጀመረ ደስ ብሎታል ። "

ዝም አለ ተሰፋዬ ።

" ብቻ እንደምታውቀው ፣ በወሬውና በፍጻሜው ማኸል ያለው ርቀት ረዘም ያለ ነው ። "

" ይኸኔ የወሬው ምንጭ እሱ ራሱ ይሆናል " አለ ተሰፋዬ ፣ አሁንም ለዘብ ባለ ድምፅ ። የንገሩን እውነትነትና ሐሰትነት ለማወቅ ደንታ አልነበረውም ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ ዋናው ነገር—ትልቁ ወሬ—አንተን ጠቅላይ ሹሙ ከገሙ ጉፋ አስቀሩህ አሉ ! ” አለ ብርሃኔ ፣ ደስ ደስ እያለው ።

“ ለምን ? ” አለ ተስፋዬ ፣ በውሳኔው አለመደሰቱን በሚያጋልጥ አነጋገር ።

“ ‘ለምን ! ? ’” አለ ብርሃኔ ፣ በመደነቅ ተስፋዬን ትኩር ብሎ እያየ ።

“ አዎን ፣ ለምን? ” አለ ተስፋዬ ደግሞ ።

“ ለምንስ ቢሆን አንተ ምን ቸገረህ ። ዋናው ነገር ውሳኔው ላንተ የሚበጅ መሆኑ ነው እንጂ ” አለ ብርሃኔ ፣ የተስፋዬ ሁኔታ የባሰውን ግራ እያጋባው ።

“ ለመሆኑ መቼ ነው ይኸ የተወሰነው ? ”

“ ዛሬ ጠዋት ። ”

“ ማን ነገረህ ? ”

“ ዘርፉ ። ”

“ የሱን ወሬ ይዘህ ነው ? ”

“ ነገሩ እርግጥ ነው ። ምንጩ ከልዩ ጽሕፈት ቤት ነው ። ”

“ የተከበሩ አቶ ድፋባቸው ምን አሉ ታዲያ ? ” አለ ፣ ለማወቅ የጓጓ መስሎ ።

“ ጨሰዋል አሉ ። የሚያስደንቅ ነው ። ስብሰባው የፈጀው አንድ ሰዓት ያህል ብቻ ነው ። እጅግ ቀለጠፈ ” አለ ብርሃኔ ፣ በመደነቅ ።

“ ደግ አርገዋል ። የወሬው ሰዓት ዐልፏል ” አለ ተስፋዬ ፣ እሁንም መንፈሱ በዚህ ጉዳይ አልሟሟቅ ብሎ ።

“ በነገራችን ላይ ፣ አጐናፍርም እንዳይዛወር ተወስኗል አሉ” አለ ብርሃኔ ።

እዚህ ላይ ተስፋዬ ሐሳቡ ተቀሰቀሰ ። በአካባቢው ስለሚሆነው ነገር የመገንዘብ ፍላጐቱ ተመለሰ ። “ እንዴት ነው ጠቅላይ ሹሙ የወሰኑት ? እንዲያው ዝም ብለው ነው ወይስ ከሌሎቹ ጋር ተመ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ገራችን ፣ የውጭ አገር ጐብኝዎች ከኛ የበለጠ ያውቃሉ ። የብዙ ዎቹን ቦታዎች ስማቸውን ብቻ ነው እኛ የምናቀው ። ማለቴ ከሰ ደሬና ከአምቦ በቀር ! ! ” አለ ተስፋዬ ፤ ማጥቃቱን እየቀጠለ ።

“ ነው ። እርግጥ ነው ። ካልከስ ካገራችን የበለጠ ስለ ባዕድ አገሮች እናውቃለን ። ብቻ ፣ ሁላችንም ገጠር ገብተን ከተማው ባዶ እንዳይቀርም ማሰብ ይገባል ! ” አለ አጐናፍር ፤ ነገሩን ወደ ዋዛ ፈዛዛ ለመለወጥ ።

“ ምናለ ፣ ከተሜዉ ገጠር ሲገባ ፣ ገጠሬዉ ደግሞ ፣ ከተማ ይተ ካላ ! ”

ሁለቱም ነገሩ ቸካቸው ። አጐናፍር ፣ ‘ ተስፋዬ መቼ ሔዶልኝ ስለ ሰማሁት ነገር ከሐሳቢ ጋር ብቻዬን በቀረሁ ’ ብሎ ሲመኝ ፣ ተስፋዬ ዝምታ ሲበዛ ጊዜ በሳምታ ሰጥቶት ወጣ ።

ተስፋዬ ከሔደ በኋላ ፣ አጐናፍር ስለ አበራ ሁኔታ ሳይጠይቀው በመቅረቱ ጥቂት ጸጸተው ። እቢሮው ደውሎ ሊጠይቀው ወሰነ። ስልክ ስለ መደወል ሲያስብ ታፈረች ትዝ አለችው ። ሁለመናው በደስታ ፈካ ። ብሩህ ገጿ ሳይና ’ ምሮዉ ታየው ። ልቡም ፣ ‘ ደው ልላት ! ደውልላት ! ’ አለው ።

ስልኩን እነሣውና ደወለ ። ኦፕሬተሯን ታፈረችን ጠየቃት። ‘ ስልኩ ተይዟል ትጠብቃለህ ወይ ? ’ ተባለ ። ‘ እጠብቃለሁ ’ አለ ። ስልኩ ወዲያው ተለቀቀ ፣ “ ሀሎ ” አለ ።

“ መቼ ? አሁን ? . . . ታዲያ ለምን ተውሺው ፣ አትደውይም ኖሯል ? . . . ”

“ እዬ ገብቶኛል ! ! ” . . .
“ ታዲያ ሥራው እንደምን ያረግሻል ? ” . . .
“ መልካም ። መልካም ። ” . . .

“ ዛሬ ይዞልኛል ባከሽ ። ‘ ባሴ መሔዴም ቀረ ’ ብሎ አንድ ሰው አሁን መጥቶ ነገረኝ ” አለ አጐናፍር ፣ ስለዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ይንገራት አይንገራት እርግጠኛ ሳይሆን ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

የከ በር አፋፍ ላይ ሲደርስ ከመንገዱ በቀኝ በኩል መኪና ውን አውጥቶ አቆመ ። ከኋላቸው ጀንበሯ ጠልቃ ሰማዩ ደም ለብ ሷል ። ነገር ግን ፣ ከፊታቸው ያለውን ቁልቁለት ፣ ለጥቆት ያለውን ጅረት ፣ ባሻገር ያለው ዳገት ላይ ያለውን ቤተ ክርስቲያን ለማሳየት ያህል በቂ ብርሃን አለ ።

ሞተሩን ለጠፋ ። ወሬዉና ማቋም አልቻለ ። በቦ ው በጣም የከረረ ጸጥታ ተተክቷል ። ሲፈራ ሲቸር ወደ ታፈረች አንገቱን አዙሮ ዐይኖቹን ገጿ ላይ አሳረፋቸው ። ወደ ማይ ፈገዘ ትመለከ ታለች ። ዐይኖቹ ገሚስ ገጿ ላይ ሲንከራተቱ ሰምቷት እሷም ፣ ስት ፈራ ስትቸር ፣ ዐይኖቿን ወደ አጕናፍር መለሰች ። ሁለቱም ፍርስ አሉ ። ታፈረች አንገቷን አቀረቀረች ። አጕናፍር ጠጋ ብሎ ቀኝ መዳፉን አሳልፎ በቀኝ ትከሻዋ ላይ አኖረ ። ዝግ ብሎ የበሰለ ትር ንጕ ጉንጯን በከንፈሮቹ ዳሰሰ ። ተሸሽጕ የሚመለከት ቢኖር ፣ አድ ራጕቱ ሥጋ የለበሰችን ሴት ጉንጭ ሳይሆን ፣ የአንድ ጻድቅን ሥዕል የሚስም ሃይማኖተኛ አድራጕት በመሰለው ነበር . . . .

ታፈረችና አጕናፍር አንድ ቃል ሳይተነፍሱ ፣ ሐተታ ሳያ በዙ ፣ በከንፈራቸው የየልባቸውን ምሥጢር ተወያዩ ። በማኽላቸው የነበረው ተራራ ተደርምሶ ፣ ልቦቻቸው ፣ አንድ ሆኑ ።

የጠለቀችው ጀንበር በጋራው ጀርባ ላይ እየተንሸራተተች ርቃ ስለ ወረደች ፣ ደም ለብሶ የነበረው ሰማይ ከኋላቸው ጠቆረ ። አጕናፍርንና ታፈረችን እመኪናው ውስጥ ጨለማ ዋጣቸው ። ከፊታቸው በነበረው ቁልቁለት ፣ ለጥቆት በነበረው ጅረትና ባሻ ገር ይታይ በነበረው ቤተ ክርስቲያን ሥፍራም ፣ ጥቁር አልቦ ገባ በት ። ከውጭ ጭለማ ፣ ከውስጥ ሙሉ ጸጥታ ሠፈነ . . . . . . .


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ዐሥር

## የፍጻሜው ዋዜማ

ተስፋዬ ባሬ ከወትሮው የበለጠ በጥንቃቄ ለብሷል ። ከጥቁር ክራባቱና ካልተላጨው ጺሙ በስተቀር ፣ ወደ ሠርግ ለመሔድ የተ ዘጋጀ ሰው ነው የሚመስለው ። ጠቅላይ ሸሙን ለማነጋገር ቀጠሮ ተቀብሎ የሰዓቱን መድረስ እቢሮው ሆኖ ይጠብቃል ። ከጥቂት ጊዜ በፊት ዘርፉ መጥቶ እንደ ዱሮው ለማውጋት ሞክሮ ነበር ። ነገር ግን ፣ የተስፋዬ ሁኔታ አሉባልታውን ባጭር ቆርጦ እንዲሔድ አድርጎት ፣ ተመልሶ ሔዷል ።

ተስፋዬ ዘርፉን በፊት ጠቃሚ የወሬ ምንጭ አድርጎ ይቆጥረው ስለ ነበር ፣ ሮው ለዘርፉ ዘወትር ክፍት ነበር ። አሁን ግን ፣ በሞ ኑን በደረሰው ነገር ሳቢያ ዘርፉን ከመጥላቱም በላይ ፣ በመሥሪያ ቤቱ ስለሚሆነው ልዩ ልዩ መሩተግ ለማወቅ የነበረው ፍላጎት ሁሉ ጨርሶ ሞቷል ። ስለዚህ ፣ ዘርፉ ቢመጣ ቢቀር ጨርሶ ደንታ የለውም . . .

የጠቅላይ ሹሙ ልዩ ጸሐፊ ደወለ . . . ተስፋዬ ወደ ጠቅላይ ሹሙ ቢሮ ሔደ ። እቢሯቸው ያለው እንግዳ እስኪወጣ ጥቂት ጠብቆ ገባ ። ጠቅላይ ሹሙ ከጠረጴዛቸው ኋላ ቆመው አገኛቸው ። እጅ ነሣ ።

“ ቁጭ በል ” አሉት ትኩር ብለው እያዩት ። ሁኔታውን ያጠኑታል ። እሳቸው እንደ ቆሙ ስለነበሩ ተስፋዬ ፣ ‘ እሺ ’ ቢልም አልተቀ ጠም ። ዝም ብሎ ቆመ ፣ ነገሩን እንዴት እንደ ሚጀምር እያሰላሰለ ። ጠቅላይ ሹሙ ወንበራቸውን ሳብ አድር ገው ተቀምጠው ተ ቻቹ ። ተስፋዬም ተቀመጠ ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

“ በረታህ ? ”

“ አዎ ። ምንም አልል ። ”

“ ለምን ፈቃድ አልወሰድከም ነበር ? ”

“ ምንም አይረባኝ ብዬ ነው ፤ አስቤበትስ ነበር ” አለ ተስፋዬ ። ዝም ብለው ይመለከቱት ጀመር ።

“ አሁን የምጠይቀውን ቢፈቅዱልኝ ከዕረፍቱ የበለጠ ይበጀኛል ። ”

“ ምንድር ነው የምትፈልገው ? ”

“ ጠቅላይ ግዛት እንዲመድቡኝ ነው ፤ እፈቀዱበት ጠቅላይ ግዛት ። ”

እጥንቅሳቱ ውስጥ ያለውን በቅጡ ለማየት እንደሚያስችላቸው ሁሉ ፤ ዐይናቸውን አከርረው ፊቱን ተመለከቱት ። ፊታቸውን መደነቅም ፤ ግራ መጋባትም አለበሰው ። “ ለምንድር ነው መዛወር የመረጥኸው ? ” አሉት ፤ ዐይናቸውን ከፊቱ ላይ ሳይነቅሉ ።

“ አገሬን የበለጠ ለማገልገል ” አለ ፤ እንደ ውዳሴ ማርያም እንደበቱ ሲደግመው የኖረውን ነገር ።

“ አገርህን የበለጠ የምታገለግልበትን ቦታ መርጦ መመደብ የአለቆችህ ፈንታ አይመስልህም ? የሠራተኞችንና የበታች ሹማምንትን ችሎታ መገዘና ፤ ሥራውን ማከፋፈል የበላይ ሹማምንት ተግባር ነው እኮ ” አሉ ጠቅላይ ሹሙ ።

ተስፋዬ ፤ ‘ በንርሱስ ቢሆን ተመድቤ አልነበረም ? ’ ሲል ቃጥቶት ነበር ። ዳሩ ግን ፤ አንደኛ ፤ ለዝውውር መቃጨትህን ማን ነገረህ ? ’ ሊያሰኝ ስለሚችል ፤ ሁለተኛ ደግሞ ፤ ለመሥሪያ ቤቱ የሁሉም የበላይ ሹም ስለሆኑ ፤ የሚቀርብላቸውን ሐሳብ ለመቀበልና ላለመቀበል መብትና ሥልጣን እንዳላቸውና ፤ ከበታች ሹም የቀረበውን አለመቀበላቸውን በምሥጢርም ቢሆን ማወቁን በመገንዘብ ፤ ነገሩን ተወው ። ዝም አለ ።

“ በልክ መልስልኝ ፤ ነው አይደለም ? ”



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ደብዳቤዉን ሲመልስለት ፤ “ እንኳን ደስ ያለህ ” ብሎ ጨበጠው ። አንጐናፍር ለጊዜው የሚለው ቃል ጠፋው ። የሱ ዕድገት ከተስፋዬ ስደት ጋር መተሳሰሩ ተሰማው ። ሆኖም ተስፋዬ ፈቅዶ ከመሔዱም በላይ ፤ እሱም ባይሆን ሌላ ሰው መተካቱ የማይቀር መሆኑን አልዘነጋውም ። ቢሆንም ጥቂት አሳሰበው ።

“ ቀስፍሽ ያሰበው ቴፈጸመሉት ፤ ” አለ አበራ ።

“ እሱ ገሙ ጐፋን ምን አስወደደው ? ምክንያቱን ገልጾልሃል ? ” ካለ በኋላ ፤ ቅድም እንደ ተረዳው ፤ ለካ ተስፋዬ መሔዱን የወሰነው እሱ ራሱ መሆኑን ነው ፣ ገልጾ ለአበራ እንዳልነገረው ትዝ አለው ። እንደ ካፍ አምልጦ ከውጣ እይመለስምና አንጐናፍር አፍሮ ዝም አለ ።

“ አይ ምንም አልነገረኝ ። እንዲያው በደፈናው ገሙ ጐፋ መሔዱን ነገረኝ እንጂ እሱ ራሱ ጠይቆ እንኳ መሆኑን አልነገረኝም ነበር ። እኔም ያው እንዳቀዱት አዛወሩት አልኩ እንጂ በነገሩ ብዙም አላሰብኩበት ” አለ አበራ ። “ እሱቱ እንዳለ ልደውልለት ” አለና ወደ ስልኩ ሔደ ።

“ ሃሎ ተስፋዬ ። . . .
“ የለም ። አንጐናፍር ቢሮ ነው ያለሁት ። ” . . .
“ ለምን ብቅ አትልም ። . . .
“ እሺ ። ” . . .

“ እኔ ባንተው ጋ አልፋለሁ እንግዲያው ” አለውና ስልኩን ዘጋ ። ተስፋዬ አንጐናፍር ቢሮ አለመጣም ያለበትን ምክንያት ራሱ ይጠረጥር እንጂ ፤ አበራ ለአንጐናፍር አልነገረውም ።

ተሰነባብተው አበራ ወደ ተስፋዬ ቢሮ አመራ ። ተስፋዬ ወደ ገሙ ጐፋ መዛወሩን የሚያስታውቀው ደብዳቤ ከጠቅላይ - ሹም - አከሉ ደርሶታል ። ይኸኔ በደስታ ይጨፍራሉ ብሎ ልቡ ተቃጥሏል። ‘ እኔ ፈልጌ መዛወሬን ማወቅ አለባቸው ፤ በርሳቸው ምክንያት አለመሆኑን እንዲረዱት ያስፈልጋል ’ ይላል በልቡ ።

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

አበራ ሲገባ ወንበሩ ላይ ተለጥጦ ተቀምጦ ፤ እግሮቹን አነባብሮ አጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ አገኘው ። ሳይነግ ኖሮ አለው ፣ ማስቲካውን እያኘከ ።

“ አንተ ጨርሶ ስሜት አልሰጠህም ፤ እ ? ” አለ አበራ ።

“ ምኑ ? ”

“ ዝውውሩ ! ”

“ ለመመነን የቆረጠ እንደዚህ ዐይነት ጥቃቅን ነገር ምን ስሜት ይሰጠዋል ብለህ ነው ። ቦታዬን የሚረከበው ያ አድርባይ ሞልፋጣ በመሆኑ ጥቂት ቅር ብሎኝ ነበር ። በኋላ ግን ሳስበው ፤ እኛ ከይሲ ሰውዬ ለቦታዬ ያጨኑት ገልጃጃ ከሚሆን ይኸኛው የሚሻል መስሎ ታየኝ ። ሌላው ቢቀር ሰውቀት እያንሰውም” አለ ተሰፋዬ ።

“ ምርጫዉ ከሞልፋጣና ከገልጃጃ ቸሯላ ! ” አለ አበራ በፌዝ። “ ባንተ አስተያየት ሞልፋጣ ተሽሎ ተገኘ . . . ታውቃለህ ፤ ተስፋዬ አንተ ሰው ስትጠላ ያስጠን ዋጋ ሁሉ ትንፍገዋለህ ። ጥሩ አይመስለኝም ። ”

“ እባክህ ለዋጋቢስ ዋጋ አልሰጥም ፤ እኔ ተስፋዬ ። እኔ ሁል ጊዜ የምጠላው አንድ ሰው የማይረባ ሲሆን ብቻ ነው ። ከሌላው ጠብ የለኝም ” አለና እግሮቹን ከጠረጴዛው ላይ አውርዶ ተነሣ ።

“ በነገራችን ላይ ፤ ገሙ ጉሩፉ እነሱ ናቸው የሚልኩኝ ለምን አልከኝ ? ” ብሎ አበራ ጠየቀው ።

“ ‘እነሱ ናቸው’ አላልኩም ። እርግጥ ፤ ‘እኔ ፤ ነኝም’ አላልኩም። እኔ ያልኩት በደፈናው ነበር ። ‘ገሙ ጉሩፉ መሐዴ ተወሰነ’ አልኩ እንጂ ፤ ማን ጠይቆ ማን እንደ ወሰነው የገለጽኩ አልመሰለኝም ” አለ ተሰፋዬ ።

“ ቢሆንም አንተ ፈልገህ መጠየቅህን ልትነግረኝ ይገባ ነበር” አለ አበራ ።

“ እዎ ። ውንትህን ነው ። ለምን እንዳላብራራሁት አላውቅም” አለ ተስፋዬ ። “ ምነው ፤ ልዩነት ያመጣ ኑሯል ? ” ብሎ አበራን ጠየቀው ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

« እሺ » አለችና ከቦርሳዋ ቁልፏን እያወጣች ወደ መኪናዋ አመራች ። አጐናፍርም ሸኛት ። ገብታ መኪናዋን ስታስነሣ ፤

« ዝግ ብለሽ ንጂ » አላት

ዞር ብላ አይታው ፤ ፈገግ አለች ።

አጐናፍር እየነዳ ሲከተላት ፤ አንድ ነገር ከነከነው ። ‘ ታፈረች አንድ ነገር ሆናለች ፤ አንድ ነገር ሰምታለች ወይም ደርሶባ ታል እንጂ በደህናዋ እንዲህ አልሆነችም ። አለ ነገር ’ እያለ በሐሳቡ እያውጠነጠነ ጉዞውን ቀጠለ ።

እንደ ደረሱ እርሷ በሩን አስከፍታ መኪናዋን እግቢ አስገ ባች ። አጐናፍር ካጥር ውጭ ቆመ ። ግቢው ሰፊ መሆኑን ፤ አንድ ላንድሮቨርና አንድ አፔል ካራቫን ቆመው ተመለከተ ። ‘ እዚህ ሠፈር ብርና ርስት አትጠፋም ’ አለ በሐሳቡ ። ፊቱን ፈገግ አደ ረገ ። በዚህን ጊዜ ታፈረች መኪናዋን ላንድሮቨሩ ጐን አቁማ ወደ እልፍኝ ስትገባ አየ ።

ፊቱን አዞሮ ወደ መጣበት አግጣጫ ሲመለከት ፤ የኮረኮንቹ መንገድ ፤ እስከ አስፋልቱ መንገድ ድረስ ፤ ርዝመቱ አምሳ ሜትር ያህል መሆኑን ገመተ ። ‘ ብር አላቸው ለምን አስፋልት አያደ ርጉትም ’ ብሎ የታፈረችን አባት ታዘበ ። ታፈረች ብቅ ስትል አይቶ ባሰበው ነገር ጥቂት አፈር አለ ።

ታፈረች እንደ ገባች መኪናውን አዙሮ ጉዞ ጀመሩ ።

“ ምነው ፣ ጥቂት ቀፈፍ ያለሽ ትመስያለሽ ። እኔን ደሞ ዛሬ ደስ ብሎኝ ነበር ! ” አለ አጐናፍር ፤ ወሬውን ለመንገር ቸኩሎ ።

ታፈረችም አሁን ንግግሩ ከሱዋ ላይ ተነሥቶ አጐናፍር ላይ እንዲዞር ፈቃዷ ስለ ነበረ ፤ ባጋጣሚው በመደሰት ፤ ፈጥና ፤ « ምነው ፤ መልካም ነገር አገኘህ ? ” አለች ።

እንደዚህ ለማወቅ መጓጓቷ አስደሰተውና ፤ « ይኸውልሽ ! እኔ ወንድምሽ ባሌ ከመሔድ በመቅረቴ ፤ ከትናንት ወዲያ እንደዚያ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ለት በሦስት ቀን አንድ ዳቦ ካገኘሁ በቂዬ ነው ። የለመድኩት ነው።” አለ ወጣቱ ፤ በማስተዛዘን አነጋገር ።

“ እናትህ ከታመሙ ስንት ቀናቸው ነው ? ”

“ ዛሬ ሦስተኛ ቀኗ ነው ። እንደ ጉንፋን አርጎ ጀመራትና ባሰባት ። ”

“ ታዲያ ለምን ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል አልወሰድካቸ ውም ? ”

“ አይ ጋሽዬ ! ቦታ የለም ነው የሚሉት — እሺ አይሉም ።”
“ ጠይቀሃል ? ”
“ ምን መጠየቅ ያስፈልጋል ፤ ሲሆኑቀው ። ”
“ እንዴ ሳትሞክር ! ”
“ እየሞከሩ ያልሆነላቸው ብዙ ሰዎች ነግረውኛል ። ”

“ ታዲያ ማላከሚያ ገንዘብ ስታጣ ፤ ሌላ ብልሃት ስታጣ፣ በወሬ ተመርተህ ከመተው፤ አንተ ራስህ አትሞክርም ? ‘ ሰዉ እን ዴህ ብሏል ’ ብለህ ባንተ ሳይደርስብህ ፤ በወሬ ብቻ እናትህ ሲሞቱ ዝም ብለህ ታያለህ ? ”

“ እሱስ ውነት ነው ጋሼ ። ነገ እሞክራለሁ ። ብቻ የሴይቼ ንቶ ማጣፈሪያ የለኝም ። በግሯ ጉለሉ ድረስ ችላልኝ አትሔድም። መንገድ ትሞታለች ” አለ ወጣቱ ።

በዚህን ጊዜ የቡና ቤቱ ልጅ መጥቶ ፤ “ ምን ልታዘዝ ? ” አለ ።

“ አንድ ቡና ማኪያቶና አንድ ብርጭቆ ወተት — ትኩስ ? ” እያለ ወደ ታፈረች አየ ። ታፈረች ራሷን ነጣ፤ የአምንታ መልስ ሰጠች ።

የቡና ቤቱ ልጅም ፤ “ አንድ ቡና ማኪያቶና አንድ ግሬ ወተት ? ” ብሎ አረጋግጦ ሔደ ፤ እየሮጠ ።

“ ታዲያስ ? ” አለ አጐናፍር ፤ ወደ ልጁ ዞር ብሎ ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

« መቼም ክርስቲያን ነዎትና—የተማረ ሰው መቼም . . .» አለ ወጣቱ ፤ እየተቅለሰለሰ ።

« ምን ? የሰይቼንቶ መጫፈሪያ ነው ? » አለ አጐናፍር ።

« እዎ ጋሼ ። እርስዎ እንዳሉት ነገ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል እወስዳታለሁ—ማጫፈሪያ ካገኘሁ ። አጥቼ ነው ። »

« መልካም ። እንግዲያው ። እንቃጠርና ፤ ነገ ጠዋት እኔ መጥቼ አብረን እንወስዳቸዋለን » ሲል አጐናፍር ፤ ወጣቱ ፊቱ ቅይር ሲል እየው ።

« እዩ ጋሼ ይኽ ፡፡ ሱ ደግነት ምን ያረጋል ። ምን በወጣዎ ይደክማሉ ። ደግሞ እኔ የምወስዳት በሌሊት ነው ። ወረፋ ሳይበዛ ፤ እለዚያ አይቻልም ። የጠዋት ውርጭ ይጐዳዎታል ። »

« ግዴለም ፤ ላንተ ብዬ አይደለም ። ለእናቴ ነው ። ለእኔም በጠዋት መሆኔ፡ፍሩ ነው ሥራዬ ሳላረፍድ እገባለሁ » አለ አጐናፍር ፤ የወጣቱ ትዕግሥት እስከ ፡ ቼ እንደሚቀጥል ለማየት እየጓጓ ።

« እረ ይኸን ሁሉ መልፋት አያስፈልግዎም ። ደሞም እቤታችን ድረስ መኪና አይሔድም ። መንገድ የሌለበት ጕራንጕር ነው ። እዚያ ገብቶ መኪናዎ አትወጣም ። መኪናዎ ትጐዳበዎ ታለች » አለ ወጣቱ ፤ ድምፁ ወደ ንዴትና ተስፋ መቁረጥ እየተቀየረ ።

« ሲይቼንቶውስ ቢሆን መኪና አይደለም ? » አለ አጐናፍር ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግታ ፊቱን እያለበሰው ።

ወጣቱ የአጐናፍርን ነገር አኪያሔድ ሲገነዘብ ፤ በንዴት ብው አለ ። ግን ፤ ለመጨረሻ ጊዜ መሞከር ስለ ፈለገ ንዴቱን ዋጥ አድርጐ ፤ « ጋሼ እኔ እንደርስዎ ያለ ደግ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም። ማነው የኔን ደሃ እናት በገዛ መኪናው ፤ በብርድ በሌሊት ተነሥቶ 'ሐኪም ቤት ልውሰድ' የሚል ? አለርስዎ ማንም የለም ። ባያደርጉትም እንዳደረጉት እቆጥረዋለሁ ። አንድ ደግ ሰው ሲገኝ እኔ

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ጣበት ገንዘብ ሰጠኝ' አትለኝም ኖሯል ? ! እኔም ወዲያው 'እንቢ' እልህ ነበር ። አሁንም አትጨቅጭቀኝ ሒድ ! ! ”

“ ባልሔድ ምን ታረገኛለህ ? የማን አገር መሰለህ ? እኔም እዚህ ለመሆን መብት አለኝ ። ደሞ ካቲካላ ! እኔ ነኝ ለቦርዴ ገን ዘብ የምለምን ! እኔ የሰውዬው ልጅ ! ! ” ይደነፋ ጀመር ፤ ልጁ ።

አጉናፍር መስተዋቱን ጨርሶ ዘጋ ። ወጣቱ እየተንጐራደደ ፤ ከወዲያ ወዲህ ፤ ከወዲህ ወዲያ እየዞረ ፤ ድምፁን ከፍ አርጐ ፤ “ የኔ ብጤ ደሀ ሁሉ ፤ አሁን ትናንት ተነሥቶ አርጌ መኪና ፤ ነዳና ሴላ ጨን መናቅ ! አዬ ደሀ ! ጥጋብ አይችል ! የኛ መኳንንት ፤ አቤቱ ! ባለ ማርቸዲስ ሲሆኑማ ያኔ ባገርም አያስቀምጡንም ። ”

ታፈረች ነገሩ ስላላስደሰታት — ውትቷን ጨርሳ ነበርና — አጉናፍር ጠጥቶ እንዲሔዱ ፈለገች ። የአጉናፍርም ስሜት ይኸው ስለ ነበረ ጠጥቶ ፤ ከፍሎ መኪናውን አስነሣ ።

በሚከሰሱ አደባባይ ገርጊ አርጐ ወደ ቦሌ ጣቢያው አማ ጣጫ አመራ ።

“ ኧረ ፤ ልጁ እሺ ቢልህ ኖሮ ፤ ነገ ጠዋት ውነት ልትመጣ ኖሯል ? ” አለቻው ታፈረች ፤ ትኩር ብላ እያየችው ።

“ መቅጠፉን ማወቁን እንዲረዳው ብዬ ነበር ” አለ በፈገ ግታ እየተመለከታት ።

“ ግን እውነት ሆኖ ወይም ልጁ ለትንኮል እሺ ብሎ ቢሔድ ኖሮ ፤ ምን ልታረግ ኖሯል ? ”

“ እሺ አይልም እንጂ ፤ እኔ መች አጣሁት ። ”
“ ድንገት እሺ ቢል ኖሮ ? ልትመጣ ነበር ? ”
ጥቂት አሰብ አረገና ፤ “ አዎ ። እመጣ ነበር ” አለ አጉናፍር
“ እዬ ? ”

“ ሙች ። እንዲያውም በጠዋት ለመነሣት ጥሩ ምክንያት ይሆነኝ ነበር ። ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" መጥተህ ብታጣውስ ኖሮ ? "

" ሽርሽር ነዋ ! "

" እኔስ ከዚህ ሁሉ ገንዘቡን ሰጥቶ መገላገሉ ቀላል ይመስለ ኛል ። "

" ክፉ ሰይጣን ! ጊዜያችንን በከንቱ አጠፋብን " አለ አጐናፍር ፣ ነገሩን እየቀየረ ።

ዝም አለች ። እሱም ዝም አለ ። ሐሳብ ገባው . . . . .

አግጣጫ እየለወጠ ወደ ቦሌ ሲጠመዘዙ ፣ ታፈረችን ድን ገት ሐሳብ ገባት ። እጅግ አሠጋት ። አድማሱ ሲፈልገው ድንገት እንዳጋ ጣሚ ሠንገድ ያገኘን ይሆን ብላ ተጨነቀች ። የሚያልፍ የሚያገድመውን መኪና በይኗ እየተመለከተ ይጠባበቅ ጀመር።

" ዛሬ ከቀትር በኋላ አበራ—የበለጠ ጓደኛ ነው ፣ አብረው ነበር የሚኖሩት—ቢሮዬ መጥቶ ነበር " አለና አጐናፍር ዝም አለ ።

የታፈረች ልብ ፈረሱን ጫነ ። ሽምጥ ይጋልብ ጀመር ። አበራን ታስታውሰዋለች . . . 'አጠር ፣ ቀጠን ያለ ፣ ብስል ቀይ ፣ ራሱ ትልቅ ፣ ቀልደኛ ብጤ ። አዎ ፣ ከበለጠ ጋር አብረው መጥተው አብረው ነበር የሔዱት ። ታዲያ ፣ የፏንና የበለጠን ያችን ምሽት ደጋግሞ አብሮ መደነስና መጫወት ፣ ልብ ያለ አልመሰላትም ነበር ። አዎ ፣ እሱ እንዲያውም ከዚያች . . . ማ ነበረች ? . . . ማን ነች ? . . . አዎ ደብሪቱ ! አዎ ። ከሷ ጋር አፍ ብሎ ነበር ። እንኳን እኛን ልብ ሊል አራሱ ያለበትንም የሚያውቅ አልመሰለኝም ነበር ። ግን ፣ ምን ይታ ወቃል ? . . .' እያለች በሐሳቧ አነበነበች ። ለአጐናፍር ግን ቃል ሳት ተነፍስ ዝም ብላ ትመለከተው ጀመር ።

" በነገራችን ላይ—" ሲል አጐናፍር ።

'ሊያመጣው ነው ጣጣቱን ' ብላ በልቧ ወይናይኑን ትመለከተው ጀመር ።



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ምናለ ፣ አብረን ነው የምንሞተው ! " አለ ፤ በፈገግታ እቦታው ተመቻችቶ ፍሬኑን እየለቀቀ ።

" ሞት ሞት ነው ። የሞት ምርጫ አለው እንዴ ! " አለች ፤ በውሸት ሥጋት ።

" ምርጫ አለ ። ካብሮ መሞት ፣ አብሮ መኖር ይሻላል ። ከሁሉም ደግሞ አብሮ ኖሮ አብሮ መሞት ይበልጣል ። "

ዝም አለች ።
" ምነው መልስ ከለከልሽኝ ? "
" ለምኑ ? አስተያየትህን ተናገርክ ። ሰማሁ ።"
" ትስማሚያለሽ ? "
" በምኑ ? "

" ሰሚ ታፈሪች ። የምሬን ነው የምልሽ ። እኔ በሕይወቴ ፣ ልቤ ላንዲት ሴት እንኳን ፣ እንደዚህ ባንቺ እንደ ነሆለለው ይቅርና ፣ የጋለ ስሜት እንኳ ተሰምቶት አያውቅም ። በብዙ መንገድ ተመልክቼሻለሁ ! ለኔ የተፈጠርሽ ሴት አንቺ ነሽ ። በቃ ! ስለዚህ ፣ በበኩሌ አንቺን አግብቼ ለመኖር ቆርጫለሁ " አለ ። በቃ ወጣለት ! ፒው ! !

ዝም አለች ። ደቂቃው እንደ ሰዓት ረዘመበት ። ታጣፊ ቢታክተው ቦር ብሎ አያት ። ዐይኖቿን ፍቅርና ትካዜ ሞልተዋቸው አገኘ ።

" ምነው - ዝም አልሽ ? የማይሆን ነገር ተናገርኩ ? "
" እኔ እንጃ ፣ " ስትል ፣ ክው አለ ።

" እምልህ ፣ ብንጋባም ባንጋባም ፣ ዕወቀው — እኔ ካንተ በፊት አንድም ወንድ አላፈቀርኩም ፤ ወደፊትም አላፈቅርም ። ግን ፣ መጀመሪያ ሀሰኔ የቀድሞ ታሪካ ካወቅህ በኋላ ፣ እኔ ስላንተ ካወቅሁ በኋላ ፣ ምን እንደሚሆን እሠጋለሁ ። "

' ምን ማለቷ ነው ? በርሷ በኩል ምን ከባድ ነገር ቢኖር ነው ፣ "ምን እንደሚሆን እሠጋለሁ " ያለችው ? ' አለ እጉሮሮ ፣ በልቡ ። ' ባወቀው ሐሳቤን ያስለወጠኛል ብላ የምትገምተው ነገር አለ ማለቷ ይሆን ! '



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

እንግናፍር የመኪና መስተዋቱን አውርዶ ፣ “ ይኸ ምን መን ደር ነው ?” አለዉ ልጁን ።

ልጁም ጠጋ ብሎ ፣ “ ሞጆ ከተማ ነው ” አለው ።
“ ምንድር ነው ያ ሁሉ ሰው ? ”

“ ጋሼ ተፈራና ጋሼ ካብቴ ፣ በእትዬ ወርቂ ተጣልተው ነው። ሲደባደቡ ነበር ቅድም ጀምሮ ” አለ ፣ ሁሉን ዐዋቂው ልጅ ፣ በነ ገራቸው በመስልቸት ።

“ እንዴት ሰዉ አይገላግልም ? . . . አይጋደሉም ? ”

“ ገና ቅድም ጀምረው ነው ። ሲገላግሏቸው ደሞ ቆይተው ይጀምራሉ ” አለ ልጁ ፣ በታከተ አረጋዊ አነጋገር ።

“እዚህ አካባቢ ማደሪያ ፣ አልቤርጎ ፣ ሆቴል የት አገኛለሁ? ታውቃለህ ? ”

“ አዎ ፣ የበቀለ ሞላ አለልዎት ። ላሳየዎት ?” አለ ልጁ ፣ ‘ መኪናው ውስጥ ግባ ’ እንዲለው እየተመኘና መጓጓቱ በግ ልጽ እየታወቀ ።

እንዳሰበውም እንግናፍር መኪናው ውስጥ አስገባውና ልጁ መርቶ ወደ ቦታዉ ወሰደው ። ‘ ሳላወቀ ሁሉ እሩቅ ነው ’ ማለት ነው እንጂ ፣ ማደሪያ ቤቱ የሚሳት አልነበረም ። ደግሞም እዚያው ቅርብ ነበር ።

* * *

ታፈረች ፣ የቤቷን በር ከኋላዋ እንደ ዘጋች ፣ የማንቃ ሣሎኑን በመጫሚያዋ ታኮ ወግታ እያስጮኸች ፣ ወደ መኝታ ቤቷ በቀጥታ አመራች ። እሣሎኑ ውስጥ ፣ እንደ ሕልም የታዩዋትን ሰዎች በዘ ልማድ ‘ እንደምን አመሻችሁ ’ ብላ ፣ መለስ ቀለስ ሳትል ፣ መኝታ ቤቷ ገብታ ፣ መብራቷን አብርታ ፣ በሩን ቆለፈች ።

አልጋዋ ላይ ቁጭ እንዳለች ፣ የራስጌ መብራቷን አብርታ የተ ጣጠፈውን ወረቀት ከቦርሳዋ አወጣች ። ነጥላ ስታይ ፣ የተጻፈው


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ታፈረች በዘነመች ወሬ ተመስጣ ፡ የቀድሞ ነገሯ ጨርሶ ትቷት ባይሔድም ፡ አዕምሮዋ ሥር ተንገዝግዞ ስለ ነበር ፡ ዘነመች ስትጠቅሰው እንደገና ወደላይ ወጥቶ አዕምሮዋ ውስጥ መንሳፈፍ ጀመረ ። ከየት መጀመር እንደሚሻል መወሰን ለጊዜው አቅቷት ጥቂት አመነታች ።

" ተጣላችሁ ወይ ? " አለች ዘነመች ፡ በሰላ ቢላዋ ድፎ ዳቦ ማኸል ለማኸል እንደሚከፍል ቁስ ፡ ወደ ነገሩ እንብርት እራሷ እያሰላች ።

" አዎ - የለም . . . እኔ ምልኸ ፡ አልተጣላንም ብቻ ልንለ ያይ ነው ። "

" እ ! - እንዴት ? "

" ዲቃላ አለው ። "

" እምዬ ማርያም ! ! . . . አንቺ ታዲያ ' ከበለጠ ጋር ቀጠሮ አድርጌ ስለ ነበር ' ብለኸ ትጨነቂያለኸ ! — እኔ አላልኩሽም ? ወንዶች ሁልጊዜ ከወደ ኋላቸው አንድ ጭራ አያጡም ። "

ታፈረች እየተከዘች ፡ ዝም አለች ።

" ለመሆኑ ማን ነገረሽ ? ድንገት እውነት እንዳልሆነ ? " አለች ዘነመች ፡ የልቧን ውስጥ ደስታ ገትታ ፡ ነገሯንም መለስ አድ ርጋ ።

" እሱ ራሱ ነው " አለች ታፈረች ፡ በዝግታ ።

" እሱ ራሱ ! ? መቼ ፡ ዛሬ ማታ ? "

" አዎ ። በቃሉ አይደለም በጽሑፍ ነው ። እኔም የራሴን እሱም የራሱን ' ጉድ ' በወረቀት ጽፈን ተለዋወጥን ። ማለቴ ፡ በየግል አስተያየታችን እንዳችን ለሌላችን አስቀድመን ማሳወቅ ይገባናል — በኋላ ጋብቻችን እንዳይናጋ ፡ ወይም ጨርሶ እንዳይፈርስ የምንለውን ነገር — ተባብለን ነበር " አለች ታፈረች ፡ አሁንም ትዝትዝ እንዳለች ።

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

“ እይ ዘኔ ! ምን ኢሰመከዚህስ አይደለም ትያለሽ ። እያየሁት ባይኔ ። ያም ሆነ ይሀ ፣ በይ ! አንቺ እንግዶችሽ ዘንድ ፣ እኔም እቤቴ እን ሒድ ። ”

“ ምናለበት ብትሜወቺ ? ” አለች ዘነሙች ፣ በቅሬታ ።

“ መሽቷል ። ቤቴ ደርሼ ተኝቼ እንቅልፍ እስኪይዘኝ — ግፊ ቢይዘኝ — ውድቅት ይሆናል ። ነገ ሥራ ገቢ ነኝ ። እኔ ልጄ እንዳ ንቺ ትንገሽ እንቅልፍ አይበቃኝም ። እንኳን አምሽቼ በደኅናውም ቀን ጠዋት መነሣት ጭንቁ ነው ” አለች ታፈረች ፣ ሰዓቷን እያየች።

“ ዘንድሮስ እኔም እንቅልፋም ሆኛለሁ ። ብቻ ፣ ነገ ጠዋቱን በሙሉ እተኛለሁ ብዬ ነው ። እነሱ ያሰማቀፍ ድርጅቶች ባልደረ ቦች በመሆናቸው ትዳሚ ስለማይሠሩ ፣ ማምሸታቸውን በሙቄ ፈቃድ ተቀብያለሁ ። የመሰነባበቻ ግብዣ ነው ። አንዱ አገሩ መመለሱ ነው ፤ ከሁለት ዓመቱ በኋላ — እንግዲያው የማትሜወቺ ከሆነ — ”

“ እዎ ። እንውጣ ። ”

ተሳስመው ተሰነባበቱ ። ታፈረች ወዲያ ወዲህ ሳታይ ፣ በማ ሎት ትርምስምስ ማኸል ተሹለክልካ ወጣች ። ፔገሮዋን አስነሥታ በስንት ጣር አዙራ ለመሔድ ቻለች ። ሙዚቃዉ ፣ ከበሮውና የዘ ፋኙ የጐረነነ ድምፅ እስከ ጥቂት መንገድ ታፈረችን ሸኙዋት ።

ዘነሙች ማሎኗ ስትገባ ፣ ገበያዉ የበሰጠ ደርቶ ተመለከተች ። ማኸል ገብታ ታስካካ ጀመር ። በወንዶቹ የጐላ ወሬና ሣቅ ፣ በሴቶቹ ማስካካት ፣ በሙዚቃው ጩኸት ፣ በዘፋኙ ድምፅ መጕርነንና በደናሾች እንዘጭ እንዘጭ ! ዓለም ሰለፈች ። በገላ ግለት ኃይልና በትንፋሽ ብዛት ክፍሉ ተቃጠለ ። አቃጠለ ! የቤቱም አየር ፣ የላብ እንፋሎትና የሽቶና የቅባት መዓዛ ቅይጥ ሆነ . . . . . . . . . .



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## ዝግጅት

ቀኑ ቅዳሜ ስለሆነ ፣ ተስፋዬ ፣ ከበደንና ብርቄን መርካቶ በጠዋት ወስዶ ፣ ሁለቱ አዳራሾች መካከል አለው አስፋልት ሜዳ ላይ ካወረዳቸው በኋላ ፣ እዚያው ሥፍራ ፣ ልክ ከአራት ሰዓት በኋላ መጥቶ እንደሚወስዳቸው ነግሯቸው ሔደ ። እሱም በበኩሉ ፣ ለገሙ ጐፋ ኑሮው የሚያስፈልጉትን ነገሮችና ልብሶች — ዝርዝር ቀደም ብሎ አዘጋጅቶ ነበርና — ለመግዛት ተሠማራ ።

እንደ ተቃጠሩትም ስድስት ሰዓት ተሩብ ላይ ተገናኝተው ፣ ተስፋዬ እየነዳ ፣ ከበደ በግራ ፣ ብርቄ በቀኝ እኋላ ተቀምጠው ፣ የቤት መልስ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ከኋላ የተቀመጡት ሁለቱ ዐልፎ ዐልፎ በሹክሹክታ ከመነጋገራቸው በቀር ፣ በመኪናዉ ውስጥ ወሬ አልነበረም ። ተስፋዬ ከሐሳቡ ጋር ተያይዞ ፣ ብዙ መንገድ ሔደ ። ከተማውን ማኸል ለማኸል ሰንጥቆ ካለፈ በኋላ ፣ ወደ ሾላ በር ሲደርስ ፣ ሐሳቡ ወደ ቤቱ መፍረስ እና ወደሱና አበራ መለያየት ደረሰ ። አበራ ቤቱን ለቅቆ መሔድ እንዳለበት ሲያስብ ፣ ስለ ሠራተኞቹ ማሰናበት ጉዳይም ትዝ አለው ።

“ አበራ ቤቱን ለቅቆ መሔድ እንዳለበት ነግሯችኋል ? ”

“ የለም ፣ ምንም አላሉንም ” አሉ ብርቄና ከበደ ባንድነት።

“ እኔ ወደ ገሙ ጐፋ ለሥራ ተዛውሬ መሔዴ ስለሆነ ፣ ብቻውን ይኼን ትልቅ ቤት ታቅፎ የሚቀመጥ አይመስለኝም ። ምናልባት አፓርትመንት የገባ እንደሆነ እናንተ ሌላ ሥራ መፈለግ ይኖርባችኋል ። ”


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ብርቄ ወደ ከበደ ዞር ብላ ፣ ‘ እኔ አላልኩህም ታዲያ ’ በሚል አስተያየት ገጠመችው ። ከበደ ዝም አለ . . .

ተስፋዬ ንግግሩን መቀጠል አልፈቀደም ። ዝም አለ ። እኑ ሱም ዝም አሉ ። ጉዞው ቀጠለ ።

አቤታቸው ሲቃረቡ ፣ ከዋናዉ መንገድ ተጠምዝዞ መኪናዋ ወደ ቤታቸው ስታቀና ፣ ተስፋዬ የመኪናዋን ድምፅ አሰማ ። የውጪዉ በር ወዲያው ስላልተከፈተ ፣ እንደ ደረሰ ነድቶ መግባት አል ቻለም ። አቆመ ። ከበደ ፣ ከመኪናዉ ወርዶ በትንሿ በር ገብቶ ለመ ክፈት ቢሞክር እሷም ተቆልፋለች ። ይኸን ነገር ተገንዝቦ ተስፋዬ እያጉረመረመ ክላክሱን በኃይል አጮኸ ።

አበራ ሰምቶ መጥቶ ከፈተለት ። ተስፋዬ ገና መኪናዋን እን ዳቆመ ወርዶ ፣ “ ያ ሰካራም አሮጌ የት ሔደ ? ” አለ ።

“ ተሰማን ልኬዋለሁ ” አለ አበራ ፣ በዝግታ ።

የገዛቸውን አንዳንድ ነገሮች ፣ እንደ ተጠቀለሉ ተስፋዬ ታቅፎ፣ ከአበራ ጋር ወደ እልፍኝ አመሩ ። ብርቄ እና ከበደም ፣ የየራሳቸ ውን ኮተት ይዘው ወደ ማድቤትና ወደ ወጥ ቤት ሔዱ ።

“ የምትፈልገውን ሁሉ አገኘህ ? ” አለ አበራ ፣ ሣሎን እንደ ገቡ ።

“ ከሞላ ጐደል ” ብሎ ተስፋዬ ፣ ወደ መኝታ ቤቱ የታቀፈ ዉን ይዞ ገባ ።

አበራም ሣሎኗ ጠረጴዛ ላይ የተበታተኑትን ወረቀቶች ይሰ በስብ ጀመር ። ርቦታል ። ወደ ወጥ ቤት ጆሮውን ጣል ሲያደርግ፣ ከበደ ምሳ ለማደራጀት ጉድ ጉድ ሲል ተሰማው ።

ተስፋዬ ወደ ሣሎኑ ተመልሶ መጣ ። “ ታዲያስ ? ” አለው አበራን ፣ ወረቀት ሲያስተካክል እየተመለከተ ።

“ ብዙ ሥራ ሠራሁ . . . ማድረግ ያለብኝን ነገር ሁሉ ዝር ዝር አወጣሁ ። እ. . . ” ሲል አበራ ፣

“ ማድረግ ያለብኝን ? ” አለ ተስፋዬ ፣ በጥያቄ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰማ ነበር ። " እንደምን ዋሉ ፣ ጋሼ ተሰማ " አለው ከበደ። " ደስ ብሎኝ ዋልኩዋ ፣ እኔ ወንድምህ ! " አለ ተሰማ ። ከበደ በትዝብት ዐይን ተመለከተው ። ተሰማ ሞቅ ብሎታል ። " ጋሼ ተሰማ ፣ ይሙት አሁንስ አበዙት ! " አለው ከበደ ።

" ምንም አልቀመስኩ ። ትንሽ ነች ። ሁለት ብርጭቆ ነች ። እስክሰክር አልጠጣም ብዬህ ! ! ምነው ባክህ ! እኔ ቃሌን የማላ ክብር ሰው ነኝ እንዴ ? ውሀ ሲጠማኝ ጊዜ ፣ ጉሮሮዬ በጣም ሲደ ርቅ ጊዜ - ጉሮሮዬን ለማርጠብ ? "

" ይበሉ ። እኔ ምን ቸገረኝ — ብቻ ፣ ያምጡ ወረቀቱን እኔ ብሰጣቸው ይሻላል ! "

" ወግድ ባክህ ! አንተ ደግሞ የሰከርኩ ታስመስላለህ ፣ እንዴ ያው ! በጃቸው እኔዉ እሰጣቸዋለሁ ። "

" እኔ መቼ ሰከሩ አልኩ ። ብቻ — "
" ብቻ ፣ ምን ? በልኮ ! " አለ ተሰማ ፣ ጮሆ ።
" ጠጁ እንዳይሸታቸውና — "

" ወይ ጊዜ ! ወይ ጊዜ ! የማር ወለላ ሽታ የሚጠላበት ዘመን ደረስን ! ታዲያስ ? ጠጅ ጠጅ መሽተት ኃጢአት ነው በል ? ! "

" ለሁሉም ቦታ ቦታ አለው — አሁን ይስጡኝና — "
" ውነቱን ተናገር ፣ ሰክረሃል ነው የምትለኝ ! ! "

" ጋሼ ተሰማ ፣ እኔ እርስዎን የጠቀምኩ መስሎኝ ነው እንጂ ፣ በከፋት ከተረገሙትስ ይግቡና ይስጧቸው ። እኔ ገበታ ማንሣት አለብኝ " ብሎ ከበደ ፣ ዘር ሲል ፡

ተሰማ ፣ " በል እሺ እንካ ውሰድና ስጣቸው " አለና ወረቀ ቱን ለከበደ ሰጠው . . .

ከበደ ወስዶ ለአበራ ሰጠው ። አበራ ወረቀቱን አንብቦ ሲጨ ርስ ቆና አለ ። ፊት ለፊት መጋረጃው በተገለጠውና ፣ በተከፈተው

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

መስኮት አሻግሮ ወደ ውጭ እየተመለከተ ያስብ ገባ ። ቀና ብሎ እስተዋለውና ፣ “ ምንድር ነው ” አለው ተስፋዬ ።

“ የቤቱ ጌታ ናቸው ። ኮንትራቱን ሳፍርስ ካልክ እስካሥር ቀን ልቀቅ ። አለበለዚያ ፣ አይሆንም ነው የሚሉ ” አለ አበራ ።

“ ለምን ባሥር ቀን ? ”

“ እስከ ዐሥር ቀን ብቻ መጠበቅ የሚችል ተከራይ አግኝ ቻለሁ ። እሱ ካመለጠኝ በግድ የሚቀረውን አራት ወር ወይ መቀ መጥ አለብህ ፣ ወይ ኪራዩን ትከፍለኛለህ ነው የሚሉት ” ሲል መለሰ አበራ ።

“ እንዴ የዚህን ወር ኪራይ ከፍለናል ። ይኸው ዛሬ ጥር ሦስት ቀን ብቻ ነው ። ታዲያ ያሥራ አምስት ቀን ኪራይ በግርግር ለመብላት ነው ሐሳባቸው ? ” አለ ተስፋዬ ።

“ በኮንትራቱ መሠረት እኮ ፣ አራቱን ወር ብትቀመጥበትም ቤቱን ብትለቅም ፣ መክፈል አለብህ ነው የሚሉ ። ግን ፣ ከዚህ ለመ ዳን የፈለግህ እንደሆን ባሥር ቀን ውስጥ ልቀቅ ። ምክንያቱም እን ዳጋጣሚ የሚከራይ ሰው ተገኝቷል ። እሱ ካመለጠ ሌላ እስቲገኝ ለብዙ ወራት ቤቱ ይዘጋ ይሆናል ፣ ነው ክርክሩ ። ልክ ይመስለ ኛል ” አለ አበራ ።

“ በኮንትራቱ መሠረት ለማለት እንዴት ይቻላል ። ይኸ ፣ ‘ ፎርስ ማዦር ’ ነው ። ወደህ ሳይሆን መልቀቅ የተገደድከው ፣ ካቅምህ በላይ በሆነ ምክንያት ነው ። ስለዚህ ፣ በኔ አስተያየት ልክ አይመስለኝም ” አለ ተስፋዬ ።

“ አንተ የምትለው ልክ የሚሆነው ፣ ኮንትራቱ የተፈረመው በሁላችንም ስም ሆኖ ቢሆን ኖሮ ነበር ። ግን ፣ በሕግ ፊት ኮንትራት ተቀባዩ እኔ ነኝ ። ይሁን ባክህ ። እኔ እስከ ዐርብ በማይም ወጥቶ ሆን ምድር ወርጄ አፓርትመንት አገኛለሁ ” አለና አበራ ፣ ከሶ ፋው ላይ ተነሥቶ ወደ ቴሌፎኑ አመራ ። የስልክ ማውጫ ደብተ ሯን እያነሣ ፣ “ ለመሆኑ አንተ መቼ ነው የምትሔደው ? ” አለው ተስፋዬን ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

« እኔ እንጃ አርግጡን ። ግን ከሰኞ ጀምሬ ቢሮ የለኝም ። ስለ ዚህ ከተምቀት በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ መሔድ አለብኝ ብዬ ገምቻለሁ—። »

አበራ የሚፈልገውን ስልክ ቁጥር አግኝቶ ደወለ ። ጥቂት ጠበቀ ። መልሰ አጥቶ ዘጋውና ወደ ሶፋው ተመለሰ ። ስልክ ደውሎ ከመሳቀቁ ሌላ አንድ ነገር ልቡን አሳዝኖታል ። ይኸውም የተስፋዬ ሁኔታ ነው ። ተስፋዬ ስለ ቤቱ ጉዳይ ሲናገር ፣ ልክ እንደ ውጪ ሰው ሆኖበት ። ስለ ኮንትራቱ ጭቅጭቅ ሲነሣ—ምንም እንኳ ኮንትራቱን የፈረመው እሱም ቢሆን — የሁለታቸውም እንጂ የርሱ የግሉ ብቻ አልነበረም ። ስለዚህ ፡ ' እኛ የምንለቀው ' በማለት ፈንታ ' አንተ የምትለቀው ' የሚለውን አነጋገር አበራ አልወደ ደለትም ። በጣም ተገረመ ፤ አዘነ ። ባንድ ሳምንት ውስጥ የቀድሞው ኑሮው ከመሠረቱ ተለወጠበት ። ሁለቱን ጓደኞቹን በሞት ሲያጣቸው ፣ ተስፋዬን ደሞ በመንፈስ ባዕድ ሆኖ አገኘው ። ቢሆንም አላማረረም ። በጊዜውና በሁኔታው ብቻ አዘነ ።

አበራ ለቤቱ ጌታ ወረቀት መጻፍ ጀመረ ። መልሱ ፣ ' እሺ እርስዎ እንዳሉት ሰኞኑን ቤት ፈልጌ እለቃለሁ ' የሚል ነው ። ከዚህ ሌላ ብዙ ሐተታ የለበትም ። መጥሪያዉን ደውሎ ከበደ ሲገባ ፣ « ተሰማ ምሳውን በልቷል ? » ብሎ ጠየቀ ።

« የለም እየበላን ነው » አለ ከበደ ።

« ይቅርታ ፣ ሒድ ብሉ ። ሲጨርስ ፣ ተሰማን አቤቱ ጌታ ዘንድ እልከዋለሁ » አለ አበራ ። ከበደ ወጣ ።

« ምን አልካቸው ? »

« እስከ ማክሰኞ ጥር 13 ቀን እለቃለሁ ። »

« ከነገ ጀምሮ ዐሥር ቀን ብቻ መሆኑ ነው ? » አለ ተስፋዬ እያሰበ ።

« ዛሬ ሦስት ነው ። »

« ታገኛለህ ፣ እንደዚህ ባጭር ጊዜ ውስጥ ? »

@OLDBOOKSPDF



t.me/OLDBOOKSPDF

" በግድ ማግኘት አለብኝ " አለ አበራ ፣ ቁርጥ ባለ አነጋገር ። ተስፋዬ ዝም አለ ። ሐሳብ ገባው . . . . .

ስልኩ ተደወለ ። አበራ ሔዶ አነሣው ።
" አበራ ነኝ . . . . . "
" እንደምን ዋልክ . . . "
" የለም ። ሁለት ሦስት ቀን ሆኖኛል ካየሁት ። ምነው ? . . ."
" እረ ! ! መቼ ? የት ? . . . "
" እይ ! እኔ ለማንም አልነግርም ። "
ስምና የስልክ ቁጥር ጻፈ ።
" እምናግዝህ ነገር እንዳለ ፣ ዝግጁ ነን ። . . . "
" መልካም ፣ እንግዲያው ስልክህን እጠብቃለሁ ።"

አበራ ስልኩን ዘግቶ ወደ ግሉን መቀመጫዉ ተመለሰ ። ተስፋዬ ይነግረኛል ብሎ በጒጒት ጥቂት ከጠበቀ በኋላ ፣ አበራ ሐሳብ እንደ ገባው ተመልክቶ ፣ " ማነው የደወለው ? " አለ ።

" አድማሱ ነው ። ያጒናፍር አርቅ ዐርፈዋል ! ! እሱን ከት ናንት ጀምሮ ፈልጐ አጥቶት ነው እዚህ የደወለው ። "

" የት ሔደ ? "
" አያውቅም ። "

" ምናልባት አጒናፍር ከሌላ ቦታ አደጋውን ሰምቶ በቀጥታ ወደ አባቱ መሬት ሔዶ እንደሆን ? " አለ ተስፋዬ ።

" አልመሰለኝም ። "
" ዛሬ ማታ ድሬዳዋ መሔዴ ተሰናከለ ! "

" መቼስ ምን ይደረግ። በጓደኞችን ድንገተኛ አደጋ ሲደርስ ! "

" እውነቱን ለመናገርስ ከሆነ ፣ አጒናፍር ጓደኛችን አይደ ለም ። በውነቱ እስከዚህ የት እናውቀዋለን ? የተዋወቅነው በበ ለጠ ሳቢያ ነበር ። በተለይ ከኛ ጋር ምን የቆየ ባልንጀርነት አለው?" አለ ተስፋዬ ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

በዚያኛው ፈንታ ስላልተበላ ርዳታው ዋጋ የለውም ነው ? ” አለ አበራ ፤ እንጀቱ እየተጣመነመነ ።

“ ይኸን አይደለም የምለው እኔ ፤ ‘ጅቡ ቢበላውምና ቢሞት ፣ የራሱን ድርሻ ነው የሞተው ፣ የሌላውን አይደለም’ ነው የምለው ” አለ ተስፋዬ ።

በዚህን ጊዜ ስልኩ ተደወለ ። አበራ ፈጥኖ አነሣው ። “ ሃሎ እ . . . እ ? . . . ”

“ እሶኛ አለው እንዴ ! ” አለ አበራ ሳያስበው ። በኋላ ግን ጥቂት አፈረ ።

“ ታዲያ ምን ማረግ ይሻላል ? . . . . . . ”

“ እሺ ” ብሎ ስልኩን አስቀመጠ ።

ተስፋዬ ቀና ብሎ አበራን አየና ፤“ማነው ፤ አድማሱ ነው ?” አለ ።

“ አዎ ! ”

“ ባለ እሶኛው ደሞ ማነው ? ”

“ አንጐናፍር ። ”

“ ባልንጀራችን ? ! እንዴት ታዲያ ምስጢሩን እኛ ሳናውቅ!” አለ ተስፋዬ ፣ በፈገግ ።

ከበደ ከወደ ወጥ ቤቱ በኩል ብቅ አለና ከርከራቸውን አጽ ረጠ ። ተሰማ ምሳውን መጨረሱን ተናገረ ። አበራ ወረቀቱን አን ሥቶ ‘ ለቤቱ ጌታ ስጥ ’ ብሎ ለተሰማ እንዲሰጠው አዝዞ ለከ በደ ሰጠው ። ለሰይቹንቶ መግፈሪያም ሁለት ብር ጨምሮ ሰጠው። ከበደ ሲወጣ አበራ ወደ መኝታ ቤቱ ሔደ . . .

ከበደ ወረቀቱን ይዞ ማድቤት ተመለሰ ። ምሳ ተበልቶ በናጨ ተፈልቶ እቦሉ ተጠጥቷል ። ሁለተኛዉ ፈልቶ ከበደ ሲደርስ ጀበ ናው ወጥቶ እንዲሰክን ተቀምጧል ። ሳቦሉ ጊዜ የተጨሰው ዕጣን


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ጨቦ አላለቀም ። አሁንም ትንሽ ትንሽ ጭሱ ቡልቅ ቡልቅ ይላል። ረከቦቱ ላይ ያሉት ብርቄ ዛሬ ገዝታቸው ከመርካቶ የመጡት ስድስት ሽልምልም ሲኒዎች ናቸው ።

ቡናዉ ሰከኖ ፣ ብርቄ አንዱን ስኒ እንደ ሞላች ፣ የውጪው በር መጥሪያ ተደወለ ። ‘ የማይወዱት ሰው በሁለተኛ ይመጣል ’ አለች ብርቄ በልቧ ። ተሰማ ሞቅታው በርዶለታል ። ምሳውና አቦሉ ቡና ሥራቸውን ሠርተዋል ። ተነሥቶ በር ሊከፍት ወጣ ።

“ እኒህ ሽማግሌ ደሞ ፣ ይኸን ወረቀት ሊያደርሱ ሲሔዱ ፣ እንደገና ለከረው ይመጡ ይሆን ? ምን ፍርጃ ነው እያ ! ” አለ ከበደ፣ ነገሩን እንደ ጥያቄም አርጎ ።

“ ባክህ ተዋቸው ። እሳቸው ይመክሩሉ ብለህ አትጠራጠር . . . እንደ ፍጥርጥራቸው ። ደሞስ ትንግዲህ እዚህ ቤት እህል ውሃችን አልቋል ” አለች ብርቄ ።

“ ቢሆንም አይገባም ። እሳቸው እንደሚያረጉት ማረግ ጥሩ የሥራ ወረቀት ለማግኘት መጥፎ ነው ። ”

“ ትንግዲህ ማን ይቆጥራቸዋል ። እዚያችው እልጃቸውጋ ሔደው ይዘፍዘፉ እንጂ ! ” አለች ብርቄ ።

ተሰማና ወልደ ሥላሴ ወደ ማድቤቱ ሲቃረቡ ኮቴያቸው ተሰማ ። ከበደና ብርቄ ዝም እንዳሉ ፤ ሁለቱ ተያይዘው ከውጪ ገቡ ።

“ ምነው ጋሼ ደሞ እንደሚጠሉት ሰው በሁለተኛ ይመጣሉ?” አለች ብርቄ ፤ በቀልድ ።

“ አይ አንቺ ። ዘላለም የዚህ የቡናና ያተላው ነገር አይለቅሽ” አለ ወልደ ሥላሴ ። ከኪሱ ሁለት ጉርድ ያለበት አንድ የሎተሪ ቲኬት አውጥቶ ለብርቄ ሰጣት ።

ብርቄ እስከዚህ ለቲኬቱ አልጓጓችም ። ተቀብላ የቡናውን ጭላጭ እምታፈስበት ነጭ ሣህን አጠገብ እወለሉ ላይ ጣል አረገችው ።


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

እነሱ አይደሉም ? እ ? ቃዲያ እስቲ እነሱ ይቅመሷትና ይይዋት ። ያኔ ከገሩናቸው ያገኟታል ” አለች ብርቄ ፡ እርር ድብን እያለች ።

“ ይኸንስ ቢሉ አንቺ ለሴትኛ አዳሪዎች ማን ጠበቃ ገዛሽ ?” አለ ከበደ ።

“ ማን ይከለክለኛል ማንንስ ባግዝ ። አንተ ደሞ ዘላለም ላለው ብቻ ነው የምታግዝ ። እንዴት ደሀ መጠጥ ሽጣ ብታድር ለምን ትሰደባለች ? ስንቱ ጨዋ መጠጥ ቤት ከፍቶ ይተዳደራል ” አለች ብርቄ ።

“ አይ መጠጥ ቤት ከፍቶ ጨዋነትን እንኳ አርሺው ” አለ ወልደ ሥላሴ ፡ በርጋታ ።

“ ለምን ? እኔ አሁን ገንዘብ አግኝቼ መጠጥ ቤት ብከፍት ጨዋ አይደለሽም ልትሉኝ ነው ? የንግድ ሥራ ነው እኮ - ምናል ባት ! ”

“ በየመጠጥ ቤት ወንድ ሁሉ የሚንጋጋው መጠጥ ፍለጋ ብቻ ነው ልትይኝ ነው ? መጠጥ ብቻ ከሆነ የሚፈልገው ፡ ገዝቶ እቤቱ አምጥቶ ሊጠጣ ይችላል ። ወጪውም ይቀንሳል ። ግን ይኸ አይደለም ፍላጐቱ ” አለ ወልደ ሥላሴ ፡ አሁንም ረጋ ብሎ ።

“ እዬ ! ? አንድ ወይ ሁለት መለኪያ ዐረቂ ገዝቶ በኪሱ ይዞ እቤቱ ይሒዳ ! ከዚህ የበለጠ መቼም ባንደዜ ብዙ ሰው መግዛት አይችልም ” አለች ብርቄ ፡ በፌዝ ።

“ አንቺ መቼም ድርቅ ካልሽ አትቻይም ። የወሩን እንጃ አንድ ጠርሙስ ገዝቶ እቤቱ አያረግም ! . . . ለማናቸውም በቃ ሌላ ወሬ አምጪ ” አለ ወልደ ሥላሴ ።

“ እዎ ፤ ሌላ ጨዋታ አምጡ ” አለ ተሰማ ፡ ከተል አርጐ ። በልቡ ከብርቄ ጋር ይስማማል ። እርሱ መጠጥ ቤት የሚሔደው ጠጥቶ ከሰዎች ጋር ለመደሰት ነው ። የደራ ወሬና ጨዋታ ፍለጋ ነው ።

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ዝም አሉ ። ከበደም የወልደ ሥላሴ ድምፅ ቀየር በማለቱ ጥቂት ልቡ ቆጣ አለ ። ተሰማን ፤ “ ይኸን ወረቀት ‘ ለቤቱ ጌታ ይስጡ ’ ብለዋል ፤ ጋሼ አበራ ” አለውና ወረቀቱን ሰጠው ።

ሦስተኛው ቡና ተቀዳና ተጠጣ ። ከበደና ተሰማ ተያይዘው ወጡ ። ብርቄና ወልደ ሥላሴ ብቻቸውን ቀሩ ።

ወልደ ሥላሴ ከመቀመጫው ተነሥቶ ይቦርቅ ጀመር ። ብር ቄም እንደ ጉድ እየተመለከተችው ፤ “ ምን ሆነሃል ! አብደሃል እንዴ ? ” አለችው ።

“ እጅግ አለመጠን ደስ ብሎኛል ። ”

“ ምን አገኘህ ? ”

“ ወደ ጽፈት ሥራ ተዛወርኩ ። ዋናዉ መዝገብ ቤታችን ዶሴ አከናዋኝ ሆንኩ ! ” አለ በሙሉ ደስታ ።

“ እንኳን ደስ ያለህ ! . . . ሁልጊዜ ያንተና የኔ ዕድል ሆድና ጀርባ ናቸው ። እኔ መከራ ሲያገኘኝ አንተን ይቀናሃል ! ” አለችው ።

“ ምን መከራ አገኘሽ ? ” አለ ወልደ ሥላሴ ፣ ምናልባት እሱ የማያውቀው አዲስ የደረሰባት ነገር እንዳለ ብሎ ፣ ለመስማት በመ ጓጓት ።

“ ምነው አከታትሎ ባሳዳሪዎቼ ላይ የደረሰውን እያወቅህ እንዳዲስ ነገር ትጠይቀኛለህ ? ” አለች ብርቄ ፣ በስጨት ብላ ።

“ እ ! እሱ ነው እንዴ ! እኔ ደሞ ሌላ ነገር መሰሎኝ ። ለሱማ እኔ ብልሃት ሠርቼልሻለሁ ” አለ ወልደ ሥላሴ ።

ብርቄ ፣ ገና እሷ ሳታዋየው አስቦ ለርሷ ሥራ መፈለጉ — ብልሃት ሠርቻለሁ ያለው ሌላ አይሆንምና — በጣም አስደሰታት ። ግን ፣ ለምን እንደዚሁ ውለታ እንደሚውልላት ፣ ለምን ዘወትር ከሥሯ እንደማይጠፋ እርግጠኛ ነገሩን አታውቅም ። የመጀመሪያ ባሏ ይሁን እንጂ ፣ የልጃገረድነት ባሏ እንኳ አይደለም ። እንዲያውም እንደ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ስለ ጣውንቶቿም ስታ ስብ ፡ ‘ ባልንቱ ለኔ ፡ የትም ዋለ የትም እመሽ ፡ ተመልሶ የሚመጣው እኔጋ ነው ’ ብላ በልቧ ታስናብታቸዋለች። ወልዴ ሥላሴ ግን ፡ ብርቄን እስቲያገኝ መቆያ አርጎ ነው ፡ ብሬ ቱን የሚያስባት . . . . .

“ የምን ብልሃት ልጄ ? ” አለች ብርቄ ፡ ለስለስ ብላ ።

“ መሥሪያ ቤታችን ቡና ቤት ውስጥ ሥራ አገኝቼልሻለሁ” አለ ፡ ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ ።

“ ስንት ሊከፍሉኝ ? ”

“ ሀርባ አምስት ብር ። ብቻ ፡ አማርኛንና አራት መደብ መግር አለብሽ—ቶሎ ቶሎ ። እኔ አሁንም ‘ ትችያለሽ ’ብያቸዋለሁ ።”

ብርቄ ከደስታና ከድንጋጤ ብዛት መሬት ለማይፍ ዞረባት ። ወዲያው ለመመለስ አቃታት ።

ወልዴ ሥላሴ ፡ ዝምታዋ ለጊዜው አልገባውም ። ሁኔታዋንም ልብ ብሎ አልተመለከተም ። እሱ ከደስታዋ ብዛት ፡ እንቃ ትስመ ኛለች ብሎ ገምቶ ነበር ። ግን ፡ ዝም አለች ። ግራ ገባው ። ሙንፈሱ ወደ መጣቀትና ወደ መናደድ አዘነበለ ። “ ምንው ? አንሰሽ ? ” አለ ፡ በምፀት ።

“ ምን ያንሰኛል ደሞ ! ባይሆን ይበዛብኝ እንደሆን ነው እንጂ!”

ወልዴ ሥላሴ በዚህ መልስ ወዲያው ተመለሰ ። እጅግ ደስ አለው ። “ ዋናው ነገር ትንሽ አማርኛና ቁጥር ለማወቅ መጣጣር አለብሽ። ”

“ የቡና ቤት ሒሳብ እስከዚህ የቱ ሆነና ነው ። በቃሌ እያ ቅተኝም ። ”

“ ማታት ፡ አያቅትሽም ። ብቻ ፡ እችላለሁ የሚል ሴላ ሲኖር ቁጥርና ትንሽ ጽፈት የማይችለውን ማይም አይቀጥሩም ። አሁን ለጽፈት ሥራ መዝገብ ቤት ቅጠሩኝ ሲባል ፡ ‘ ስንተኛ ደርሰ ሃል ? ’ ይላሉ ። ግን ፡ ዐሥራ ሁለተኛ እስቲጨርስ የሚማረው ለሥ



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ራው አስፈላጊ ሆኖ አይደለም ። ግን ይጠይቃሉ ። በመሥሪያ ቤታችን ላለው ለብዙው ሥራ ፈረንጅ አገር ሔዶ መማር የሚያስፈልግ አይ ደለም ። ግን ይጠይቃሉ ። የምስክር ወረቀት የሚባል ነገር አምጡ ይላሉ . . . አንቺ ” አለ ፤ ወደ ብርቄ ዞር ብሎ ፤ “ ማታ ማታ ትንሽ ብትማሪ ምን ችገረሽ ? ”

“ ከእንግዲህ ተምሬ የት ልደርስ ? እባክህ ተወኝ ” አለች፤ በመሰልቸት ቁና እየተነፈሰች ።

“ እስከዚህ ብዙ አያስፈልግሽም እኮ ። ከዚህ ቀደም ደሞ ‘ ትንሽ ተምሬያለሁ ’ ትይ የለም ? ትንሽ አማርኛ ለስሙ ያህል ማል ገዝገዝ ነው ። ትንሽ ቁጥር ደሞ ። ”

“ ሥራውን እለዚህ አላገኘውም ማለት ነው ? ” አለች ትኩር ብላ ፤ እያየችው ።

“ አይ እሱስ ሥራው አለሽ ። ብቻ ፤ እኔ ቶሎ የቡና ቤቱን ገንዘብ ያገርነት ጠቅልለሽ እንድትወስጂ አስቤ ነበር ። ደሞዙም ያኔ እጥፍ ይሆናል ። ከኔ አዲስ ደሞዝ እኩል ሲሆን ምንም አይቀ ቀረው ብዬ ነው ። ”

ብርቄ በሐሳብ ባሕር ተዋጠች ። እውነት አልመሰላት አለ ። በወር እጥፍ ዐርባ አምስት ብር ማግኘት ! እዬ ፤ አይደረግም ! ግን የማታ ትምህርት ነገር የሚቻል አልመሰላት አለ ። ኧረ ዐርባ አም ስትስ ቢሆን የትና የት ነው ። ያውም እሳትና ጭስ ሳይነካት ! ዋናው እሱ ነው ። ከእሳትና ጭስ መገላገል ! አዲሱ ሥራዋ ቡናና ሻይ ማፍላት ቢሆንም እንኳ ጥሩ ነው ። በኮረንቲ ነው የሚፈላው ።

“ ከመቼ ጀምሮ ነው ያሰብከው ? ”

“ ምኑን ? ሥራ ፍለጋውን ነው ? ”

“ አይ ፤ የምጀምረው መቼ ነው ሥራውን ማለቴ ነው ። ”

“ እ ። በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥም ልትጀምሪ ትችያለሽ፤ ከፈለግሽ ። ”

“ ጥሩ ። ለጌቶቼ ይኸንኑ እነግራቸውና መልሱን እነግርሃለሁ።”

@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ብርቄ ታያት ! የቡና ቤቱ እመቤት ስትሆን ። በደስታና በሐሳብ ሰከረች ። “ እህል ወኃ ካለን መቼም አይቀርም ። እስቲ ለሁሉም ገብሬል ያውቃል ። ”

“ አስቢበት ፣ ሁሉንም ። በበኩሌ አስቤበት ጨርሻለሁ ።አብረን ከሆን ፣ ሥራም ትምህርትም አብረን ውለን እናመሻለን ። ትምህርቱንም እኔ አግዝሻለሁ . . . በይ አሁን ልሒድ ! ዕቁብ ዳኛ ዘንድ መሔድ አለብኝ ። ጉዳይ አለኝ ” ብሎ ተነሣ ። ብርቄም ብድግ አለች።

ወልደ ሥላሴ ወደ በሩ ሲሔድ ፣ ከበደ ከውጪ መጥቶ እበሩ ላይ ድቅን አለ ። “ ጋሼ ወልዴ ፣ ‘ እባክዎን ሥራ ይፈልጉልኝ ’ ብዬ ለመጠየቅ ነበር የመጣሁት ” አለ ከበደ ።

“ አሽከር የሚፈልጉ ሰዎች እንዳሉ እስቲ መሥሪያ ቤት አጠያይቅልሃለሁ ። ”

“ የመላላክ ሥራ እዚያ ቢገኝማ እንዴት ጥሩ ነበር ።”

ብርቄ በልቧ ከበደ እንዴት ወገኛ ነው ብላ ታዘበችው ። ወልደ ሥላሴ ግን ፣ “ አዬ ! እሱ የት ይቻላል ። አሁን ተላላኪነት የሚቀጠሩ ዘጠነኛና ዐሥረኛ የደረሱ ናቸው ። አንተን ግን እሺ ብሎ ይቀጥረኛል ብለህ ነው ” አለ ፣ ንቀቱን ለመሰወር እየሞከረ ። ከዚያ ወልደ ሥላሴ ወጥቶ ሔደ ።

ከበደ ብርቄን ፣ “ በያ ፍራንኬን ስጭኝ ” አላት ።

“ ምነው ምን አስቸኮለህ ? የት ይኸርብህ የምጠፋ መሰለህ?”

“ ለሱ አይደለም ። ወይም ይኸን እመሬት የጣልሽውን ሎተሪ ስጭኝና የቀረውን ሰሞኑን ትሰጭኛለሽ ” አለ ከበደ ።

“ እሱማ ጥሩ ። በል ውሰደው ። ብር ተስሙኒውን ሰሞኑን እስጥሃለሁ ።

ከበደ ሎተሪውን ይዞ ወጣ ። ብርቄ ስኒዎቿን ታጥብ ጀመር ። የቀን ሕልሟንም ጀመረች......



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ዐሥራ ሁለት

### ውሳኔ

አንድ ሰው ፈተና ሲገጥመው ፡ ዓለም በሙሉ ተሰብስባ አንድ ነጥብ ብቻ ትሆናለች ። አእምሮው ከዚያች ነጥብ ውጭ ምንም ነገር አይታየውም ፤ አይሰማውም ። ከትናንት ወዲያ ፣ ዐርብ ማታ ፣ አጐናፍርም ይህ ዕድል ገጠመው ፣ ዓለም በሙሉ ተሰብስባ አንድ ነጥብ ብቻ ሆነች—የታፈረች ወረቀትና የሠፈረባት መልእክት ። ከዚህ ውጭ ሌላ ነገር አልታየው አለ ። በሥራዉ የደረጃ ዕድገት ማግኘቱ ፣ ያባቱ ሕመም ፣ የልጁ ነገር ፣ ሌላው ቀርቶ ፣ ታፈረች ለለ ራሱ ፣ የጻፈላትን ስትመለከት ‘ ምን ተሰምቷት ይሆን ? ’ የሚል ሐሳብ እንኳ ጨርሶ ከአእምሮዉ ተሰወሩ ። ወረቀቷን አንብቦ እንደ ጨረሰ ፣ እንደ ዕብድ ከአዲስ አበባ የከንፈ ሞጆ አልቤርጐ ተከራ ይቶ እስከ ገባበት ጊዜ ድረስ ፤ የሐሳብ አጀብ በአእምሮው ውስጥ ተተራመሰ እንጂ አንድ ቁልጭ ያለ ነገር አላሰበም ነበር ። በኋላ ግን ፣ ቀልቡን ገዝቶ ነገሩን ለመተንተን ቻለ ።

አሁንም አፓርታማው ቁጭ ብሎ ፣ እንደ መጣ ለአድማሱ እንዲደውልለት የገፋፋውን ስሜቱን ገትቶ ፣ ከዐርብ ማታ አንሥቶ እስካሁን የደረሰውን በአእምሮው ይከልስ ጀመር . . . .

አሁን ቀልቡን ገዝቷል ። መንፈሱም ተረጋግቷል ። አእም ሮዉ የበላይ ሆኗል ። ዓለምም አንዲት ነጥብ ብቻ መሆኗ ቀርቷል።

ዓርብ ለት ማታ ግን ታፈረች ከበለጠ ጋር ፣ ታፈረች ከጆን ቴይለር ፣ በለጠ ወደ ታፈረች ሲገሠግሥ መኪና አደጋ እንዳገኘው፣ በርሷ ሳቢያ ባገኘው መኪና አደጋ ምክንያት መሞቱ ፤ እነዚህ ብቻ ነበሩ፣ ሕልዉናውን ቀስፈው፣ ግራና ቀኝ፣ ፊትና ኋላ እንዳይመለከት

@OLDBOOKSPDF



t.me/OLDBOOKSPDF

" የት እንደ ሔደ ፣ ታውቃለህ ? . . . "
" መቼ ? . . . "

" ጥሩ ። የመጣ ወይም የደወለ እንደሆነ ፣ እቤት ነው ያለሁት በሉት . . . "

" እኔም እፈልገዋለሁ " ብሎ ፣ ስልኩን አስቀመጠና ወደ መኝታ ቤቱ ገባ ።

ልብሱን አወላልቆ ገላውን ለመታጠብ ሙቅ ውሃውን ለቀቀ። ዐርብ ለት ጠዋት ያያዘው ነው ። የማህን ጎንዳው እስቲሞላ የሦስት ቀን ጢሙን በጥንቃቄ ተላጨ፤ ውሃውን በርዞ ነፈር ሲል ገብቶ መታጠብ ጀመረ ። እንደ ወትሮው ለማፏጨትም ፣ ለማንጎራጎርም ሞከረ ። ከንቱ ሆነ ። መንፈሱ ተበጥብጧልና ሁኔታዉ ለዘፈን አልተመቸም . . .

ውሃውን ዳግመኛ ሞልቶ እንደገና ገባ ። ሦስተኛ ጊዜ ንጹሕ ውሃውን ሞልቶ ፣ ሳሙናውን መትቶ መታጠብ ፈራ ። ሲጨርስ የመታጠቢያ ማህኑን ካጠበ በኋላ ፣ ለቅንጦት አራተኛ ጊዜ ሞልቶ እንደ ገባ ፣ ስልኩ ተደወለ ።

በችኮላ ወጥቶ ውሃውን ወለሉ ላይ እያዝረበረበ ፣ ቴሌፎኑን አነሣ ። አድማሱ ነው ።

" ደኅና ። እንደምን ከረምክ . . . "
" ወደ ላንጋኖ ሔጀ ነበር — በድንገት . . . "

" የለም ። ማንንም አላገኘሁም ። ከመጣሁም ገና ላንተ ብቻ መደወሌ ነው . . . "

' የለም ፣ አልደወልኩም ። ለምን ? ደህና አደለችም እንዴ ?" አለ እየተርበደበደ ።

" መቼ ደውለህላት ነበር ? . . . "

" ትናንት ? ታዲያ አገኛሀት ? . . . ምናለች ? ድምጿ . . . እን ዴት ? "



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ምን ፣ አሟት ነበር ? . . . "

" ለብርቱ ጉዳይ እፈልግሃለሁ ። ልትመጣ ትችላለህ ፣ አሁን?"

" መልካም ። እጠብቅሃለሁ " ብሎ ስልኩን ዘጋ ።

መታጠቢያ ቤት ገብቶ ፣ ተለቃልቆ ወጣ ። በችኮላ ልብሱን መልበስ ጀመረ ። ሸሚዙን እንደ ለበሰ መታጠቢያ ቤት ተመልሶ ጥርሱን ፋቀ ። በሸሚዙ ሳሎን ቁጭ ብሎ አድማሱን ይጠብቅ ጀመር ። ሰሞኑን ወስፋቱ ተዘግቶ እህል በደንብ ስላልተመገበ ፣ ገላውን ታጥቦ ሲወጣ ረኃብ ሞረሞረው ። በድንገት ብድግ ብሎ ምና ምን ፍለጋ ወጥ ቤት ገባ . . .


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

## ዐሥራ ሦስት

### ፈረስ

ወልደ ሥላሴ ቅዳሜ ማታ ጠጥቶና አምሽቶ ቤቱ ገባ ። ምክንያት ፈልጐ ፣ ጠብ አንሥቶ ብሪቱን ደበደባት ። ከወትሮው ጠንከር አርጐ ስለ ደቆሳት እሑድን ሙሉ ቀን ተኛች ።

እሱ ግን እሑድ ከቀትር በኋላ ብርቄን አምጥቶ ባቅራቢያው ያለውን ፣ ‘ይለቀቃል’ ያላትን ቤት ከውጭ አሳያት ። ባል አግብታ ቤቱን ለቃ ለመሔድ የምትዘጋጀውን ቤት ስለሚያውቃት ፣ ውስጡንም ብርቄን አስጐበኛት ። ብርቄ ሳታይ ፣ ሴትዮዋ ከወልደ ሥላሴ ጋር ተጠቃቀሱ ። ሙሉ ምስጢር ያለው ፈገግታ ፈገግ አሉ ።

ወልደ ሥላሴ ብርቄን ይዞ ከሔደ በኋላ ፣ የብሪቱ ቡና አጣጪ ወዳጆቿ እተኛችበት ሔደው ፣ ስለ ርሷ በመቆጨትና በመቆርቆር ስለ ወልደ ሥላሴና ስለ ብርቄ ነገሯት ። ከመካከላቸው ብርቄ ፣ የዱሮ ሚስቱ መሆኗንና ፣ ሊታረቃት ዘወትር የሚመኝ መሆኑን የሚያውቁ ነበሩ ። ብሪቱ ግን ምንም የቁጣ ቃል ባትናገርም ፣ ውስጥ ውስጡን አርራ ነበርና ፣ ይነዝራትና የቆሳሰለ የነበረውን ሰውነቷን ረስታ ፣ ብድግ ብላ አልጋዋ ላይ ተቀምጣ አዳመጠች ። እመት በለጥሻቸው የሚባሉት የቅርብ ጐረቤቷ ቡና ላፍላ ብለው እዚያው አፍልተው ፣ የቀሩት ጐረቤቶች ሁሉ ተጠርተው ሊጠጡ መጡ ። ከመካከላቸው ጣውንትነታቸው በግልጽ የታወቁትም እንኳ ሳይቀሩ ፣ ባንድ ቃል ለብሪቱ አዛኞች ሆኑ ።

ከዚህ ሁሉ ሐተታ ፣ ብሪቱ ልብ ውስጥ እንደማይፋቅ ሆኖ የተጻፈው ፣ ‘እሷን አባሮ ብርቄን ለመታረቅ’ አስቧል የሚባለው ነገር ነው ። ባሏን ሌሎች መጋራታቸውን ባትወድም ፣ አዲስ ልማድ አይ



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ከታፈረች ጋር ክትናንት ወዲያ ማታ 'የመረጃ' ልውውጥ አደረግን " አለና ከውስኪው ጉንጬት አደረገ ፣ አጐናፍር ።

" አልገባኝም ። የምን 'መረጃ'?"

" ቸኮልክ . . . እኔ የምስጢር ታሪኬን አንድ ሳይቀር ፣ እርሷም እንደዚሁ በወረቀት ዘርዝረን ተለዋወጥን ማለቴ ነው ። "

" ይኸ አዲስ ነገር ነው ! "

" ዓላማችን ፣ 'በኋላ "የቀድሞ ታሪክ" መጥቶ ጋብቻችንን ከሚያናጋብን ፣ ሁለታችንም ዐውቀን ብንገባበት ወይም ቆርጠን ብንተወው ይሻላል' የሚል ነበር ። "

" ገባኝ " አለና አድማሱ ፣ ሐሳብ ገባው ። ዝግ ብሎ ፣ የውስኪ ብርጭቆውን አንሥቶ ተጐነጨ ። ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ከሠፈነ በኋላ ፣ " ታዲያ 'መረጃውን' ካየህ በኋላ ውሳኔ ላይ ደረስክ?" ብሎ ፣ አጐናፍርን አትኩሮ ተመለከተው ።

" አንድ ነገር አረጋግጫለሁ ። ታፈረችን በጣም እወዳታለሁ!"

" ታዲያ ባንተ በኩል ለማግባት ችግር የለብህማ " ሲል አድማሱ ፣ የታጠፈ ወረቀት አውጥቶ አጐናፍር ሰጠውና ፣ ውስኪውን ጭልጥ አደረገ ። ጓደኛው ሲያነብም ፣ በፊቱ ላይ የሚነበብ ነገር ፍለጋ ትኩር ብሎ ያስተውለው ጀመር ።

" ታዲያስ? " አለው አድማሱ ፣ አንብቦ ጨረሰና ።

" ምን 'ታዲያስ' ትለኛለህ ፣ አነበብከው አደለም ታሪኳን !"

" በበኩሌ ጋብቻን ሊያግድ የሚችል ምንም ነገር አልታየኝም ። "

" የቴይለርስ ጉዳይ? የቀድሞ እጮኛዋስ ጉዳይ? "

" የዶሪስስ ጉዳይ? አፓርትመንትህ ያለው የሕፃን ልጅ ፎቶግራፍስ? ወይስ እኼህ ነጥቦች ለታፈረች እሰጠሃት ወረቀት ውስጥ አልተጠቀሱም!? "


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

አጐናፍር በረጅሙ ተንፈሰና ፣ ወረቀቱን ከአድማሱ እጅ ወስዶ ኪሱ ውስጥ ከተተው ። " ያልተናዘዝኩላት እንዳችም ኃጢያት ስለሌለ በዚህ አትሥጋ ። የሆነው ሆኖ ፣ በበኩሌ ላገባት ቆርጫለሁ ። "

" እሺ ያለችህ እንደሆን ! " አለው አድማሱ ።

" አጐናፍር ውስኪ ቀድቶ አንዴ ጉንጨት ካለለት በኋላ ፣ " ከተገደድኩም ጠልፌ እወስዳታለሁ ! ! " አለ ፣ ቁርጠኛ በሆነ አነጋገር ።

አድማሱ የአጐናፍርን አባባልና አኳኋን ሲመለከት በሣቅ ተን ከተከተ ።

" የምሬን ነው የምልህ ! ! " አለ አጐናፍር ፣ በቁም ነገር ። " ደግሞ የሚያሥቅ ነገር አይመስለኝም ። "

" ሳትወድ በግድ ያገባሃት ሴት ምን ትረባሃለች ። "

" ሐሳብዋን ካልቀየረች ፣ ለመጋባትማ በመሠረቱ ተስማም ተን ነበር ። እኔ የእምልህ ፣ ሐሳቧን እንድትቀይር አልፈቅድላትም ነው ? "

" በፊት የተስማማችውማ ጉድህን ሳታውቅ ነው ። አሁን " ጉድህን ከእውነተኛዉ ምንጭ — ከራስህ — ፀውቃዋለች ። "

" ታዲያ ባለፈ ታሪክ ምክንያት ፣ ስንት ዘመን ተዳፍኖኖሮ፣ ዛሬ እንደበት ያገኘው ፍቅራችን እንደገና ይዳፈን እንዴ ?! "

" በል ፣ እራታችን ቀርቧል መሰለኝ ፣ በዚህ እንጣላ ። ሔደን እንብላ " ብሎ አድማሱ ፣ እጁን ለመታጠብ ተነሣ ፤ " ና ቅደም ' አለው ።

ራታቸውን በልተው ከጨረሱ በኋላ ትንሽ ተጨዋውተው ፣ አጐናፍር ድካም ስለ ተሰማው ፣ "እድርሰኝና በጊዜ ልተኛ" አለው ።

አድማሱም በጉዳዩ ፈጥኖ ተስማማ ። " እዎ ። ከጥቂት ጊዜ በፊት ነው ከመንገድ የገባኸው ። ነገ ደግሞ ፣ በጠዋት መነሣት ይኖርብሀ ይሆናል ። "



@OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያ ተያይዘው በመኪና ወጡ ። መንገድ ላይ እንዳሉ ፣ "ሰሞኑን በስልክ ስታነጋግራት ፣ እንዴት ነበረች ? ከድምጿ ፣ የተቀየረች ትመስላለች ? " አለ አጐናፍር ።

' ከዐርባ ማታ ወዲህ ተገናኝታችኋል ወይ ? እኔ ፈልጌ ፈልጌ አጣሁት ' ስላት ትናንት ጠዋት ፣ የሥጋትና የፍርሃት ድምፅ ነው የአሰማችኝ — በስልክ ። ሆኖም ፣ ይኸ ለደህንነትህ ማሰቧን ያሳያል እንጂ ፣ ከነዲቃላህ ለማግባት ዝግጁ መሆኗን አያረጋግጥም ! "

" እሷስ ከጀን ቴይለር ልትደቅል ትችል አልነበረም ? ይኸ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ! "

" ያጋጣሚም ሆነ የሌላ ፣ አሁን ያለው እውነታ ፣ አንተ አንድ የአምስት ዓመት የጀርመን ክልስ ወንድ ልጅ አለህ ። ታፈረች ግን ምንም የጥቁር አሜሪካን ልጅ ዲቃላ የላትም ። ስለዚህ ፣ ውሳኔዋን እስክትሰማ መጠበቅ ብቻ ነው ያንተ ፋንታ " አለው አድማሱ ።

አጐናፍር ትንሽ በስጨት ብሎ ፣ " ልጁ ያለው ከናቱ ጋር ጀርመን አገር ። እንዴት እሱ 'በመካከላችን ሊመጣ ይችላል' ብላ ልትፈራ ወይም ልትሠጋ ትችላለች ? " አለ ።

በዚህን ጊዜ አጐናፍር አፓርተማ ሕንፃ ዘንድ ደረሱ ።

" ግባና አንድ ለመንገድ ብለህ ትሔዳለህ ። "

" መልካም . . . ! ታፈረች እስተዋይ መሆኗን አትዘንጋ ። የምታደርገውም ውሳኔ የበሰለ እንደሚሆን አትጠርጥር ። "

" ውሳኔዋ ብስልም ሆነ ጥሬ እኔ እሷን ማግባት ነው የምፈልገው ! ! "

" እንግዲህ ይኸን ሁለታችሁ ወስኑ ። እኔን ልቤን ባታደርቀኝ ደስ ይለኛል ። ይልቅ ሌላ ወሬ አምጣ ። "

" እኔ ሌላ ወሬ የለኝም ! "

' እንግዲያው ዝም እንበል ! ' አንድ ለመንገዱ ልጠጣና በሰላም ቤቴ ልሒድ . . . በነገራችን ላይ ፣ " እኛ በለጠ የዳጣቸው ሽማግሌ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

" ነገርኩሽ እኮ። እኔ 'አባቴ በሽታቸው ጠንቶባቸዋል' አልኩ እንጂ ፣ 'ዐርፈዋል' አላልኩሽም ነበር " አለ አድማሱ ።

" ቢሆንም ፣ መንገር ነበረብኝ ። "

" እኔም እስካሁን አልነገርኩትም እኮ ! ለዚህ ነው በአስቸ ኳይ አሁን እንገናኝ ብዬ ያስቸገርኩሽ ። ስለዚህ ፣ አብረን ሆነን ነገ ጠዋት እናርዳው ። "

ታፈረች፣'እሺም እንቢም' ለማለት ተቸገረች። አወላወለች ። አመነታች ። አድማሱም ለጊዜው የሚለው ስለ ጠፋው ዝም አለ ። ትንሽ አሰላስሎ፣ " እስካሁን ሁለታችንም አልነገርነውም ። እን ዲያውም እኔ ዛሬ ቤቱ ወስጄ ራት ሳበላው፣ እርሙን ያበላሁት ነበር የመሰለኝ ። ግን ፣ እንቺን ይህ ጉዳይ የቆጨሽ ስለ መሰለኝ፣ ብቻ ዬን ዛሬ ማታውኑ ሳረዳው አልፈለግሁም ። ደግሞም ትንሽ ጉስ ቁልቁል ብሏል — ቅድም ሳየው " አለ ።

" ምናልባት እሱ በኔ መገኘት ደስ አይለውም ይሆናል " አለች እያቅማማች ።

" ሰው እኮ በደስታውና በሐዘኑ ጊዜ አጠገቡ እንዲገኙ የሚ ፈልገው የሚወዳቸውንና የሚያቀርባቸውን ነው ። "

በግልጽ አብራርቶ ባይለውም ፣ ወዴት አግጣጫ እንደሚያ መራ ገብቶታል ። ግን ዝም አለች ።

" የኔ ሐሳብ ፣ ነገ አንድ ቦታ ተገናኝተን ፣ ልክ ከጠዋቱ በአ ንድ ሰዓት እሱ ዘንድ ለመድረስ ነው ። "

" እስከዚያስ በስልክ እንዴ ደውሎለት አባቱ መሞታቸውን ያወቀስ እንደሆን ? " የሚል ጥያቄ ሰነዘረች ።

" ውነትሽን ነው ። እስቲ ዘዴ እፈልጋለሁ . . . . . ታዲ ያስ ፣ ትመጫለሽ አብረሽኝ ፣ ነገ ጠዋት ? " .......

* * *

እጐናፍር የአፓርተማው ደወል ደጋግሞ ሲደውል ሰምቶ ነቃ። የራስጌ መብራቱን አብርቶ ሰዓቱን አየ ። ሳንድ ሰዓት ሰባት ደቂቃ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ድንገት ብድግ ብሎ መኝታ ቤቱ ገብቶ ልብሱን ለባበሰ ። ወደ ሣሎን ሲመለስ አድማሱና ታፈረች የሉም ። ላንዳፍታ ግራ ገባው ። ወዲያው ከወደ ወጥ ቤቱ አግጣጫ ድምፅ ሰማ ። “ አድማሱ ! ምንድር ነው የምታደርጉት ? እኔ ቁርስ አልበላም ” አለ ።

አድማሱ ወደ ሣሎን እየመጣ፣ “ ቡና ለማፍላት ፈልጋ ነው፣ ታፈረች ” አለ ።

አጐናፍር ሶፋው ላይ ተቀምጦ ዝም አለ ።

ሦስት ሰዓት ላይ አድማሱ እሦስታቸውም ቢሮዎች ደውሎ፣ ለቅሶ ስላለባቸው እንደማይመጡና ምናልባትም ፣ ከከተማ ውጭ፣ የሚሔዱ መሆኑንም ጠቁሞ ሲጨርስ ፣ ስልኩን ነቀለው ። ሦስቱም አብረው ውለው ፣ ማታ ታፈረችን አድርሶ ፣ አድማሱ ወደ ቤቱ ሔደ ።

*　　*　　*

የአጐናፍር ሽማግሌዎች ቀጠሮ ተሰጧቸው እንደ ወጡ ፣ የታፈረች ወላጆችና የቅርብ ቤተ ዘመዶች በጉዳዩ በሰፊው ሲወያዩ ቆዩ . . .

“ ሰውዬው ፈት ነው ለካ ! ይኸም ብቻ አይደል ፣ ያቺው ፈረንጅ ሚስቱ ልጅ ወልዳታለች አሉ ። ወደ አገሩ ሲመጣ ነው ፈቷት የመጣ ! !

“ ታዲያ ፣ ለስንቱ የመኳንንትና የመሳፍንት ልጅ ልጃችንን እንድንድር ስንለመንና እኛም ብናግርጥ ኖረን ፣ አሁን ለዚህ ማን ነቱ ላልታወቀ ፈት ፣ እንደ ጋለሞታ ለሁለተኛ ሚስትነት ልጃችንን እንዳር ? ” አሉ የታፈረች የአባቷ ታላቅ ወንድም ። ለቤት አያቷ የበኵር ልጅ ፣ ለታፈረች አባት የሁለቱ ታላቅ ናቸው ።

“ ልጁ እዚያ እሰው አገር ለረጅም ጊዜ እየተማረ ሲኖር ስሕተት ሠርቶ ይሆናል ። ደቅሎም ይሆናል ። በወንድ ልጅ ላይ ሁሉ


@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

ከታተለው ያ የቀድሞ ዕጮኛዋ ወይም አባቱ እንዳይሆን ?! ”አሉ የበዙር ልጃቸውን አተኩረው እየተመለከቱ ።

“ እኔ አልታመንም ማለት ነዋ ! ” ብለው ራሳቸውን እየነቀነቁ ፣ ታላቅ ወንድም ዝም አሉ ።

በዚህን ጊዜ የታፈረች ትልቋ አክስት ፣ “ ሁሉም ይሁን በጀ ! ግን ፣ እቧ ሁሉንም ነገር ወውታ አገባዋለሁ ካለች ፣ እኛ ምን ኃይል አለን ለመከልከል ? እኛ እምቢ ብንል ከማግባት ልናግዳት እንችላለን ወይ ? ቅያሜ ብቻ አይሆንም ወይ ትርፉ ? ” አሉ ።

“ ‘ እንቢ ’ ብላን ፣ ከቃላችን ወጥታ ካገባችው ፣ ጋብቻዋ እንዲባረክ አለ መመረቅ ብቻ ሳይሆን ፣ ተወግዛ ከቤተ ዘመድ ማኅበር ትወጣለች ። በቅድሚያ ይኸን ማወቅ አለባት ” አሉ ታላቅ ወንድም ፣ ጥያቄውን ባለመመለስ መውጫ አግኝተው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን የታፈረች እናትና አባት የነርሱ ጉዳይ ያልሆነ ይመስል ፣ ምንም አስተያየት አልሰነዘሩም ። የታፈረች አባት ብዙ ጊዜ የታላቅ ወንድማቸውን ሐሳብ ይከተላሉ ። የታፈረች እናት ደግሞ የባላቸውን ።

የሆነው ሆኖ ፣ ታላቅ ወንድምየው አሁን ያሉትን ፣ የታፈረች ወላጆች የሚቀበሉት ለመሆናቸው ፣ እፊታቸው ላይ ምንም ምልክት አይታይም ።

ከጥቂት ደቂቃ ዝምታ በኋላ ፣ “ እኔ ልጄን በምንም ምክንያት ቢሆን ስረግም አልገኝም ። ጋብቻዋን እንኳን ማውገዝ ፣ አልቃወምም ” ብለው ፣ አያት ቆንጠር ቆንጠር እያሉ ወጡ ። የታፈረች እናትም ተከተሏቸው ። የቀሩት ተነሥተው ባይወጡም ፣ የብዙዎቹ ልብ ከአሮጊቷ ጋር ወጥቷል . . . . . . .



@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF

@OLDBOOKSPDF
t.me/OLDBOOKSPDF